**DSpace Institution**

**DSpace Repository** | **http://dspace.org**

Ethiopian Languages and Literature - Amharic | Thesis and Dissertations

2018-11-05

# þÿ è 3 e ð + b . } • @ ` - › K • K è þÿ - } s • “ è ; M p • 3 = • u • ` u ë þÿ “ d ` # ì p › ð ( “ 0 “ ö u - u d u þÿ ` Ø • › - M p p ³ * • u

þÿ ® ¨ e , (

http://hdl.handle.net/123456789/9102

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

# ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ

## ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

## የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)እና ስነጽሁፍ- አማርኛ ትምህርት ክፍል


## ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

# የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን መጠቀም በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ችሎታንና የመጻፍ ተነሳሽነትን ለማጎልበት ያለው ሚና፤ በአጣዬ ሁለተኛ ደረጃናመሰናዶ ትምህርትቤት በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት


በኮከብ አማረ



ነሀሴ/2010ዓ.ም

ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ

# የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን መጠቀም በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ችሎታንና የመጻፍ ተነሳሽነትን ለማጎልበት ያለው ሚና፤ በአጣዬ ሁለተኛ ደረጃናመሰናዶ ትምህርትቤት በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት

አማርኛን በማስተማር ዘዴ (TeAm) ለትምህርት ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ቴሲስ)


በኮከብ አማረ

አማካሪ

ዶር. ማረው አለሙ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)እና ስነጽሁፍ- አማርኛ ትምህርት ክፍል

ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ



ነሀሴ/2010 ዓ.ም

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን መጠቀም በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ችሎታንና የመጻፍ ተነሳሽነትን ለማጎልበት ያለው ሚና፣ በአጣዬ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርትቤት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፣ በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በኮከብ አማረ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል።

የፈተና ቦርድ አባላት፣

አማካሪ ------------------------------------------------ ፊርማ ------------------ ቀን -----------------

የውስጥ ፈታኝ -------------------------------------------------- ፊርማ ------------------ ቀን ---------

የውጭ ፈታኝ -------------------------------------------------- ፊርማ ------------------ ቀን ----------

# ምስጋና

እውቀታቸውንና ጊዜአቸውን ሳይሰስቱ የጥናቱን ርዕስ አቅጣጫ ከማስያዝ ጀምሮ ልዩልዩ መረጃዎችን በመስጠት ረቂቁን እያነበቡ በማረም የማያቋርጥ ድጋፋቸውንና ገንቢ አስተያየቶችን እንዲሁም ማስተካከያዎችን በመስጠት ለረዱኝ አማካሪዬ ዶ/ር ማረው አለሙ ምስጋናዬ ጥልቅና ልባዊ ነው፡፡

የማስተማሪያ ቴክስቱንና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመገምገም፣ ስታትስቲክሳዊ ስሌቶችን በማገዝ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ደጋግመው በማንበብ፣ በማስተካከል፣ ሙያዊ አስተያየቶችን በመስጠት ለተባበሩኝ ዶ/ር እንድሪስ አባይ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

የነበረኝን የቤተሰብ ሃላፊነት በመሸፈን ሳይሰለች ላበረታታኝ ውድ ባለቤቴ ደሳለኝ አሳምነው፤ በጽህፈት ስራ፤ በሀሳብ፣ በሞራልና በገንዘብ ለደገፉኝ ቤተሰቦቼና ልጆቼ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

በመጨረሻም አስተያየት በመሰጠት፣ መረጃ በመሰብሰብና በማረም ለተባበሩኝ የስራ ባልደረቦቼ፣ በሀሳብ፣ በሞራልና፣ በልዩልዩ ስራዎች እገዛና ትብብር ላደረጉልኝ የትምህርትቤቱ አመራሮችና በዚህ ጥናት ለመሳተፍ ፍቃደኛ ለሆኑ ተማሪዎች የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# አህጽሮተ-ጥናት (Abstract)

*የጥናቱ ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን በመጠቀም መጻፍን መማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል የሚኖረውን ሚና መፈተሽ ነው፡፡ ዓላማውን ለማሳካትም ፍትነትመሰል(Quasi-experiment) የጥናት ንድፍ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በሰሜን ሸዋ ዞን በአጣዬ ከተማ አስተዳደር በአጣዬ የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት በ2010 ዓ.ም በዘጠነኛ ክፍል ሲማሩ ከነበሩ በ17 መማሪያ ክፍል ከሚገኙ1015 ተማሪዎች መካከል በተራ እጣ ንሞና ዘዴ በተመረጡ ሁለት መማሪያ ክፍሎች የተገኙ 92 ተማሪዎች ናቸው፡፡በመሆኑም በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች መጻፍን የሚማር ቡድንና ያለሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች በተለመደው መንገድ መጻፍን የሚማር ቡድን በማድረግ የመጻፍ ክሂል ትምህርትን በ8 ሳምንታት ለ17 ክፍለ ጊዜያት ተምረዋል፡፡ ከተሳታፊዎቹም ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የመጻፍ ችሎታ በፈተና፣ ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት በመጠይቅ አማካይነት ተለክተው መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ መረጃዎቹም በአማካይ ውጤት፣ በመደበኛ ልይይት፣ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልተው ተተንትነዋል፡፡ የጥናቱ ግኝቶች እንዳመላከቱትም ያለሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹ በተለመደው መንገድ መጻፍን ከተማሩት ተማሪዎች ይልቅ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን በመጠቀም መጻፍን የተማሩት በመጻፍ ችሎታቸው ጉልህ (t(90)= 4.974፣ P=0.000) መሻሻል ከማሳየታቸው ባለፈ የተጽዕኖ ደረጃው (effect size) ከፍተኛ ሆኖ (eta squared = 0.22) ተገኝቷል፡፡ በተመሳሳይ በመጻፍ ተነሳሽነታቸውም በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የተማሩት ተማሪዎች ጉልህ (t(90)= 2.742፣ P=0.007) መሻሻል አሳይተዋል፤ መካከለኛ የተጽዕኖ ደረጃም (eta squared = 0.077) አሳይቷል፡፡ ከጥናቱ ግኝቶች በመነሳትም በአማርኛ ቋንቋ በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች መጻፍን መማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ያዳብራል፤ ብሎም የመጻፍ ተነሳሽነት ያሻሽላል ወደሚል ድምዳሜ ተደርሷል፡፡ ከግኝቶቹ በመነሳትም ስነትምህርታዊ የመፍትሄ ሀሳቦች ተጠቁመዋል፤ የወደፊት የምርምር አቅጣጫዎችም ተመላክተዋል፡፡*

# የይዘት ማውጫ


ምስጋና.................................................................................................... i

አህጽሮተ-ጥናት (Abstract)........................................................................ ii

የይዘት ማውጫ .......................................................................................iii

የሰንጠረዥ ማውጫ .................................................................................. vi

ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ ............................................................................ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ.......................................................................................... 1

1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር.................................................................................. 8

1.3 የጥናቱ አላማ ...................................................................................... 13

1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት ................................................................................ 13

1.5 የጥናቱ ወሰን........................................................................................ 14

1.6. የጥናቱ ውስንነት ................................................................................... 15

1.7. የቁልፍ ቃላት ብያኔ ................................................................................ 15

ምዕራፍ ሁለት፤ የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ ...................................................... 17

2.1 የሃሳብ ማደራጃ ቢጋሮችና የመጻፍ ችሎታ ...................................................... 17

2.2 የሃሳብ ማደራጃ ቢጋሮችና የመጻፍ ተነሳሽነት ................................................. 24

2.3 የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር፣ የመጻፍ ተነሳሽነትና የመጻፍ ችሎታ ትስስር ......................... 26

ምዕራፍ ሦስት፤ የአጠናን ዘዴ..................................................................... 28

3.1 የምርምሩ ስልት ..................................................................................... 28

3.2 የጥናቱ ተሳታፊዎች ................................................................................. 28

3.3 የማስተማሪያ ቴክስቶች አዘገጃጀትና የማስተማር ትግበራ ...................................... 29

3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ................................................................... 31

3.4.1 ፈተና.................................................................................................. 31

3.4.2 የጽሑፍ መጠይቅ ..... 33
3.5 የአጠናን ሂደት ..... 34
3.6 የጥናቱ ስነምግባራዊ ሁኔታ ..... 36
3.7 የመረጃ አተናተን ዘዴ ..... 36
ምዕራፍ አራት፤ የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ..... 39
4.1 የጥናቱ ውጤት ትንተና ..... 39
4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ..... 45
ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሀሳቦች ..... 48
5.1 ማጠቃለያ ..... 48
5.2 መደምደሚያ ..... 51
5.3 የመፍትሄ ሀሳቦች ..... 52
ዋቢዎች ..... 54
አባሪዎች ..... 61
አባሪ ሀ. የሙከራ ቡድኑ መማሪያ መልመጃዎች ..... 61
አባሪ ለ. ለሙከራ ቡድኑ የተሰጠው ትምህርት እቅድ ..... 85
አባሪ ሐ. ለቁጥጥር ቡድኑ የተሰጠው ትምህርት እቅድ ..... 95
አባሪ መ. ቅድመጥናት (pilot) የቀረበ የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቅ ..... 102
አባሪ ሠ. የዋናው ጥናት የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቅ (የተሻሻለው) ..... 107
አባሪ ረ. ቅድመጥናት (pilot) የቀረበ የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና ..... 109
አባሪ ሰ. ለዋናው ጥናት የቀረበ የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና (የተሻሻለው) ..... 113
አባሪ ሸ. የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቁ በቅድመጥናት (pilot) ወቅት የፍተሻ ውጤት ..... 115
አባሪ ቀ. የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቁ በቅድመጥናት (pilot) ወቅት ..... 116
አባሪ በ. በቅድመትምህርት ወቅት የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቁ አስተማማኝነት ..... 117

አባሪ ተ. በቅድመትምህርት ወቅት የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቁ የውጤት ስርጭት ወጥነት ........ 119

አባሪ ቸ. በድህረትምህርት ወቅት የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቁ አስተማማኝነት...... 120

አባሪ ነ. በድህረትምህርት ወቅት የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቁ የውጤት ስርጭት ወጥነት ........ 121

አባሪ ኘ. በቅድመትምህርት ወቅት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተናው የውጤት ስርጭት ወጥነት ........ 122

አባሪ አ. በድህረትምህርት ወቅት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተናው የውጤት ስርጭት ወጥነት ........ 123

አባሪ ከ. የሙከራ ቡድኑ ቅድመትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት ውጤት........ 124

አባሪ ወ. የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት ውጤት ........ 125

አባሪ ዘ. የሙከራ ቡድኑ ድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት ውጤት........ 126

አባሪ ዠ. የቁጥጥር ቡድኑ ድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት ውጤት ........ 127

አባሪ የ. የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመትምህርት የመጻፍ ችሎታ ውጤት........ 128

አባሪ ደ. የሙከራ ቡድኑ ቅድመትምህርት የመጻፍ ችሎታ ውጤት........ 129

አባሪ ጀ. የቁጥጥር ቡድኑ ድህረትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት ........ 130

አባሪ ገ. የሙከራ ቡድኑ ድህረትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት ........ 131

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ 4.1 የቡድኖቹ ቅድመትምህርት የመጻፍ ችሎታ አማካይ ንፅፅር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ........................................................................................................................ 39
ሠንጠረዥ 4.2 የቡድኖቹ ድህረትምህርት የመጻፍ ችሎታ አማካይ ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ........................................................................................................................ 41
ሠንጠረዥ 4.3 የቡድኖቹ ቅድመትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት አማካይ ን ጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ........................................................................................................................ 42
ሠንጠረዥ 4.4 የቡድኖቹ ድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት አማካይ ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ........................................................................................................................ 43

# ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

በየዘመኑ የተነሱ የቋንቋ መማር ንድፈሃሳቦች የመጻፍ ክሂልን በመማርና በማስተማር ስልቶች ላይ የራሳቸውን ተጽዕኖ አሳድረዋል፡፡ ለምሳሌ የባህርያዊያን የመማር ንድፈሃሳብ እስከተዳከመበት1960ዎቹ (እ.ኤ.አ) ድረስ በቋንቋ ማስተማር ውስጥ የመጻፍ ክሂል የተዘነጋ ሆኖ ቆይቷል (Hyland, 2009; Usó-Juan, Martínez-Flor & Palmer-Silveira, 2006)፡፡ በወቅቱ ለንግግር ቋንቋ ትኩረት ይሰጥ ስለነበር መጻፍ የሰዋስውና የቃላት እውቀት ማጠናከሪያ በመሆን ትክክለኛ ንግግርን ለማቅረብ በሚያስችልበት መንገድ ይቀርብ ነበር፡፡ ይህ በመሆኑም የተነሳ ብዙዎቹ የቋንቋ ማስተማሪያ መርሃግብሮች ላይ የሚቀርበው የመጻፍ ክሂል ትምህርት በተማሪዎች የጽሁፍ ቅርጽ ትክክለኛነት ላይ ያተኮሩ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ በተለይም ችግር ያለባቸውን አረፍተነገሮች በማስተካከልና አረፍተነገሮችን በትክክል በማቀናጀት ከመዋቅር ልምምድ በሚገኝ ትክክለኛነት ላይ ያተኮረ የትምህርት አቀራረብ ይዘወተር ነበር፡፡ ሆኖም ግን ይህ የመጻፍ ክሂል አቀራረብ በውጤት ላይ በማተኮር ተማሪዎች በመጻፍ ስራ ለሚያልፉባቸው አእምሯዊ ሂደቶች ትኩረት ባለመስጠቱ ትችት ገጥሞታል፡፡

እ.አ.ኤ1960ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ደግሞ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ከቅርጽ ይልቅ ወደመጻፍ ሂደት ትኩረቱን የለወጠበት ጊዜ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት የአዕምሯዊያን የመማር ንድፈሃሳብ እየተጠናከረ የመጣበት በመሆኑ ተማሪዎች ጽሑፍ በሚያዋቅሩበት ጊዜ ለሚኖራቸው አእምሯዊ ሂደት አጽንዖት መስጠት እንዳለበት ግንዛቤ ሊገኝ ችሏል፡፡ ይህን ተከትሎ በወቅቱ በተደረጉ ምርምሮች (Flower & Hayes, 1981)መጻፍ የማቀድ፣ የማርቀቅና የመከለስ ደረጃዎችን የሚያልፍ ሂደታዊ ተግባር መሆኑ ግንዛቤ ተገኝቷል፡፡ በዚህም የተነሳ ከቅርጽ ትክክለኛነት ባሻገር ለሀሳብ ትባት፣ ፈጥሮ ለመጻፍና የተማሪዎቹን ሀሳብና እይታ ለማካተት የሚያስችል የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የበለጠ ትኩረት መስጠት ተችሏል፡፡ ክሂሉን የሚያስተምሩ መምህራን ሚናም ተማሪዎችን በማርቀቅ፣ በመከለስና በማረም ሂደት ድጋፍ ወደመስጠትና በምሪት ወደማሳየት ተቀይሯል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ሂደታዊ የመጻፍ ክሂል

ትምህርት አቀራረብ የመጻፍ ስራ የሚካሄድበትን ማህበረባህላዊ አውድ በመዘንጋቱ የተማሪዎችን የመጻፍ ዓላማዎችና የተግባቦት ፍላጎቶች አያማክልም በሚል ትችት ገጥሞታል፡፡

ከላይ በተገለጹት የለውጥ ሂደቶች ውስጥ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ በቴክስቱ ላይ ብቻ ሳይሆን በጸኃፊዎች ብሎም በአንባቢዎች ባህርያት ላይ ጭምር ማተኮር እንዳለበት የሚያሳዩ የማስተማር ስልቶች እንደሚስፈልጉ ማሳየት ችሏል (Hyland, 2009)፡፡ ይህን ተከትሎ እንደተነሳሽነት፣ ግለብቃት እምነት ያሉት የተማሪዎች ስሜታዊ ባህርያት ጭምር ከመጻፍ ክሂል ጋር ያላቸውን ትስስር መፈተሽ ጀምረዋል (Pajares, 2003 ዋቢ ያደረጓቸው Beach, 1989; Cherry, Faigley, Jolliffe, & Skinner, 1985)፡፡

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች መጻፍን ለመማር አሳላጭ ስለመሆናቸው የተለያዩ የመማር ንድፈሃሳቦች ያመላክታሉ፡፡ ለምሳሌ እንደChen, Hirumi and Zhang (2007) ገለጻ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን የመጠቀም ምክንያት መነሻው የአዕምሯዊ መማር ንድፈሃሳቦች ናቸው፡፡ በአዕምሯዊ መማር ንድፈሃሳቦች መሰረትም መማር መረጃን በማብላላት ሂደትና በዳራዊ እውቀት የሚወሰን ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች በመታገዝ የሚያውቁትን ሀሳብ ከአዲስ መረጃ ጋር ያስተሳስራሉ፤ በአዳዲስ አውዶች ውስጥ ይተገብራሉ፡፡ Ellis(2004)ን ጠቅሰው Yasin,Herdi,& Syarif (2014) እንደገለጹት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ተማሪዎች ስለሚጽፉት ጉዳይ ሀሳብ እንዲያመነጩ፣ከርእስ እንዳይወጡ፣ በዋናና በዝርዝር ሀሳቦች ላይ እንዲያተኩሩ፣ የተዘነጋ ሃሳብ ካለ እንዲያካትቱ ስለሚያግዛቸው የመጻፍ ችግራቸውን ለመቋቋምና ለመፍታት በማስቻል ተነሳሽነታቸውንና ብቃታቸውን ለማሻሻል ውጤታማ ዘዴ ነው፡፡

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ከተግባር ተኮር የማስተማሪያ ዘዴዎች ዉስጥ የሚካተቱ ሲሆኑ እይታዊ ወይም ምስላዊ (visual aid) አቀራረብ ያላቸው ናቸው:: ዘዴዎቹ በ1970ዎቹ መጨረሻና በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችና ለሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎች (TESOL) ማስተማሪያ ዘዴ ውስጥ የተካተቱና እስካሁን ድረስ በመተግበር ላይ ያሉ መሆናቸውን Cheng (2002) ገልጸዋል፡፡እነዚህን የሀሳብ

ማደራጃ ቢጋሮች ለመፃፍ ክሂል ማስተማሪያነት መጠቀም የሚያስችሉ የተለያዩ ጽንሰ ሃሳባዊ፣ ንድፈ ሃሳባዊና ምርምራዊ መሰረቶች አሏቸዉ፡፡

የAusebel (1968)ን ስራ ዋቢ አድርገው Mokhtar, Nawawi, & Zaini (2010) እንዳብራሩት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የአዕምሯዊ መማር ውህደት ወይም በአዲሱና በነባሩ ጉዳይ ላይ ስምምነት መፍጠር የሚለውን ንድፈሃሳብ (assimilation theory) መሰረት አድርጎ የተዋወቀ ነው፡፡ በተመሳሳይAusebel (1968)ን በመጥቀስ Chen, Hirumi & Zhang (2007) እንዳስረዱት እንደሌሎቹ የአዕምሯዊ ንድፈሀሳብ ዘርፎች ሁሉ የውህደት ንድፈሀሳብ መረጃ በአዕምሮ ውስጥ የሚደራጀው ከጥቅል ወደ ዝርዝር ተዋረዳዊ አሰዳደር ባለው መልክ እንደሆነ ይታመናል፡፡ መማርም መረጃዎች ስርዓታዊ በሆነ አደረጃጀት ሲቀርቡና በአዕምሮ ውስጥም በተሳሰረ ሁኔታ ሲደራጁ እንደሚሳለጥ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም Hall,& strongman (2008) የገለጹትን የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ተማሪዎች በሚጽፉበት ጊዜ አዳዲስ መረጃዎችን ከቀደመ እውቀታቸው ጋር እንዲያስተሳስሩና በአዳዲስ አውዶች ውስጥ ይህን የእውቀት ትስስር በተግባር እንዲጠቀሙበት ያግዛል የሚለውን ሃሳብ ያጠናክራል፡፡

Mayer (1979) በበኩላቸው Ausubel (1968) ን ዋቢ በማደረግ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን ጽንሰሃሳብ የውህደት-ቅበላ ከሚለው ንድፈሀሳብ (assimilation encoding theory) አንጻር ተርጉመው ለማሳየት ጥረት አድርገዋል፡፡ የዚህም መሰረት ሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የተሳካ አጠቃቀም በትውስታ ውስጥ የማዋሃድ አውድ በመኖርና እውቀትን በንቃት በመጠቀም ተጽዕኖ ስር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ከዚህም ሌላ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ከአዕምሮ-መር የመማር ንድፈሃሳቦች (brain-based learning theories) ጋር ትስስር እንዳለው የCaine (1991) ሀሳብ መነሻ በማድረግ Chen, Hirumi and Zhang (2007) ገልጸዋል፡፡ በአዕምሮ-መር የመማር ንድፈሃሳቦችም መሰረት ከመረጃ ይልቅ ትርጉም ጠቃሚ እንደሆነ ብሎም ንቁ የመረጃ ማብላላት (information processing) ከዳራዊ እውቀት ጋር ከፍተኛ ተዛምዶ እንዳላቸው ያመላክታል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች አዳዲስ መረጃዎችን ከዳራዊ እውቀታቸው ጋር እንዲያዛምዱ መምህራን በቅድሚያ

ከማዛመጃ ስልቶች ጋር ማስተዋወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችም ከማዛመጃ ስልቶቹ ውስጥ የሚመደቡ ናቸው፡፡

በአንድ ጊዜ በርካታ የስሜት ህዋሳቶችን በማስተባበር መማርን መከወን ላይ በሚያተኩረው በMayer (1997) አይነተብዙ ሚዲያ መማር አፍልቆታዊ ንድፈሃሳብ (generative theory of multimedia learning) መሰረት ደግሞ ትርጉምአዘል መማር የሚፈጠረው ተማሪዎች ከቀረበላቸው ግብዓት ጠቃሚ መረጃዎችን መርጠው፣ መረጃዎቹን ተያያዥነት ወዳለው አዕምሯዊ ውክልና ሲያደራጁና አዲስ የተፈጠረውን ሀሳብ ከባለፈዉ ሀሳብ ጋር ማዋሃድ ሲችሉ ነው፡፡ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችም ተማሪዎች ሀሳባቸውን በቃላትና በምስል አቀናጅተው የሚያፈልቁበትን እድል ስለሚፈጥሩ መማራቸው የተሳለጠ እንዲሆን ያግዛሉ፡፡ በተለይም በመጻፍ ክሂል መማር ውስጥ የተለያየ የአደረጃጀት ባህርይ ላላቸው ሀሳቦች የሚስማሙ ስዕላዊ የሀሳብ ማዋቀሪያዎችን ከቁልፍ ሀሳቦች ጋር አቀናጅተው ለማሳየት ስለሚያስችሉ የመጻፍ ሂደቱን ለማሳለጥ ወሳኝ ሚና ይኖራቸዋል፡፡

በPaivio (1986) የጥምርኮድ የመማር ንድፈሃሳብ (dual-coding theory) መሰረት ደግሞ እሳቦት ቃላዊና ኢቃላዊ በሚባሉ ሁለት የተለያዩ ግን የርስበርስ ትስስር ባላቸው ሥርዓቶች ይገለጻል፡፡ የመጻፍ ስራም ከፍተኛ የእሳቦት ችሎታን የሚጠይቅ ነው፡፡ ሀሳቦችን የመምረጥ፣ የማደራጀትና እንደየዝምድናቸው የማስተሳሰር ስራን ይጠይቃል፡፡ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችም እይታዊና ቃላዊ የመረጃ ማብለያ ስርዓቶችን በጥምረት የመተግበር እድል ስለሚሰጡ መረጃን የመምረጥ፣ በአዕምሯዊ ውክልና የማደራጀትና ከሌሎች ሀሳቦች ጋር የማዋሃድ አዕምሯዊ ሂደቶች ያሳልጣሉ፡፡ በተለይም የPaivio (1986) ጥምርኮድ የመማር ንድፈሃሳብ ቃላዊና ኢቃላዊ መረጃዎች ጎን በጎን የሚብላሉበት አጋጣሚ ሲፈጠር ሀሳብ የማፍለቅም ሆነ የማደራጀት ሂደት ላይ እገዛ እንዳለው ያመላክታል፡፡ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችም ቃላዊና ኢቃላዊ የሀሳብ ማስፈሪያ ስልቶችን አጣምረው መተግበር የሚያስችሉ በመሆናቸው መጻፍን ለማሳለጥ ሚናቸው ከፍ ያለ ይሆናል፡፡

Ausubel (1960, 1963)ን ጠቅሰው Griffin and Tulbert (1995) እንዳብራሩት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር በአነሳሱ የተዋቀረ ማጠቃለያ (structured overview) በሚል ስያሜ የተዋወቀ ነበር። በአዕምሯዊ ንድፈሃሳብ የተነሳውን መማርን ትርጉምአዘል በሆነ መንገድ መገንዘብ የሚል መርህ ወደተግባር ለመለወጥ ጥረት የተደረገበት መሆኑን ጭምር በማብራሪያቸው ጠቁመዋል።አዳዲስ ሀሳቦችን ለመማር ነባር እውቀት ወይም አዕምሯዊ መዋቅር ወሳኝ ተላውጦ መሆኑን ያስገነዝባል። ነባር ወይም ቀደምት መረጃዎች በግልጽና በጥንቃቄ ከተደራጁ የተማሪዎቹ አዲስ ሀሳብን የመማር ሂደት የተሳለጠ ይሆናል። የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችም የተማሪዎችን ነባር አዕምሯዊ አወቃቀርን ከመማሪያ ክፍል በሚገኙ ተግባራት የማጠናከሪያ መንገድ ነው።

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ጽንሰሃሳቦች ያላቸውን የርስበርስ ትስስር ወይም ግንኙነት ቅደምተከተል በማስያዝ እውቀትን ሊታይ በሚችል ውክልና የማስፈሪያ ስልቶችም እንደሆኑ Bromley, DeVitis and Modlo (1999)ን በመጥቀስ Curriculum Development Institute (2001) ጽፏል። ስለሆነም መሰረታዊ ተግባራቸውም ጽንሰሃሳቦቹ ያላቸውን አደረጃጀትና ዝምድን በግልጽ ሊያሳይ በሚችል ሁኔታ መረጃን ለማቅረብ ማስቻል ነው።

በBaxendell (2003) አገላለጽ መሰረት ደግሞ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ሀሳቦች ርስበርስ ያላቸውን ግንኙነት፣ ቅደምተከተል ወይም ተዋረዳዊ የሀሳበ ፍሰት የሚያሳይ ምስላዊ እሳቤ ነው። በመሆኑም ተማሪዎች ሀሳባቸውን ስዕላዊ በሆነ መንገድ ማደራጀት እንዲችሉ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ። በተመሳሳይ Miller (2011) እንደገለጹት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ተማሪዎች ሀሳቦቻቸውን ለማዋቀር የሚረዷቸውና የማሰብ ክሂሎቻቸውን በተሰናሰለ ሁኔታ ለማቅረብ ተግባር ላይ የሚያውሏቸው እይታዊ የሀሳብ መወከያዎች ናቸው። ቢጋሮቹ አዘውትረው ቁልፍ ቃላትና ሀረጋት በልዩ ልዩ ስዕሎች በማስተሳሰር የሚቀርቡ ስለሆኑ ተማሪዎቹ ከአረፍተነገር ወይም ከአንቀጽ ቅርጾች ይልቅ በትርጉም ላይ እንዲያተኩሩ የሚያግዙ መሆናቸውን ጭምር ጠቁመዋል።

ከዚህም ሌላ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር የቴክስት ጽንሰሃሳብ ምስላዊ ውክልና እንደሆነ ይታሰባል (Zaini, Mokhtar, & Nawawi, 2010)፡፡ ይህ ምስላዊ ውክልናም ተማሪዎች በሚያደራጇቸውና በሚያዋቅሯቸው ሀሳቦች ውስጥ የተዘነጉ መረጃዎችን ወይም የተረሱ የሀሳብ ቁርኝቶችን እንዲለዩ ስለሚያግዝና እይታዊ አቀራረብ ስለአለው ተማሪዎች ለመጻፍ ይነሳሳሉ፡፡

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን ለመጻፍ ክሂል ማስተማሪያነት መጠቀም በርካታ ሁነኛ ምክንያቶች አሉት። ከምክንያቶቹ አንዱ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ለፈጠራዊ አስተሳሰብ መዳበር አጋዥ መሳሪያዎች ናቸው። ቁልፍ ቃላትንና ጽንሰሃሳቦችን ብሎም በመካከላቸው ያሉትን ዝምድናዎች ስለሚያመላክቱ ተማሪዎች በጠቃሚ ሀሳቦች ላይ እንዲያተኩሩ ይረዷቸዋል። የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን መጠቀም መረጃ ማቀናበርን፣ ሀሳብ ማመንጨትን፣ ሀሳብ መገምገምን፣ መተንተንንና ጽብረቃን ስለሚያካትት የተማሪዎችን የሀሳብ ማደራጀትና የማሰብ ክሂሎችን የማሻሻል ሚና አላቸው (Curriculum Development Institute, 2001 ዋቢ ያደረጋቸው Ausubel, 1968; Bromley,et al. 1995; Dunston,1992; Vygotsky, 1962)፡፡

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች መረጃዎችን ለማደራጀትና ተዛምዷቸውን ለመረዳት መሰረታዊ መሳሪያዎች ናቸዉ፡፡ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የሰው ልጅ አዕምሮ መረጃዎችን ከሚያደራጅበትና ከሚያቀይበት የኔትወርክ ስርዓት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው በመሆኑ ተማሪዎች መረጃዎችን ከነተዛምዷቸው መረዳትና ማቆየት የሚያችል፣ በአዳዲስ መረጃዎችና በዳራዊ እውቀታቸው መካከል ያሉ ተመሳስሎዎችንና ልዩነቶች የመለየት እውቀታቸውን ያሻሽልላቸዋል። በተለይም ሰፋፊ መረጃዎችን ለአጠቃቀም ምቹ ወደሆኑ ክፍሎች ከፋፍለው ማየት እንዲችሉ ስለሚያግዟቸው በእያንዳንዱ ሃሳብ መካከል ያሉ ዝምድናዎችን በቀላሉ ለማብራራት እድል ይሰጣቸዋል (Curriculum Development Institute, 2001 ዋቢ ያደረጋቸው Ausubel, 1968; Bromley,et al. 1995; Dunston,1992; Vygotsky, 1962)፡፡

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች እውቀትንና መረዳትን ከአዕምሮ አውጥቶ ለማሳየት አማራጭ ሆነው ያገለግላሉ፡፡በሌላ አገላለጽ የማሰብን ውስጣዊ ሂደትን ውጫዊ ወይም በሚታይ ቅርጽ ለማቅረብ እገዛ ያደርጋሉ። ይህም የተማሪዎችን የእሳቦት ሂደቶች ለመቃኘትና ለመገምገም የሚያስችል

መንገድን ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም በጽንሰሃሳቦች መካከል ያሉ ዝምድናዎችን ለይተው የመግለጽና የማብራራት፣ሀሳባቸውን የማፍለቅና የማደራጀት ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ጠቀሜታቸው የጎላ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ግለመማርን (self-learning) ለማሳለጥ ፋይዳ ያላቸው መሆኑ ነው፡፡ በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን የሚገለገሉ ተማሪዎች በግል ጥናታቸውም ማስታወሻ ለማዘጋጀት፣ ሀሳብ ለማቅረብ፣ ሀሳብ ለመከለስ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ረቂቅ ንጽጽሮችን፣ ግምገማዎችንና ማጠቃለያዎችን እንዲያደርጉ ስለሚያግዙ በመጻፍ ክሂል ትምህርታቸው ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ እድል ይፈጥራሉ (Curriculum Development Institute, 2001 ዋቢ ያደረጋቸው Ausubel, 1968; Bromley,et al. 1995; Dunston,1992; Vygotsky, 1962)፡፡

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች እውቀትንና መረዳትን ከአዕምሮ አውጥቶ ለማሳየት አማራጭ ሆነው ያገለግላሉ፡፡በሌላ አገላለጽ የማሰብን ውስጣዊ ሂደትን ውጫዊ ወይም በሚታይ ቅርጽ ለማቅረብ እገዛ ያደርጋሉ፡፡ ይህም የተማሪዎችን የእሳቦት ሂደቶች ለመቃኘትና ለመገምገም የሚያስችል መንገድን ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም በሚጽፉበት ጊዜ በጽንሰሃሳቦች መካከል ያሉ ዝምድናዎችን ለይተው የመግለጽና የማብራራት፣ሀሳባቸውን የማፍለቅና የማደራጀት ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ጠቀሜታቸው የጎላ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ግለመማርን (self-learning) ለማሳለጥ ፋይዳ ያላቸው መሆኑ ነው፡፡ በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን የሚገለገሉ ተማሪዎች በግል ጥናታቸውም ማስታወሻ ለማዘጋጀት፣ ሀሳብ ለማቅረብ፣ ሀሳብ ለመከለስ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ረቂቅ ንጽጽሮችን፣ ግምገማዎችንና ማጠቃለያዎችን እንዲያደርጉ ስለሚያግዙ የመማራቸው ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ እድል ይፈጥራሉ (Curriculum Development Institute, 2001 ዋቢ ያደረጋቸው Ausubel, 1968; Bromley,et al. 1995; Dunston,1992; Vygotsky, 1962)፡፡

ከDrapeau (1998) በተወሰደ መረጃ Curriculum Development Institute (2001) የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ተማሪዎች የአዕምሮ ጨመቃ፣ አዳዲስ ሀሳቦች ማመንጨት፣ ሀሳቦችን በየዘርፋቸው ማጠቃለል፣ ሀሳቦችን ቅደምተከተል ማስያዝ፣ የሀሳቦችን ምክንያትና ውጤት መተንተን እንዲችሉ በማገዝ የማሰብ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ያደርጋሉ፡፡የሀሳብ ማደራጃ

ቢጋሮች ዝቅተኛ የመጻፍ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች የሚገጥሟቸውን መሰናክሎች በማቃለል የማቀድ፣ የማዋቀር፣ የቃላት ምርጫና የግጥምጥምነት ስራዎቻቸውን ለማሻሻል አጋዦች መሆናቸውን Bishop (2013) ጠቁመዋል፡፡ ከዚህም ሌላ ከሚፈለገው ደረጃ በታች የመጻፍ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ለመረጃዎች ስሜት እንዲኖቸው ብሎም ለመጻፍ በተነሱባቸው ርዕሰጉዳዮች ዙሪያ ላይ ብቻ ጸንተው እንዲቆዩ የሚረዱ ናቸው(Ching & Chee 2010)፡፡

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች መማርን በልዩ ልዩ ሁኔታ እንደሚያሳልጡ የሚያመላክቱ የተለያዩ ጽንሰሃሳባዊ፣ ንድፈሃሳባዊና ምርምራዊ መሰረቶች አሉት፡፡ በመሆኑም የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል መቻል አለመቻላቸውንና ክሂሉን ለማስተማር ያላቸውን አማራጭነት በማሰብ አጥኚዋ ስልቶቹ የተማሪዎቹን ችግሮች ለማቃለል ሚና ይኖራቸው እንደሆነ ለመፈተሽ ተነሳስታለች፡፡ በተጨማሪም ተማራማሪዋ እነዚህን የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች በመጠቀም መጻፍን መማር ተማሪዎቹ ለመጻፍ ባላቸው ተነሳሽነት ላይ ተጽዕኖ ያሳድሩ እንደሆነ ለማወቅ ፈልጋለች፡፡

## 1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር

የመፃፍ ክሂል በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት የቋንቋ ክሂል ነው፡፡ አንድ ግለሰብ በፅሁፍ አማካኝነት ሀሳቡን መግለፅ፣ አላማውን ማሳካት ይችላል፡፡ ስለሆነም ይህንን ወሳኝ የሆነ ክሂል ከታችኛው ክሂል ጀምሮ በአግባቡ ማስተማር ይገባል፡፡ ነገር ግን በተግባር እየተሰራ ያለው ከዚህ በተለየና ለክሂሉ አነስተኛ ትኩረት በሰጠ መንገድ መሆኑን Prtatama (2014/2015) ገልፀዋል፡፡

መጻፍ የህይወት ዘመን ክሂል ነው፡፡ በትምህርትቤት የተለያዩ የትምህርት አይነቶችን ለመማርም ሆነ ያወቁትን ለማንጸባረቅ ወሳኝ ከሆኑ ክሂሎች አንዱ ነው፡፡ እንደNik, Hamzah & Rafidee (2010) አገላለጽ መጻፍ አለም የሚመረመርበት ወይም የሚዳሰስበት፣ ተመክሮ ወይም ልምድ የሚተላለፍበት መሳሪያ ነው፡፡ ተማሪዎች ይህን ወሳኝ ክሂል በአግባቡ ካልተማሩ

በትምህርታቸው፣ በስራም ሆነ በሌሎች የህይወት ውጣውረድ ውስጥ ክሂሉን በሚፈለገው ደረጃ መጠቀም አይችሉም፡፡ በአግባቡ መጻፍ የማይችሉ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርትም ሆነ በአጠቃላይ የትምህርት ውጤታቸው ውስጥ ለልዩ ልዩ ችግሮች የተጋለጡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ መጻፍን በሚጠይቁ የትምህርት ምዘናዎች ውስጥ ሀሳባቸውን በጽሁፍ አሟልተውና አሳክተው ስለማይገልጹ ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘግባሉ፡፡ በዚህም የተነሳ በትምህርታቸው ይወድቃሉ፤ ትምህርታቸውን በሚጠበቀው ጊዜ ማጠናቀቅ እንደሚቸገሩ Bishop (2013) ገልጸዋል ፡፡

በመሆኑም ተማሪዎች ጥሩ የመፃፍ ችሎታ ሳይኖራቸውና ከተለያዩ የመፃፍ ስልቶች ጋር ሳይተዋወቁ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቅቃሉ፡፡ አብዛኛዎቹ ተማሪዎችም የመፃፍ ክሂልን በአግባቡ ስለማይማሩ የመፃፍ ችሎታቸው ደካማ ነው፡፡ የዳበረ የመፃፍ ችሎታም ስለሌላቸው የተዋጣለትና በአግባቡ የተደራጀ ላሉበት ደረጃ የሚመጥን ፅሁፍ የማዘጋጀት አቅማቸው አናሳ ነው፡፡ ይሁን እንጂ መፃፍ ከክሂልነቱ ባሻገር የእውቀት ማግኛ መንገድ ነው፡፡ ስለሆነም በትምህርት ውጤታቸውም ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡ በስራ በሚሰማሩበት ጊዜም በመፃፍ ተግባራት እንዳይሳተፉ ያደርጋቸዋል (ባዬ፣2000)፡፡

በብዙ መልኩ ሲታይ በተሻለ ደረጃ መፃፍ በየትኛውም ቦታ እጅግ ተፈላጊ ችሎታ እየሆነ ከመምጣቱ አኳያ በሁሉም የክፍል ደረጃ የሚሰጥ ትምህርት አንዱ ሚና የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ማጎልበት ነው፡፡ በተለይ የተማሪዎች የክፍል ደረጃ እየጨመረ ሲመጣ የመጻፍ ክሂል ሚናው እየጎላ ይሄዳል (Brown, 2011; Hall & Strangman, 2008)፡፡ ይሁን እንጂ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በሚገባው ደረጃ አገጣጥመው የተሻለ ጽሁፍ ማዋቀር ይቅርና መሰረታዊ የሚባሉ የጽህፈት ስርዓቶችን አሟልተው የመጻፍ ችግር ይስተዋልባቸዋል፡፡

ከትምህርትቤት ውጭ በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች ጭምር የመጻፍ ችሎታ አስፈላጊነቱ እየጨመረ መጥቷል፡፡ እንደBishop (2013) ገለጻ ተማሪዎች የህይወት ገጠመኛቸውን ለማንጸባረቅ መጻፍ ይኖርባቸዋል፤ የህይወት ገጠመኛቸውን በጽሁፍ ማንጸባረቃቸውም ለአዕምሯዊ እድገታቸው ብቻ ሳይሆን ለስነልቦናቸው መዳበር ወሳኝ ሚና አለው፡፡ በስራ ላይም ቢሆን ከሚያስፈልጉት ወሳኝ የተግባቦት ክሂሎች አንዱ የተሳለጠ የመጻፍ ክሂል ችሎታ ነው፡፡

በትምህርት፣ በስራና በማህበራዊ አውዶች ውስጥ መጻፍ አስፈላጊ ክሂል ቢሆንም የመማር ሂደቱ አስቸጋሪ ተግባር ነው፡፡ ለተማሪዎች ቀርቶ ብዙ መምህራን ክሂሉን በአግባቡ ባለመማራቸውና የመጻፍ ልምዳቸውን በስራ ስለማያዳብሩ መጻፍን ለማስተማር ባላቸው ብቃት እንደማይተማመኑ Shin (2003)ን ዋቢ አድርገው Marashi and Massoodi-Hematabadi (2011) ገልጸዋል፡፡ የመጻፍ ስራን አስቸጋሪ የሚያደርገው ሀሳቦችን ማፍለቅና ማዋቀር ብቻ ሳይሆን ሀሳቦችን ተነባቢ ወደሆነ ቴክስት የመለወጥ ሂደት ጭምር ነው፡፡ እንዲያውም የብዙ ሰዎች የመጻፍ ችግር መጻፍን መጀመር ላይ ወይም ከምን ልነሳ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡

መጻፍ ለተለያዩ አላማዎች ሀሳብን የመግለጽና የማመንጨት ችሎታን በመጠቀም በጽሁፍ መግባባት ነው (Richard, 2003)፡፡ በርካታ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ሀሳባቸውን የማመንጨት፣ የማደራጀት ብሎም በአግባቡ የተደረጀ ጽሁፍ የመጻፍ ችግር እንዳለባቸው ይገልጻሉ፡፡ እንደUnzeta (2009) ገለጻም ብዙዎቹ ተማሪዎች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመከለስ፣ በአርትዖት የመጻፍ ሂደት ደረጃዎች ሁሉ በርካታ ችግሮች ይገጥሟቸዋል፡፡ የችግሩን ስፋት የሚያጠናክረው “ብዙጊዜ እንደሚስተዋለው በመጻፍ ስራ ተማሪዎች ሶስት ችግሮች አሉባቸው፤ ክብደትና ቅለታቸው እንደተማሪው ሁኔታ የሚለያይ ቢሆንም የሀሳብ እጥረት ወይም የሚጽፉት ማጣት፣ የቋንቋ ችሎታ ማነስ እና ሀሳብን በአግባቡ ማደራጀት አለመቻል ተጠቃሽ ችግሮች ናቸው፡፡” በማለት ማረው (1996፣ v¡¡) ያቀረቡት ሀሳብ ነው፡፡ በተለይም ሀሳብ በማፍለቅ፣በማቀድና በማደራጀት ደረጃዎች የሚገጥሟቸውን ችግሮች ካልፈቱ ወደሌሎቹ የመጻፍ ሂደቶች ተሸጋግረው የመጻፍ ስራን ለመስራት እንደሚቸገሩ የዚህ ጥናት አቅራቢም በስራ ልምዷ ታዝባለች፡፡

በሁሉም አቅጣጫ ለተማሪዎቹ ዝቅተኛ የመጻፍ ችሎታ ከሚጠቀሱ ምክንያቶች አብዛኛዎቹ ክሂሉን ለማስተማር እያገለገሉ ያሉት ዘዴዎች ባላቸው አዋጭነት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ብዙ ጊዜ በስራ ላይ የሚውሉት ዘዴዎች መምህራን ርዕስ ያቀርባሉ፤ ተማሪዎች ይጽፋሉ፤ መምህራን የተማሪዎቹን ጽሁፎች ይገመግማሉ፤ ግብረመልስ ይሰጣሉ፡፡ እንዲህ አይነቱ ዘወትራዊ አቀራረብ በአጥኚዋ እይታ ውጤታማ ያልሆነ ብሎም ተነሳሽነትን የሚያዳክም፣ ለመጻፍ አሉታዊ ዝንባሌ እንዲኖር የሚያደርግ ነው፡፡ Chohan (2011) እንደገለጹትም በመጻፍ ክሂል ማስተማር ትግበራ ውስጥ ብዙ መምህራንን የሚፈትናቸው ችግር ተማሪዎቻቸው ለመጻፍ ስራ ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆን ጭምር ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በመጻፍ

ውጤታማ፣ ተነሳሽና አወንታዊ ዝንባሌ እንዲኖራቸው የሚያግዝ አማራጭ የመጻፍ ክሂል አቀራረብ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር ያላቸውን ሚና የፈተሹ ጥናቶችም የሚቃረኑ ውጤቶችን ማሳየታቸው ተጨማሪ ጥናት ለማድረግ የሚያነሳሳ ችግር ነው፡፡ ለምሳሌ የተወሰኑት ጥናቶች (Cronin, Barkley, & Sinatra ,1992; Delarose ,2011; Meera & Aiswary, 2014; Miller, 2011; Sharrock, 2008) የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን የተማሪዎችን የመጻፍ ውጤት እንዳሻሻሉ አመላክተዋል፡፡ ሌሎች ጥናቶች ደግሞ (Blair, Ormsbee, & Brandies, 2002; Marashi, & Massoodi-Hematabadi, 2011) በቢጋሮች የተደገፈ ትምህርት የተማሪዎችን የመጻፍ ውጤት አለማሻሻላቸውን አሳይተዋል፡፡ እንዲህ አይነት የጥናቶች ውጤት መጣረስ መኖሩም በጉዳዩ ዙሪያ ተጨማሪ ጥናቶችን ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ያመላክታል፡፡

እንደመጻፍ ግለብቃት እምነት፣ የመጻፍ ተግባራትን በራስ መምራት ባሉት የመጻፍ ተነሳሽነት ዘርፎችና በመጻፍ ችሎታ መካከል ዝምድና መኖሩን የMcCarthy et al. (1985)፣ Schunk & Zimmerman (1994)፣ የZimmerman & Martinez-Pons (1990) ያሳዩ ጥናቶች መኖራቸውን Pajares (1996) አስረድተዋል፡፡ እነዚህ ጥናቶች በመጻፍ ተነሳሽነትና በመጻፍ ችሎታ መካከል ትስስር መኖሩን ቢጠቁሙም ተዛምዷዊ ንድፍን ተከትለው የተሰሩ በመሆናቸው በተላውጦዎቹ መካከል ስለሚኖረው የምክንያትና ውጤት ግንኙነት የተሟላ መረጃ ሊሰጡ አይችሉም፡፡ ስለዚህም ፍትነታዊ የምርምር ንድፍን መሰረት አድርጎ በሚሰራ ጥናት ተላውጦዎቹ ያላቸውን ግንኙነት መፈተሽ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በጥናቶቹ ከታየው የውጤት ተቃርኖ ችግር በተጨማሪም በአጠናን ዘዴዎቻቸው ላይ ክፍተቶች መኖራቸው ጉዳዩ ተጨማሪ ጥናት እንዲደረግበት የሚያነሳሳ ችግር ነው፡፡ አብዛኛዎቹ በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ማስተማር ላይ የተሰሩት ጥናቶች እንደመጻፍ ተነሳሽነት ባለ ስሜታዊ ባህርያት ላይ የሚያመጣውን ለውጥ አካትተው የፈተሹ አይደሉም፡፡ በመጻፍ ክሂልና በተማሪዎች የተነሳሽነት ባህርያት መካከል የተሰሩት ጥናቶችም

(Boscolo, Favero & Borghetto, 2007; Boscolo, 2007;Pajares, 2003) ቢሆኑ የተላውጦዎቹን ተንባይ ተተንባይነት በተዛምዶ የምርምር ንድፎች ከመፈተሽ አልፈው ያላቸውን የምክንያትና ውጤት ትስስር የለኩ አይደሉም፡፡ እንደBishop (2013) እና Blair, Ormsbee, & Brandes (2002)ያሉት ጥናቶች ደግሞ የመጻፍ ክሂል እክል (disabled) ባለባቸው የተለዩ ተማሪዎች ላይ ብቻ የተካሄዱ በመሆናቸው መደበኛ ባህርይ ላላቸው ተማሪዎች የሚሰሩ አይሆኑም፡፡ ከዚህም ሌላ አብዛኛዎቹ ጥናቶች በሁለተኛ ቋንቋና በውጭ ቋንቋ የማስተማር አውድ ውስጥ የተሰሩ በመሆናቸው በአፍመፍቻ ቋንቋ አውድ ውስጥ ስለሚማሩ ተማሪዎች የተሟላ መረጃ የሚሰጡ አይደሉም፡፡ በመጨረሻም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የመጻፍ ክሂልን ከማጎልበት አኳያ ያላቸውን ሚና የፈተሸ ጥናት አጥኝዋ ካነበበቻቸው ምንጮች ውስጥ አልተገኘም፤ ይህም እንደአንድ የጥናት መነሻ ሆኗታል፡፡

እንደNik, Hamzah & Rafidee (2010) መጻፍ አስቸጋሪና ውስብስብ ክሂል ነው፡፡ በተለይ ደግሞ የመጻፍ ክሂላቸው ገና በጅምር ላይ የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ተማሪዎች ለደረጃው በሚጠበቅባቸው መጠን ሀሳባቸውን በጽሁፍ አፍልቀው ከማቅረብ አኳያ መሰረታዊ ችግሮች እንዳሉባቸው በደረጃው የሚያስተምሩ የቋንቋ መምህራን ሲናገሩ ይሰማል፤ የዚህ ጥናት አቅራቢም በስራ ተመክሯዋ በርካታ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ሀሳባቸውን በቃል የመግለጽ ብቃታቸውን ያክል በጽሁፍ በሚገልጹበት ጊዜ ሃሳበ የማፍለቅና የማደራጀት ችሎታቸው አነስተኛ በመሆኑ በደንብ የተቀነባባረ ጽሁፍ አለመጻፋቸውን ተመልክታለች፡፡ ከቋንቋ ትምህርት ውጭ ያሉት መምህራንም ቢሆኑ ኢ-መደበኛ በሆነ ውይይት ላይ ተማሪዎች በየትምህርት አይነቶቹ መጻፍን ለሚጠይቁ ተግባራት የሚፈለግባቸውን ያህል ችሎታ እንደሌላቸው ይናገራሉ፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ነባራዊ ችግሮችና በተሰሩ ምርምሮች ዙሪያ የታዩ ክፍተቶች ይህን ጥናት ለማካሄድ አጥኝዋን አነሳስተዋታል፡፡ ስለዚህም የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የተማሪዎችን የመጻፍ ስራ በማሳለጥ በመጻፍ ችሎታቸውና በመጻፍ ተነሳሽነታቸው ላይ የሚኖራቸውን ሚና በጥናት መፈተሽ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተዋለች፡፡ በመሆኑም በአማርኛ ቋንቋ መማር አውድ

ውስጥ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን መሰረት ያደረገ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት ለማሻሻል የሚኖውን ሚና መመርመር የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት ሆኗል፡፡

ጥናቱ ለሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፡-

1. በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የመጻፍ ክሂልን መማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ያሻሽላል? የተጽዕኖ ደረጃውስ ምን ያህል ነው?
2. በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የተደገፈ የመጻፍ ክሂል ትምህርት የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ያጎለብታል? የተጽዕኖ ደረጃውስ ምን ያህል ነው?

## 1.3 የጥናቱ አላማ

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ታግዞ መጻፍን መማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል የሚኖረውን ሚና መፈተሽ የዚህ ጥናት ዋና አላማ ነው፡፡ በዚህ ዋና አላማ ስርም የሚከተሉት ንኡስ አላማዎች አሉ፡፡

1. በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የተደገፈ የመጻፍ ክሂል ትምህርት የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር ያለውን ሚና መመርመር
2. በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የታገዘ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ተማሪዎች ለመጻፍ ስራ ያላቸውን ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለውን ሚና መፈተሽ

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

በዚህ ጥናት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች መጻፍን መማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ውጤትና የመጻፍ ተነሳሽነት የሚያሻሽል ሆኖ ከተገኘ፣ ግኝቱ የሚከተሉት ሥነትምህርታዊና ምርምራዊ ፋይዳዎች ሊኖሩት ይችላል፡፡

1.ሥነትምህርታዊ ፋይዳው ለተማሪዎች የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን እንዴት በመጻፍ ክዋኔ ሂደታቸው በመጠቀም የመጻፍ ችሎታቸውንና ተነሳሽነታቸውን ሊያሻሽሉ እንደሚችሉ

የሚያሳይ ትምህርት እንዲያገኙ ያግዛል፡፡ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ለመጻፍ ችሎታ መጎበልት ያላቸው ፋይዳ በመገንዘብ ተማሪዎቻቸው በመጻፍ ክዋኔ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን እንዴት መከተል እንዳለባቸው፣ ሀሳባቸውን አፍልቀው እንዴት በጽሁፍ ማደራጀት እንደሚችሉ ለማስተማር የሚያስችል ግንዛቤ ያስገኛል፡፡ ጥናቱ በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ውስጥ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን በመጠቀም የሀሰቦችን ተዋረዳዊ አደረጃጀት እንዴት ጠብቀው ማቅረብ እንደሚችሉ ለተማሪዎች ለማስተማር የሚረዳ ግንዛቤም ያስገኛል፡፡

2.ለአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተትምህርት ባለሙያዎችና የመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን እንደአንድ የመጻፍ ተግባራት ማቅረቢያ መንገድ ሊጠቀሙ ስለሚችሉበት ሁኔታ ፍንጭ ይሰጣል፡፡

3.ምርምራዊ ፋይዳው ደግሞ ሌሎች ተመራማሪዎች በዚህ ጥናት ያልተካተቱ ሌሎች የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች በመጻፍ ችሎታ ላይ የሚኖራቸውን ሚና እንዲፈትሹ መነሻ ይሆናል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ የተካሄደው በአማራ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን በኤፍራታና ግድም ወረዳ በአጣዬ ከተማ በሚገኘው የአጣዬ የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ነው፡፡ ትምህርትቤቱ የተመረጠበት የአጥኝዋ የስራ ቦታ በመሆኑ ከሌሎቹ ትምህርትቤቶች በተሻለ መልኩ አስፈላጊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አመቺ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ በትምህርትቤቱም በ2010 ዓ.ም በዘጠነኛ ክፍል ተመዝግበው በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ተከናውኗል፡፡ የክፍል ደረጃው የተመረጠበት ምክንያት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለሀገር አቀፍ ፈተና የሚዘጋጁ በመሆናቸው፣ የመሰናዶ የክፍል ደረጃ ተማሪዎችም ቢሆኑ አማርኛ ትምህርት ከመሰናዶ ወደ ከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና ላይ ባለመካተቱ ሶስቱም የክፍል ደረጃዎች ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው የሚሰጡትን ትምህርትና ልዩ ልዩ ተግባራት አይከታተሉም በሚል እሳቤ ነው፡፡

ጥናቱ በአንድ በኩል የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ከማዳበር አኳያ ሊኖራቸው የሚችለውን ሚና ብቻ የፈተሸ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የመጻፍ ተነሳሽነትን ከማጎልበት አንጻር ሊኖራቸው የሚችለውን ተጽዕኖ ብቻ የፈተሸ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በሁለቱ ጥገኛ ተላውጦች (በመጻፍ ችሎታና በመጻፍ ተነሳሽነት) ላይ በየተናጠል ያለውን ተጽዕኖ እንጂ በጥምረት የሚያስከትለውን ተጽዕኖ አይፈትሽም፡፡ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን በተመለከተም አይነታቸው በርካታ ናቸው፡፡ በዚህ ጥናትም የተተኮረባቸው የቅደምተከተላዊ፣የዋናና ዝርዝር ሀሳቦች ማደራጃ፣ ምክንያትና ውጤት፣ አወዳዳሪና አነጻጻሪ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ብቻ ናቸው፡፡ ጥናቱ በእነዚህ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የተወሰነበት አንዱ ምክንያት በደረጃው የሚሰጠው ትምህርት በአብዛኛው ትኩረት የሚያደርግባቸው መረጃ ሰጭ ጽሁፎች በመሆናቸው የተነሳ ነው (እንድሪስ፣ 2009 ዋቢ ያደረጋቸው Piccolo, 1987; Sharp, 2004; Wong & Au, 1985)፡፡ ሌላው ምክንያት ጥናቱን በሚፈለገው የጊዜ ወሰን ለማጠናቀቅ በእነዚህ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ላይ መወሰን ግድ ሆኗል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ውስንነት

ጥናቱ  በአንድ ትምህርትቤት በአንድ ክፍል ደረጃ በሁለት ምድብ (ሴክሽን) የተደረገ መሆኑና ሁሉም የሃሳብ ማደራጃ ቢጋሮች በጥናቱ ውስጥ አለመካተታቸው አንጻራዊ የሆነ ውስንነት ሊታይበት ይችላል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የጊዜ፣የጉልበትና የገንዘብ ውስንነት ነው፡፡

## 1.7. የቁልፍ ቃላት ብያኔ

የዚህ ጥናት ቁልፍ ቃላት የሃሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ፣ቅደም ተከተላዊ የሃሳብ ማደራጃ ቢጋር ዋናና ዝርዝር የሃሳብ ማደራጃ ቢጋር፣ ምክንያትና ውጤት የሃሳብ ማደራጃ ቢጋር፣ አወዳዳሪና አነጻጻሪ የሃሳብ ማደራጃ ቢጋር፣የመጻፍ ተነሳሽነትና የመጻፍ ችሎታ ናቸው፡፡ብያኔያቸውም እንደሚከተለው ነው፡፡

1. የሃሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ፦ሀሳቦች ርስበርስ ያላቸውን ግንኙነት ምስላዊ አደረጃጀቶችን በመጠቀም ቅደምተከተላዊ ወይም ተዋረዳዊ የሃሳብ ፍሰት የሚያሳይ ምስላዊ (እይታዊ) የሃሳብ መወከያ ናቸው ፡፡

2. ቅደም ተከተላዊ የሃሳብ ማደራጃ ቢጋር፦ መረጃዎች ወይም ሁነቶች በሚከሰቱባቸው ቅደምተከተሎች አንጻር ሀሳቦችን ለማዋቀር የሚያስችል የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር አይነት ነው፡፡
3. የዋናና ዝርዝር ሀሳቦች ማደራጃ ቢጋር፦ አንድን ቁልፍ ርዕሰ ጉዳይ በአብይነትና በንኡስነት አማክሎ የሚፈልቅና የመረጃዎችን ትስስር የሚያሳይ ነው፡፡
4. ምክንያትና ውጤት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር፦ ሁነቶች ወይም ነገሮች የተከሰቱበትን ሰበብና ያስከተሉትን ውጤት በትስስር በማቅረብ ሀሳብ የሚደራጅበት የሀሳብ አወቃቀር ዓይነት ነው፡፡
5. አወዳዳሪና አነጻጻሪ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር፦ ሀሳቦች ወይም ነገሮች ባሏቸው መሰረታዊ ገጽታዎች ጥራት ወይም ባህርያት አኳያ እያመዛዘኑ ለማወዳደርና ለማነጻጸር ወይም አንድነትና ልዩነታቸውን ለማተት በስራ ላይ የሚውል ስልት ነው፡፡
6. የመጻፍ ችሎታ፦ በፈተና የሚረጋገጥ ሲሆን ተማሪዎች በምክንያትና ውጤት፤ በዋናና ዝርዝር፣ በማውዳደርና በማነጻጸርና በቅደም ተከተል ልዩልዩ ሃሳቦችን በማፍለቅና በማደራጀት አብራረተውና አሰፋፍተው ወጥ የሆነ መልእክት በጽሁፍ ማስተላለፍን ያመለክታል፡፡
7. የመጻፍ ተነሳሽነት፦ በጽሁፍ መጠይቅ የሚለካ፣ ተማሪዎች ለመጻፍ የሚኖራቸው ዝግጁነት፣ ጉጉት፣ ፍላጎትና መነቃቃት ያመለክታል ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፤ የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ

## 2.1 የሃሳብ ማደራጃ ቢጋሮችና የመጻፍ ችሎታ

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የአንድን ጽሁፍ ጽንሰሃሳባዊ አደረጃጀት ሊወክሉ የሚችሉ መሪ ሀሳቦች በምስል የሚቀርቡባቸው ናቸው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህም የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን በመጻፍ ክሂል ውስጥ ማካተት እየተለመደ መጥቷል፡፡ ለዚህም አንዱ ምክንያት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ተማሪዎች ተጨባጭ የመረጃዎች የተደራጀ አወቃቀር እንዲፈጥሩ ብሎም ከተነጣጠሉ ሀሳቦች ይልቅ ቁልፍ በሆኑና ጽንሰሃሳባዊ ተዛምዶዎች ባሏቸው ሀሳቦች ላይ እንዲያተኩሩ እገዛ ማድረጋቸው ነው (Delrose, 2011)፡፡ ሌላው ምክንያት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች መረዳትን፣ ማዋቀርንና ትርጉምአዘል መማርን የሚያሳልጡ በመሆናቸውም የተማሪዎችን ድካም በመቀነስ ውስብስብ የሆነውን የመጻፍ ተግባር በቀላሉ ስራቸውን የማከናወን እድል መፍጠራቸው ነው፡፡ ተማሪዎች ሲጽፉ ሀሳባቸውን እንዲያደራጁና የአስተሳሰብ፣ የፈጠራ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ መርዳታቸውም ተመራጭ የሚያደርጋቸው ተጨማሪ ምክንያት ሆኖ ይነሳል (Tracey, 2006)፡፡

ከዚህም ሌላ ተማሪዎች አንድን ጽሁፍ ሲጽፉ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች በአዕምሮ ጨመቃ (brainstorming) ፣ በማዋቀር (structuring) እና በዳግም ማዋቀር (restructuring) ደረጃ ተግባራዊ በማድረግ መጻፍ ይችላሉ (Harrington, Holik, & Hurt, 1998; Parker,2012)፡፡ ይኸውም ቅድመጽህፈት ደረጃ ላይ በሚተገበሩት የአዕምሮ ጨመቃ ስለሚጽፉበት ርዕስጉዳይ በቂ መረጃና ሀሳብ ለማፈላለግ የሚያስታውሷቸውን ሀሳቦች እያሰላሰሉ ከአዕምሯቸው እያፈለቁ በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ዙሪያ ይጽፋሉ፡፡ በማዋቀር ደረጃ ደግሞ ከአዕምሯቸው ያፈለቋቸውን ሀሳቦች እንዳላቸው ተዛምዶና ግንኙነት እየለዩ በፈርጅ በፈርጁ ለማዋገን የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹ በስልትነት ይጠቅማሉ፡፡ በዳግም ማዋቀር ደረጃም ቢሆን ተማሪዎች ያዘጋጁትን የጽሁፍ ረቂቅ በመከለስ ሀሳቦች በተገቢ ቅደምተከተላቸውና ዝምድናቸው መደራጀታቸውን ለመፈተሽ፣ ያልተስፋፉ ሃሳቦች ካሉ ለማስፋፈት፣ ተዘንግተው የታለፉ ሀሳቦች ካሉ ለማካተት የማደራጃ ቢጋሮቹ በአጋዥነት ያገለግላሉ፡፡

በተጨማሪም የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ተማሪዎች ከሚያውቁት ተነስተው ዋና ሀሳቦችን ለመንደፍ፣ ለማደራጀትና ቅደምተከተል ለማስያዝ የሚስችሉ መሳሪያዎች ናቸው (Mohammadia, Moenikiab, & Zahed-Babelanc, 2010)፡፡ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ተማሪዎች እውቀትን ለማሸጋገርና በአዲስ ሁነት ውስጥ በፈጠራ ለመተግበር እንዲያግዟቸው የሚያስችሉ፣ የሚያውቋቸውን ስያሜዎችና ጽንሰሃሳቦች በመጠቀም አዲስና ነባር መረጃዎችን በማዛመድ የሚጽፉበትን አጋጣሚም የሚፈጥሩ ናቸው፡፡ ይህ ሂደትም አዳዲስ መረጃዎችን በረጅም ጊዜ ትውስታቸው ውስጥ ለማቆየት ከማስቻሉም በላይ ሀሳቦች ያላቸውን ተዛምዶ ባልተወሳሰበ ሁኔታ እንዲያቀርቡ ያግዛቸዋል፡፡

ከዚህም በላይ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የመጻፍ ክሂልን ውጤታማ የማስተማሪያ መሳሪያዎች መሆናቸውን ለመፈተሽ የተሰሩ ምርምሮች ክሂሉን በተሻለ ደረጃ የማጎልበት ሚና እንዳላቸው አመላክተዋል፡፡ ለምሳሌ Cronin, Barkley, & Sinatra (1992) ለአራት ተከታታይ አመታት ባደረጉት ጥናት ደረጃዊ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋርን ተጠቅመው በተማሪዎች የመጻፍና የማንበብ ችሎታ ላይ ያለውን ተጽዕኖ ፈትሸዋል፡፡ የተማሪዎችን የመጻፍ ተግባራትን መረዳት፣ የሀሳብ ደረጃዎችን ለይቶ ማዋቀር፣ የአረፍተነገር አደረጃጀት፣ የቃላት ምርጫና ቋንቋ አጠቃቀም እና ስርዓተጽህፈት ለመገምገም በሚያስችሉ የማመሳከሪያ ቅጾች ተጠቅመው ባደረጓቸው ግምገማዎች በመጻፍ ችሎታቸው መሻሻል እንዳሳዩ አመላክተዋል፡፡ ቢጋሮቹ ተማሪዎች ረቂቅ ሀሳቦችን አጉልተው ለማሳየት፣ የመጻፍ ተግባራትን ወደተመጠኑ ትናንሽ ክፍሎች ከፋፍሎ ለመከወንና የመጻፍ ለውጣቸውን ለመቆጣጠር እንደሚረዱ Unzueta ( 2009) በጥናታቸው አሳይተዋል፡፡

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ተማሪዎች በመጻፍ ሂደት የሚገጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል እንደሚያግዙ ጭምር ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች በመጻፍ ሂደት ውስጥ ሀሳቦች ያላቸውን የጎንዮሽም ሆነ ተዋረዳዊ ዝምድናዎች እያስላሰሉ ለማዋቀር እንደሚያግዟቸው ብሎም ሀሳቦቹን ርስበርስ ለማነጻጸር እድል እንደሚፈጥሩላቸው የKatayama, Robinson, Kiewra, Dubois, & Jonassen (2001) ጥናት በማጣቀስ Lee & Tan (2010) አስረድተዋል፡፡ ከዚህም ሌላ Mokhtar, Nawawi, & Zaini (2010) ዋቢ ባደረጉት የClark (n.d) ተከታታይ ጥናት ሀሳቦችን እንደየተዛምዷቸው የማደራጀት ችግር ያለባቸው ተማሪዎችም ሆኑ

የሚጽፉበትን ርዕሰ ጉዳይ የመረዳት፣ ሀሳብ የማፍለቅና በሀሳቦች መካከል ያሉ ዝምድናዎችን ለመፍጠር ድክመት የሚታይባቸው ተማሪዎች በተለያዩ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ታግዘው ሲጽፉ ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንደቻሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተለይ Pizzo and Sinatra (1992)ን ዋቢ በማድረግ Sharrock (2008) እንዳብራሩት የብዙዎቹ ተማሪዎች ችግር ዝምድናቸውን የጠበቁ ሀሳቦች ያሉት ጽሁፍ ማዋቀር በመሆኑ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ይህን ችግር የመፍቻ መሳሪያዎች ናቸው፡፡

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ተማሪዎች በሚጽፏቸው ጽሁፎች ስፋትም ሆነ ባህርያት ላይ ተጽዕኖ አላቸው፡፡ ለምሳሌ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን ተጠቅመው መጻፍን የተለማመዱ ተማሪዎች ትክክለኛ ሀይለ ቃልን፣ ተገቢ ደጋፊ ሀሳቦችን፣ በቂ ዝርዝር ሀሳቦችንና የተሻለ መደምደሚያ ሀሳብን በጽሁፋቸው ውስጥ አካተው መገኘት መቻላቸውን የEmerson (2010) እና Sharrock (2008) ጥናቶች ጠቁመዋል፡፡ የሃሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ተማሪዎች ከሚጽፉበት ርዕሰ ጉዳይ እንዳይወጡ የሚያስችል ትኩረት እንዲኖራቸው ስለሚያደርጉ አንድነታቸውን የጠበቁ አንቀጾችንም እንዲያዋቅሩ ያስችላሉ (Sharrock 2008)፡፡ በተጨማሪም ሀሳቦቹ ያላቸውን ጎናዊና ተዋረዳዊ ቅደምተከተል ስለሚጠቁሙ የሀሳብ ግጥምጥምነቱ የተጠበቀ ጽሁፍ ለማዋቀር እገዛ ያደርጋሉ፡፡ ተማሪዎች በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ተጠቅመው ሲጽፉ በጽሁፋቸው ውስጥ የዘለሏቸውን ቁልፍ ሃሳቦች ለማሟላትም ሆነ በሀሳቦች መካከል ትስስር ያለመፍጠር ችግሮቻቸውን ለመፍታት ያስችሏቸዋል (Ellis, 2004)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሚጽፉበት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ያላቸውን ቀደምት እውቀት እያደራጁና በርዕሰ ጉዳይ ዝምድና ጽንሰሃሳቦችን እያሰናሰሉ በርከትና ሰፋ ያሉ ሀሳቦችን ለማፍለቅ ያግዟቸዋል፡፡

የSinatra (1986) ጥናትን በመጥቀስ Meyer (1995) እንዳስረዱት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን ተጠቅመው መጻፍን የተማሩ ተማሪዎች በሚጽፉት ጽሁፍ ስፋት ብቻ ሳይሆኑ በጥራቱ ጭምር መሻሻል ማሳየት ችለዋል፡፡ በተጨማሪም Miller (2011) ዋቢ ባደረጉት የGraham and Perin (2007) ጥናት በቅድመጽህፈት ደረጃ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን መጠቀም እስከ32% ያህል በተማሪዎች የጽሁፍ ጥራት ላይ ተጽዕኖ እንዳለው አሳይተዋል፡፡ Strangman, Vue, Hall, & Meyer (2004) ባደረጉት ጥናትም ተማሪዎች የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ብልሃቶችን ተጠቅመው በመጻፋቸው የማጠቃለያ አጻጻፍ ጥራታቸው ላይ ጉልህ ልዩነት

ማሳየት ችለዋል። Miller (2011) በበኩላቸው የሀሳብ ማደራጃ ቢ.ጋሮችን እንደቅድመጽህፈት መተግበሪያ መጠቀም በተማሪዎች የመጻፍ ብቃት ደረጃ ላይ የሚያሳድረውን ለውጥ በአይነታዊ ምርምር ፈትሸዋል። በጥናቱ ተግባራዊ የተደረጉት የሀሳብ ማደራጃ ቢ.ጋሮችም አስተዋጽዖ መንደፍ፣ ዝርዝር የሀሳብ ድርና ማወዳደርና ማነጻጸር ነበሩ። ሁለት የአራተኛ ክፍልና አንድ የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደው ይህ ጥናት ተማሪዎቹ የተሰጧቸውን ቴክስቶች አንብበው ሀሳባቸውን በቢ.ጋሮች እንዲያደራጁ እየተደረገ አይነታዊ መረጃዎች ተሰብስበዋል። እያንዳንዱን የሀሳብ ማደራጃ ቢ.ጋር ሦስት ሦስት ጊዜ እንዲጠቀሙ ተደርጎ በተካሄደው ተግባራዊ ምርምር በባለ ስድስት ስኬል መስፈርት በተደረገው ልኬታ ሲመዘኑ በሁሉም የጽሁፍ ገጽታዎች እስከሦስት ነጥቦች ማሻሻላቸው ታውቋል።

ከዚህም በላይ የሀሳብ ማደራጃ ቢ.ጋሮች ተማሪዎች በሚጽፏቸው ጽሁፎች ውስጥ በሚያካትቷቸው ከፍተኛ የቋንቋ አሃዶች ላይ ጭምር መሻሻል እንድታይባቸው ያግዛሉ። ለምሳሌ በአረፍተነገርና በትርክት ግንባታ የአገባብና የድስኩር ውቅር ውስብስብነትን ለማሳለጥ የሀሳብ ማደራጃ ቢ.ጋሮችን በብልሃትነት መጠቀም ፋይዳው ከፍ ያለ እንደሆነ Delrose (2011) በጥናታቸው አመላክተዋል። ይኸውም ከሰባት ሳምንታት ሙከራ በኋላ በድንገት እንዲጽፏቸው በተደረጉ ታሪኮችና በቢ.ጋሮቹ ድጋፍ በጻፏቸው ታሪኮች መካከል ብሎም በቅድመሙከራና በድህረሙከራ አረፍተነገር የማገጣጠም ችሎታቸው ተለክቷል። በውጤቱም በመጻፍ ሂደት ውስጥ የሀሳብ ማደራጃ ቢ.ጋሮችን መጠቀም ውስብስብ አገባባዊ ውቅሮችና ድስኩር ያላቸው አረፍተነገሮችንና ታሪኮችን ለማፍለቅ እንደሚያግዙ መረዳት ተችሏል።

የሀሳብ ማደራጃ ቢ.ጋሮችን ተጠቅሞ መጻፍን መማር ከሌሎች የመጻፍ መማሪያ ስልቶች በተሻለ ሁኔታ የመጻፍ ችሎታን ሊያሻሽል እንደሚችልም ጥናቶች ያመላክታሉ። ለምሳሌ Harrington, Holik, & Hurt (1998) የመጻፍ ዓላማን መለየት የሚያስችል ኮንፈረንስን፣ በትብብር መጻፍ መማርን፣ የሀሳብ ማደራጃ ቢ.ጋሮችን መጠቀምንና የአጻጻፍ መመሪያ ማሳወቅን እንደአማራጭ ብልሃቶች በመተግበር ባካሄዱት ጥናት ከሌሎቹ ብልሃቶች ይልቅ ተማሪዎች የሀሳብ ማደራጃ ቢ.ጋሮችን ሲጠቀሙ በርካታ ለውጦች ማሳየታቸው ተጠቁሟል። ይኸውም ለመጻፍ ያላቸው ደስታ ጨምሯል፤ የመጻፍ ስራን ሲሰጣቸው ወዲያው ወደተግባሩ የመግባት ሁኔታ

ታይቶባቸዋል፤ ለመጻፍ ዓላማ የማስቀመጥ ልምዳቸው ዳብሯል፤ በቢጤ አርትዖት ተግባር ላይ የሚያሳዩት ተሳትፎ ጨምሯል። ይህም የሚያመላክተው የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን መሰረት ያደረገ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ከቅድመጽህፈት እስከአርትዖት ባሉት የመጻፍ ሂደቶች ውስጥ ተማሪዎች የተሳካ ስራ ለመስራት አጋዥ መሆኑን ነው።

በተመሳሳይ Anggrainy, Diem, Vianty, & Sugandi (2016) በሀሳብ ማደራጃ ቢጋርና በምሪት መጻፍ አቀራረብን ባነጻጸሩበት ጥናት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋር የተማሩ ተማሪዎች በምሪት መጻፍ አቀራረብ ከተማሩት የተሻለ የመጻፍ ችሎታ ውጤት እንዳስመዘገቡ አሳይተዋል። ከዚህም ሌላ ፈጥሮ መጻፍን፣ ለመጻፍ የሚያበቃ የቃላት እውቀትን ማስፋትን፣ ፖርትፎሊዮን፣ የአጻጻፍ መመሪያ ማሳወቅንና የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን እንደአማራጭ የመጻፍ ተግባር መከወኛ ብልሃቶች በመተግበር Capretz, Ricker, & Sasak (2003) ባካሄዱት ጥናት ከሌሎቹ ብልሃቶች ይልቅ ተማሪዎች የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን ሲጠቀሙ በርካታ ለውጦች ማሳየታቸው ተጠቁሟል። ይኸውም ተማሪዎች የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን ተጠቅመው በሚጽፉበት ጊዜ ተጨባጭ ከሆነው የእሳቦት ሂደት ረቂቅና ጥልቅ ወደሆኑ ሃሳቦች ማፍለቅ መሸጋገር ችለዋል፤ ይህን ውስብስብ የእሳቦት ሂደትም ሊያሳይ የሚችል እይታዊ ትስስር ፈጥረዋል። በተጨማሪም የተማሪዎቹ የመጻፍ ትኩረት ከ80% ወደ95% ፣ የሀሳብ አደረጃጀት ብቃታቸው ደግሞ ከ68% ወደ84% ከፍ ብሏል።

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ከዝቅተኛ የክፍል ደረጃ እስከዩኒቨርሲቲ ድረስ ባሉ በተለያየ የመጻፍ ችሎታ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች መማርን አሳላጭ እንደሚያደርግ ጥናቶች አመላክተዋል። ለምሳሌ Meyer (1995) ባደረጉት ጥናት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የተደገፈ ልምምድ ያደረጉ የሶስተኛ ክፍል ተማሪዎች የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹን ሳይጠቀሙ ከተማሩት በበለጠ የፈጠራ ጽሁፋቸው ተሻሽሎ መታየቱ ታውቋል። Sharrock (2008) በበኩላቸው የሀሳብ ድር ቢጋርን (concept map) በመጠቀም ለስድስት ሳምንታት በሶስተኛ ክፍል ተማሪዎች የግል ታሪክ መጻፍ ችሎታ ላይ ያለውን ተጽዕኖ በፍትነታዊ ምርምር ፈትሸዋል። በጥናታቸውም ተማሪዎቹ የጻፏቸውን ሁለት ድርሰቶች በተንታኝ እርማት ስልት ተጠቅመው ልኬታ አካሂደዋል። በውጤቱም የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን ሳይጠቀሙ ከጻፉት ጽሁፍ ይልቅ ቢጋሮቹን በመጠቀም በጻፉት ጽሁፍ የተሻለ የመጻፍ ችሎታ እንዳሳዩ ተጠቁሟል።

በተጨማሪም በሀሳብ ማደራጃ ቢጋር የተማሩት ተማሪዎች ፈጥረው በመጻፍ ችሎታቸው ጉልህ መሻሻል እንዳሳዩ ታውቋል፡፡ ከዚህም ሌላ በሚጽፉባቸው ርዕሰጉዳዮች ላይ በመርጋት (በማተኮር) ብሎም ሀሳቦችን በተገቢ ቅደምተከተል በማደራጀት አንጻር ከፍተኛ መሻሻል እንዳሳዩ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ Meera & Aiswary (2014) የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን በብልሃትነት መማራቸው በመጻፍ ችሎታቸው ላይ ያለውን ተጽዕኖ በፍትነትመሰል የጥናት ንድፍ ፈትሸዋል፡፡ በድህረሙከራ በተሰጣቸው ፈተናም የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ የጎላ የመጻፍ ውጤት ማስመዝገቡ ታውቋል፡፡ Ching & Chee (2010)ም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች አጠቃቀም ላይ የሚሰጥ ግብረመልስ ተማሪዎች በጽሁፋቸው ውስጥ የሚያፈልቋቸው ሀሳቦች ለጽሁፉ ያላቸውን ተስማሚነት ደረጃ እንዳሻሻለው አመላክተዋል፡፡

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን ተጠቅሞ መጻፍን መማር የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ለሚማሩ ብቻ ሳይሆን ለሁለተኛና ለውጭ ቋንቋ ተማሪዎች ጭምር አስተዋጽኦ አለው፡፡ ለምሳሌ Ojima (2006) በሦስት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ በሰሩት ጥናት ጽንሰሃሳባዊ ድርን ለመጻፍ ቅድመማቀድ ተግባር መጠቀም ከትክክለኛነት ውጭ ባሉት የጽሁፍ ውጤቶቻቸው ላይ መሻሻል እንዳስከተሉ ማወቅ ችለዋል፡፡ ከዚህም ሌላ በጥናቱ ብልሃቱን በመጠቀም ደረጃ በተማሪዎቹ መካከል የታየው ልዩነት ከልምዳቸው፣ ከተነሳሽነታቸውና ከተግባሩ ሁኔታ ጋር ዝምድና እንዳለው ጭምር ተጠቁሟል፡፡ Marashi, & Massoodi-Hematabadi (2011) በበኩላቸው የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን መጠቀም የውጭ ቋንቋን በሚማሩ ሴት ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ ጉልህ የሆነ ተጽዕኖ እንዳላመጣ አመላክተዋል፡፡ ይሁን እንጂ በዚሁ ጥናት ተማሪዎች በራሳቸው ከሚፈጥሯቸው የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ይልቅ በመምህራን የቀረቡ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች በመጻፍ ውጤት ላይ ጉልህ ልዩነት እንደሚያመጣ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች እይታዊና ቃላዊ መረጃዎችን አጣምረው የሚይዙ ከመሆናቸው አኳያ የተለያዩ የመማር ምርጫዎችም ሆነ የተለያየ የችሎታ ደረጃ ያላቸውን ተማሪዎች ተጠቃሚ ያደርጋሉ (Harrington, Holik, & Hurt, 1998)፡፡ በተመሳሳይ የተለያዩ የመጻፍ ስልቶችን የሚከተሉ ተማሪዎችን የሚያግዙ እንደሆኑ የBromley, Irwin-DeVitis & Modlo (1995) ጥናትን ዋቢ በማድረግ Harrington, Holik, & Hurt (1998) አስረድተዋል፡፡ ለምሳሌ ያህልም

ዋና ሀሳብን ከነንኡስ ሀሳቦች በደረጃ ማስቀመጥ ለሚፈልጉ፣ በምደባ ስልት ከነደጋፊ ማስረጃቸው መግለጽ ለሚፈልጉ፣ የሁነቶችን ወይም የድርጊቶችን ቅደምተከተል ማሳየት ለሚፈልጉ፣ ወዘተ ሁሉ እንደየፍላጎታቸው ሊጠቀሙባቸው እንደሚችሉ ጠቁመዋል፡፡ ከዚህም ሌላ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተከታታይ በሆኑ የመጻፍ ተግባራት ሲሰጧቸው ሀሳብ አፍልቀው የማስፈር ችግር ባለባቸው ተማሪዎች ላይ Young (2005) ባካሄዱት ጥናት በቅድመጽህፈት ደረጃ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን አጠቃቀም በመማራቸው ምስል ፈጣሪ ጽሁፎችን መጻፍ መቻላቸው ተጠቁሟል፡፡

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን ከኮምፒዩተር ቴክኖሎጅ ጋር አስተሳስሮ መጠቀም በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ የሚያስከትለውን ለውጥ የፈተሹ ጥናቶችም አሉ፡፡ በዚህ ዙሪያ ከተሰሩ ጥናቶችም Lin, Strickland, Ray, & Denner (2004) ያደረጉት አንዱ ሲሆን የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የማሳመኛ ጽሁፍ ለመጻፍ በእጅ የተጻፉና በኮምፒዩተር የተደራጁ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን እንደቅድመጽህፈት ብልሃት መጠቀማቸው በመጻፍ ችሎታቸው ላይ ያላቸውን ለውጥ አነጻጽረዋል፡፡ በጥናቱ ውጤት መሰረትም ኮምፒዩተርን በመጠቀም ከቀረቡት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ይልቅ በእጅ በተዘጋጁት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ተመስርተው የጻፉት ተማሪዎች ባፈለቋቸው ቁልፍ ሀሳቦች ብዛት ልቀው ተገኝተዋል፡፡ በተጨማሪም Sturm & Rankin-Erickson (2002) ተማሪዎች የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን ሳይጠቀሙ፣ በእጅ የተጻፉ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን ተጠቅመውና በኮምፒዩተር የቀረቡ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን መሰረት አድርገው ከጻፉ በኂላ ባደረጉት ንጽጽር ሁለቱን የሀሳብ ማደራጃ ስልቶች በተገበሩበት ወቅት በጽሁፋቸው ባካተቷቸው ቃላት ብዛት፣ በመሰረቷቸው ሀረጎች ብዛት፣ በጽሁፍ ጥራታቸው ብልጫ እንዳሳዩ አመላክተዋል፡፡ ከዚህም ሌላ በኮምፒዩተር የታገዘ የጽንሰሃሳባዊ ድሮችን ተጠቅሞ የተማረው ቡድን በእጅ ከተሳሉትም ሆነ ያለምንም የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ከተማሩት ቡድኖች የበለጠ ለመጻፍ ጥሩ አመለካከት አዳብሮ ተገኝቷል፡፡

ከዚህም ሌላ Lorbre (2004) በስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ባደረጉት ጥናት ኮምፒዩተርን መሰረት ባደረጉ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የተጠቀሙ ተማሪዎች በሀሳብ አደረጃጀታቸውና ተገቢ የድርሰት አላባዎችን በማካተት ችሎታቸው የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸውን አመላክተዋል፡፡

Blair, Ormsbee, & Brandies (2002) ባደረጉት ጥናት ደግሞ በኮምፒዩተር የታገዘ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ትምህርት የመረጋጋት ችግር ባለቸው ተማሪዎች ተራኪ ጽሁፍ የመጻፍ ችሎታ ላይ ያለውን ተጽዕኖ ፈትሸው በጽሁፍ ጥራት ደረጃ ያሳየው መሻሻል ዝቅተኛ ቢሆንም በመጠን ደረጃ ግን አበረታች ለውጥ ማሳየቱ ተጠቁሟል፡፡

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ ልዩ ልዩ መሻሻሎችን የሚያመጡ መሆናቸውን ጥናቶች ያሳዩ እንጂ የተጽዕኖ ደረጃቸው የተለያየ ነው፡፡ ለምሳሌ Higgins (2012) ዋቢ ባደረጉት የMoore and Readance (1984) ጥናት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን ተጠቅመውና የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹን ሳይጠቀሙ መጻፍ በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ ያለውን ልዩነት የፈተሹ 23 የታተሙ ጥናቶችን አነጻጽረው ቢጋሮቹን ሲጠቀሙ የተሻለ ችሎታ እንዳሳዩ ጠቁመው የተጽዕኖ ደረጃው በአማካይ ዝቅተኛ (effect size 0. 22) መሆኑን አመላክተዋል፡፡ በአንጻሩ Kansızoğlu (2017) 70 ጥናቶችን ወስደው ባደረጉት ንጽጽር የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች በአራቱም የቋንቋ ክሂሎች ላይ ከፍተኛ አወንታዊ የተጽዕኖ ደረጃ (effect size) እንዳላቸው ጠቁመው ለመጻፍ ችሎታ በአማካይ 0.877 የሆነ ከፍተኛ የተጽዕኖ ደረጃ መገኘቱን ገልጸዋል፡፡ ይህ የተጽኗቸው ደረጃ መለያየትም የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹ ውጤታማነት ተግባራዊ እንደሚደረጉበት የመማር ማስተማር አውድ እንደሚወሰን አመላካች ነው፡፡

## 2.2 የሃሳብ ማደራጃ ቢጋሮችና የመጻፍ ተነሳሽነት

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ ብቻ ሳይሆን ልዩ ልዩ ባህርያቸው ጭምር እንዲሻሻል አስተዋጽዖ ያደርጋሉ፡፡ ከእነዚህ ባህርያት ውስጥ የመጻፍ ተነሳሽነት አንዱ ነው፡፡ በመጻፍ ተነሳሽነትና በመጻፍ ችሎታ መካከል ትስስር መኖሩንም ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ እንደመጻፍ ግለብቃት እምነት፣ የመጻፍ ተግባራትን በራስ መምራት ባሉት የመጻፍ ተነሳሽነት ዘርፎችና በመጻፍ ችሎታ መካከል ዝምድና መኖሩን የMcCarthy et al. (1985)፣ የSchunk & Zimmerman (1994)፣ የZimmerman & Martinez-Pons (1990) ጥናቶችን ዋቢ በማድረግ Pajares (1996) አስረድተዋል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ጥናቶች ተዛምዷዊ

ንድፍን ተከትለው የተሰሩ በመሆናቸው በተላውጦዎቹ መካከል ስለሚኖረው የምክንያትና ውጤት ግንኙነት የተሟላ መረጃ አይሰጡም፡፡

Hashemian & Heidari (2013) እንደገለጹት ደግሞ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች በአራት መንገዶች የተማሪዎችን ተነሳሽነት ለማሻሻል ይረዳሉ፡፡ እነሱም በመጻፍ ተግባራቸው ላይ በጽናት እንዲቆዩ፣ ለመጻፍ ተግባር እንዲገፋፉ፣ የመጻፍ አቅማቸው ከፍ እንዳለ እንዲሰማቸውና አላማቸውን ለማሳካት ቁርጠኝነት እንዲኖራቸው በማድረግ አኳያ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነትና በመጻፍ ችሎታቸው መካከል አወንታዊ ዝምድና መኖሩን ጥናታቸው አመላክቷል፡፡ Cheng (2002) በበኩላቸው መምህራን ተማሪዎቻቸው ለመጻፍ ስራ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ድጋፍ ከሚያደርጉባቸው ብልሃቶች አንዱ በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የታገዘ ትምህርት ማቅረብ እንደሆነ ከጥናት ውጤታቸው በመነሳት አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

መጻፍን በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ተጠቅሞ መማር ተማሪዎች በመጻፍ ችሎታቸው እያሳዩ ያሉትን ለውጥና እድገት ጭምር እየገመገሙ እንዲያልፉ ስለሚያግዙ ትርጉም ያለውና አስደሳች እንደሚያደርገው Marten, Seagraves, Thacker, & Young (2005) ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ Lancaster (2013) የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች በማስተማር ትግበራው መጠቀም ተማሪዎች ለመጻፍ ስራ ፍቅር እንዲያድርባቸው የሚያደርግ የመማሪያ ክፍል አውድ መፍጠሪያ አንዱ መንገድ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ እንደዚህ አይነት አውድ ሲፈጠር ደግሞ የተማሪዎችን የመጻፍ ጭንቀትና ፍርሃት ስለሚቀንሰው ለመጻፍ ያላቸው ተነሳሽነት ይጨምራል፡፡

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን መጠቀም ተማሪዎች የሚጽፉበትን ይዘት በቀላሉ ተረድተው መጻፍ የሚፈጥረውን ጭንቀት ስለሚቀንስላቸው ለመጻፍ ተግባር ያላቸው ተነሳሽነት እንደሚሻሻል Zaini at al. (2010)ም ጠቁመዋል፡፡ Mede (2010) በበኩላቸው ተማሪዎች በመጻፍ ሂደት ውስጥ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን ተጠቅመው ሲጽፉ ቀድሞ ከነበራቸው የመጻፍ አፈጻጸም የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸው ደስታ ስለሚፈጥርባቸው የመጻፍ ተነሳሽነታቸው ከፍ ይላል፡፡

የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን መጠቀም የተማሪዎችን የግለብቃት እምነትና ተነሳሽነት ለማሻሻል እንደሚያስችሉ Eissa (2012) በጥናታቸው አመላክተዋል፡፡ ከእነዚህ ጥናቶች ውጤት መረዳት የሚቻለውም የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የመጻፍ ተነሳሽነት በቀጥታ ከማሳደግ ባለፈ በሌሎች ተላውጦዎች ላይ በሚያደረሱት አወንታዊ ተጽዕኖ ሳቢያ ጭምር የመጻፍ ተነሳሽነት እንደሚሻሻል ነው፡፡

ተማሪዎች ለመጻፍ ስራ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ከሚያደርጉ ሁኔታዎች አንዱ ሁነኛ የመጻፍ ምክንያታቸውን አውቀው ተግባሩን ማከናወን መቻላቸው እንደሆነ የBruning & Horn (2000) ጥናት ዋቢ በማድረግ Hashemian & Heidari (2013) ገልጸው የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን መጠቀም አንዱ ሚናም ይህ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በአንጻሩ የመጻፍ ምክንያታቸውን ባላወቁበት ሁኔታ መጻፍን ሲከውኑ በሚያገኙት ዝቅተኛ የመጻፍ ውጤት የተነሳ የሚያጎለብቱት አሉታዊ ስሜት የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን እንደሚቀንሰው ጭምር አስረድተዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው ተማሪዎች የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን መነሻ አድርገው ለመጻፍ ስራቸው አላማ በማስቀመጥ ስለሚጽፉ መጻፍን እንደአዝናኝ ተግባር የሚያዩበትን ሁኔታ ስለሚፈጥርላቸው የመጻፍ ተነሳሽነታቸው ከፍ ይላል፡፡

## 2.3 የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር፣ የመጻፍ ተነሳሽነትና የመጻፍ ችሎታ ትስስር

መጻፍ በተማሪዎች እሳቦታዊ ችሎታ ብቻ ሳይሆን ስሜታዊ ባህርያት ጭምር ተጽዕኖ የሚደርስበት ነው፡፡ ይህም ሲባል መጻፍ ተማሪዎች በአንድ ጊዜ በርካታ አዕምሯዊ ሂደቶችን በተሳካ ሁኔታ እንዲተገብሩ የሚጠይቅ ክሂል ነው፡፡ ሀሳብን እያስታወሱ ማፍለቅ፣ የመጻፍ አላማን መለየት፣ መጻፍን ማቀድ፣ የመጻፍ መሰናክሎችን መፍታትና የጻፉትን መገምገም የመጻፍ ሂደት ከሚጠይቃቸው አዕምሯዊ ተግባራት ውስጥ ይገኙበታል፡፡ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን መጠቀም እነዚህን የመጻፍ አዕምሯዊ ሂደቶች ያሳልጣሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እነዚህን አዕምሯዊ ተግባራት ለመከወን በተማሪዎች በኩል የመጻፍ ተነሳሽት መኖርን ግድ ይላል (Flower & Hayes, 1981)፡፡ የመጻፍ ተነሳሽነትም የመጻፍ ብቃት ከሚያካትታቸው አላባዎች ወሳኙ ነው (Pajares, 1996)፡፡ በአንጻሩ የመጻፍ ተነሳሽነት የሌላቸው ተማሪዎች

በመጻፍ ተግባራት ሙሉ ተሳትፎ አድርገው የመጻፍ ችሎታቸውን ሊያዳብሩ አይችሉም፡፡ እንዲያውም ለመጻፍ ከፍተኛ ጭንቀት የሚታይባቸው፣ ስለመጻፍ ግለብቃታቸው ያላቸው እምነት ዝቅ ያለ፣ የመጻፍ ስራቸውን በራሳቸው ለመምራት የማይችሉ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል (Payne, 2012)፡፡ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን መሰረት ያደረገ የመጻፍ ክሂል ትምህርትም ተማሪዎች ሀሳብን ከማፍለቅ፣ ከማደራጀትና ከመገምገም ጋር የሚገጥሟቸውን መሰናክሎች ለማቃለል ስለሚያግዛቸው መጻፍን እንደአስቸጋሪ ተግባር እንዳይቆጥሩት ብሎም ደጋግመው የመጻፍ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ስለሚያደርግ የመጻፍ ችሎታቸው እንዲሻሻል በር ይከፍታል፡፡

ተማሪዎች በመጻፍ ሰርቶ ማሳያዎች የመሳተፍ እድል ሲያገኙና ልዩ ልዩ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን የሚጠቀሙበት ልምድ ሲያጎለብቱ መጻፍ ትርጉም ያለው፣ ፈጠራ የሚንጸባረቅበትና አስደሳች ሆኖ እንዲሰማቸው እንደሚያደርግ Lancaster (2013) አስገንዝበዋል፡፡ ከዚህም አልፎ ተማሪዎች ከጫናና ከፍርሃት ነጻ በሆኑ ሁነቶች ውስጥ መጻፍን የሚለማመዱበት እድል ሲፈጠርላቸው በመጻፍ ሂደት ውስጥ በራሳቸው የሚተማመኑና ምቾት የሚሰማቸው እንዲሆኑ ማድረጉን ጠቁመዋል፡፡ ይህም ተጨማሪ የመጻፍ ተግባራትን በራሳቸው አነሳሽነት በመተግበር የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች አቅም የሚፈጥሩላቸው መሆኑን ያመላክታል፡፡

የመጻፍ ዓላማን መለየት የሚያስችል ኮንፈረንስን፣ በትብብር መጻፍ መማርን፣ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን መጠቀምንና የአጻጻፍ መመሪያ ማሳወቅን እንደአማራጭ ብልሃቶች በተገበሩበት የHarrington, Holik, & Hurt (1998) ጥናት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹ ከሌሎቹ ሁለት ብልሃቶች በበለጠ ተማሪዎች ለመጻፍ ያላቸው ደስታ እንዲጨምር፤ የመጻፍ ስራን ሲሰጣቸው ወዲያውኑ ወደተግባሩ እንዲገቡ፤ በቢጤ አርትዖት ተግባር ላይ የሚያሳዩት ተሳትፎ ከፍ እንዲል ከማድረጋቸው ጋር ተያይዞ የመጻፍ ተነሳሽታቸው እንደተሻሻለ አመላክቷል፡፡
በመጨረሻም የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር፣ የመጻፍ ተነሳሽነትና የመጻፍ ችሎታ ከላይ በተነሱት አኳኋን ትስስር ያላቸው መሆኑን አመላካች ጥናቶቹ ቢኖሩም ጉዳዩ በስፋትና በጥልቀት የተዳሰሰ አይመስልም፡፡ በመሆኑም ሶስቱንም ተላውጦች በአንድ ጥናት አካቶ ተጨማሪ ፍተሻ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑም ይህ ጥናት ተካሂዷል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት፤ የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የምርምሩ ስልት

ጥናቱ ባለሁለት ቡድን ሲሆን የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ፤ ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ፈተና ያለው ፍትነትመሰል ንድፍ (Quasi-experimental pre-test and post-test with comparison group) የተከተለ ነው፡፡ የንድፉ መዋቅርም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

| ቡድን | ቅድመትምህርት ፈተና | ልዩነት ፈጣሪ | ድህረትምህርት ፈተና |
|---|---|---|---|
| የሙከራ | ✓ | ✓ | ✓ |
| የቁጥጥር | ✓ | X | ✓ |

## 3.2 የጥናቱ ተሳታፊዎች

የጥናቱ ተተኳሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ተማሪዎች ናቸው፡፡ በአጣዬ ከተማ የከፍተኛ መሰናዶ ትምህርትና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት በ2010 ዓ.ም በዘጠነኛ ክፍል የሚማሩ ወንድ 503፣ ሴት 512 በድምሩ 1015 ተማሪዎች የጥናቱ ተተኳሪዎች ነበሩ፡፡ የጥናቱ ቦታም ሆነ ጥናቱ የተካሄደበት ትምህርትቤት የተመረጡት በዓላማ ንሞና ዘዴ ነው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ቦታው ለአጥኚዋ የስራ አካባቢ ቅርብ በመሆኑ ጥናቱን በቅርበት ለመከታተል፣ በጥናቱ የሚያግዙ መምህራንን ለማግኘትና በጥናቱ የሚሳተፉ ተማሪዎችን ትብብር ለማግኘት፣ ከልዩ ልዩ ወጪዎች አንጻርም የተወሰነ ቅናሽ ስለሚኖረው ነው፡፡

ጥናቱ የቡድን ንሞና ዘዴ (cluster sampling) የተከተለ ነው፡፡ይሁን እንጂ የሙከራ ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ የተለዩት እኩል እድል ሰጭ ንሞናን ተከትሎ ነው፡፡ ይኸውም በትምህርት ቤቱ ከተገኙት የዘጠነኛ ክፍል 17 የመማሪያ ክፍሎች በተራ እጣ ንሞና ዘዴ 9ኛ B እና 9ኛ C ተመርጠዋል፡፡ ከዚያም ቅድመትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና እንዲፈተኑ ከተደረገ በኋላ ሙከራው ከመካሄዱ በፊት በመጻፍ ችሎታቸው ተመጣጣኝ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በቅድመትምህርት ፈተና ውጤቱ መሰረት በመጻፍ ችሎታቸው ያላቸው ተመጣጣኝነት ከታወቀ በኋላም ለሁለቱ መማሪያ ክፍሎች እጣ በመምታት 9ኛ B የሙከራ ቡድን፣ 9ኛ C ደግሞ የቁጥጥር ቡድን መሆናቸው ተለይቷል፡፡ በመሆኑም በ9ኛ B ውስጥ የተገኙት ወንድ 20፣ ሴት 26 በድምሩ 46 ተማሪዎች በሙከራ ቡድኑ የተሳተፉ ሲሆን፣ በ9ኛ C ውስጥ የተገኙት ወንድ 22፣ ሴት 24 በድምሩ 46 ተማሪዎች በቁጥጥር ቡድኑ ተሳትፈዋል፡፡

## 3.3 የማስተማሪያ ቴክስቶች አዘገጃጀትና የማስተማር ትግበራ

በዚህ ጥናት የተተኮባረቸው የቅደምተከተላዊ፣ ምክንያትና ውጤት፣ የዋናና ዝርዝር፣ አወዳዳሪና አነጻጻሪ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ናቸው፡፡ በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹ መጻፍን ለሚማረው የሙከራ ቡድን ማስተማሪያ የተዘጋጁት መልመጃዎች በየክፍለትምህርቱ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ምንነትና ባህርይ ለተማሪዎቹ በማስተዋወቅ ይጀምራሉ፡፡ ከዚያም እያንዳንዱን የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ነጥሎ በማቅረብ በእሱ ላይ ብቻ ትኩረት እንዲሰጡ የሚያደርጉ ተግባራት ቀርበዋል፡፡ በዚህም የተለያዩ ጽሁፎችን ለመጻፍ እንደማወዳደርና ማነጻጸር፣ ቅደምተከተል፣የዋናና ዝርዝር፣ ምክንያትና ውጤት ያሉትን የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ግንዛቤ እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡ በመቀጠል ታላሚውን የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ለማለማመድ የሚያስችሉ ቀደም ሲል የተመረጡ የመጻፊያ ርዕሶች ተሰጥተው ተለማምደዋል፡፡ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ እንዲለዩም በአጋዥነት የሚረዷቸውን የቴክስት ጠቋሚዎችን፣ የመሸጋገሪያ ስልቶችንና ዓላማዎቻቸውን የሚያሳዩ የብልሃቶቹ ማስተማሪያ ተግባራት ተካተዋል፡፡ በተጨማሪም ውቅር ጠቋሚ ጥያቄዎችን ጣልቃ በማስገባት መልሳቸውን ከጽሁፋቸው እንዲሰጡ የሚጠይቁ ተግባራት ተሰጥተዋል፡፡ ከጠቋሚ ቃላቱና ሐረጋቱ ጋር ከተዋወቁ በኋላም ጠቋሚዎቹን ተከትለው ተቆራራጭ (template) ወይም ጅምር (frame) ውቅርን እንዲጽፉ ተደርጓል፡፡ ይህም ለእያንዳንዱ ውቅር የግጥምጣሜ መመስረቻ አያያዦችን

በመጠቀም ቃላት፣ ሐረጋት፣ አረፍተነገሮችና ሀሳቦች እንዴት እንደተዛመዱ ጽሁፉን እንደሚገነቡ ይገነዘባሉ፡፡ በመቀጠልም ባዶ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ከሚዛመደው ርዕስ ጋር ተሰጥቷቸው ለጽሁፋቸው መነሻ መሰረታዊ ሀሳቦችን በማደራጃዎቹ ጽፈዋል፡፡ በዚህ ሂደትም ዋናና ደጋፊ ሀሳቦችን ይለያሉ፤ የምክንያትና ውጤት፣ የማወዳደርና ማነጻጸር፣ የዋናና ዝርዝር፣ የቅደምተከተል ተዛምዶዎች የሚታዩባቸውን ሀሳቦች እየለዩ ሀሳባቸውን በማስፋፊት ጽሁፋቸውን አሟልተው እንዲጽፉ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም ከብልሃት ልምምዱ ጋር ተያያዥ የሆኑ የጽብረቃና ግምገማ ጥያቄዎችን በማቅረብ ተማሪዎቹ ስለሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ምንነት፣ አጠቃቀምና ፋይዳ በልምምድ ሂደቱ የተገነዘቧቸውን ሀሳቦች ማንጸባረቅ የሚችሉባቸውን ተግባራት ቀርበዋል(እንድሪስ፣ 2009)፡፡ በአጭሩ ለዚህ ቡድን ተሳታፊዎች የቀረበው ማስተማሪያ እነዚህን ይዘቶች ከላይ በተገለጹት ግልጽ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ብልሃቶች ማለማመጃ ተግባራት በቅደምተከተል ለማለማመድ በሚያስችል ሁኔታ ተዘጋጅቷል፤ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹንም ለምን፣ መቼና እንዴት እንደሚጠቀሙባቸው በግልጽ ተምረዋል፤ በብልሃቶቹ ትግበራ ወቅት የሚገጥሟቸውን ችግሮች እንዴት መፍታት እንደቻሉ የሚያንጸባርቁበት እድል በሚሰጥ ሁኔታ ቀርበዋል (አባሪ **ሀ** ይመለከቷል)፡፡ የማስተማር ትግበራውም በዚሁ በተገለጸው ሁኔታ የተካሄደ ነበር(አባሪ **ለ** ይመለከቷል)፡፡

በተለመደው አቀራረብ የመጻፍ ክሂልን ለተማረው የቁጥጥር ቡድን ደግሞ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ትምህርት ሚኒስተር በ2004 ዓ.ም አሻሽሎ ባዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በሚገኙ የመጻፍ ክሂል የማስተማሪያ ዘዴዎች መልመጃዎቹን እንዲማር ተደርጓል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የመጻፍ ክሂል መማሪያ መልመጃዎችም በአረፍተነገሮች ውስጥ የተጓደሉ ቃላትንና ሀረጋትን ማሟላት፣ በተሰጣቸው ርእስ ተራኪ ድርሰት መጻፍ፤ በጅምር የቀሩ ሃሳቦችን መጨረስ፣ ከምንባብ የወጡ አረፍተነገሮችን በራሳቸው አባባል ቀይረው መጻፍ፣ አካባቢያቸውን የሚያስረዳ ገላጭ ጽሁፍ መጻፍ፣ ከተሰጡ ርዕሶች አንዱን መርጠው አንቀጽ መጻፍ፣ የምንባብን ሀሳብ አሳጥሮ መጻፍ፣ ስርዓተነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው አስገብተው መጻፍ፣ የመንስኤና ውጤት ትስስርን የሚያሳዩ አረፍተነገሮችን መጻፍ የተለማመዱባቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የመጻፍ ክሂል መልመጃዎች የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን እውቀትንም ሆነ የሀሳብ ማደራጃ

ብልሃቶችን ለተማሪዎቹ የሚያስተዋውቁ አይደሉም፡፡ የማስተማር ትግበራውም በዚሁ በተገለጸው አግባብ የተከናወነ ነበር (አባሪ ሐ ይመለከቷል)፡፡

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያነት የዋሉት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተናና የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ የጽሁፍ መጠይቅ ናቸው፡፡

### 3.4.1 ፈተና

የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች በጥናቱ ሂደት ሁለት ጊዜ የመጻፍ ችሎታ ፈተናን ተፈትነው መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የመጀመሪያው ቅድመትምህርት (Pre-test) የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና ሲሆን የዚህ ፈተና አላማ የተገኘው የፈተና ውጤት (አባሪ የ እና ደ ይመለከቷል) በጥናቱ መነሻ ላይ በሙከራ ቡድኑና በቁጥጥር ቡድኑ ተመጣጣኝ ውጤት ያላቸውን የናሙና አባላት ለማደራጀት ስራ ውሏል፡፡ በተጨማሪም ይህ ውጤት ለጥናቱ ለተመረጡት ተማሪዎች የቅድመትምህርት የመጻፍ ችሎታ ውጤት ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ሌላው ፈተና ድህረትምህርት (Post-test) የመጻፍ ችሎታ ፈተና ነው፡፡ የዚህ ፈተና ዓላማ ሁለቱ ቡድኖች በተለያዩ ዘዴዎች በመማራቸው የመጻፍ ችሎታ ውጤት (አባሪ ጀ እና ገ ይመለከቷል) መበላለጥ ማሳየት አለማሳየታቸውን በሚመለከት መረጃ ማስገኘት ነው፡፡

ለቅድመትምህርትና ለድህረትምህርት የቀረበው ፈተና አንድ ሲሆን ከቅድመፍተሻ በፊት አምስት ክፍሎችን ይዞ የተዘጋጀ ነበር(አባሪ ረ ይመለከቷል)፡፡ ይኸውም በአንቀጽ ውስጥ የቀረቡ የመሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን ለይቶ መጻፍ፣ በአረፍተነገሮች ውስጥ የሚታዩ አላስፈላጊ ድግግሞሾችን በማስወገድ በራስ አባባል እንደገና መጻፍ፣ የተዘበራረቁ አረፍተነገሮችን በማስተካከል የመንስኤና ውጤት ትስስርን የሚያሳይ አንቀጽ መጻፍ፣ የተዘበራረቁ አረፍተነገሮችን ቅደምተከተል በማስተካከል ገላጭ አንቀጽን መጻፍ፣ በአንድ ርዕስ በመጀመሪያ መንደርደሪያ አረፍተነገርን በመመስረት የሀሳብ ዝምድናቸውን የጠበቁ፣ ከዋናው ሀሳብ ያላፈነገጡ፣ ሰዋስዋዊ ስህተቶች የሌሉባቸውና ተገቢ የስርዓተነጥቦች አጠቃቀም በሚታይባቸው

አረፍተነገሮች የምክንያትና ውጤት ትስስርን የሚያሳይ አንቀጽ መገንባትን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ይዟል። እነዚህ ጥያቄዎች የተመረጡበት ምክንያት በክፍል ደረጃው ለማስተማሪያነት በቀረበው የተማሪ መጽሃፍም ሆነ በመርሃትምህርቱ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች በአመዛኙ ያላቸውን የይዘት ትኩረት መነሻ በማድረግ ነው። በተጨማሪም የተመረጡት ይዘቶች በተማሪ መጽሃፍ ውስጥ በተደጋጋሚ ለልምምድ የቀረቡ መሆናቸው ከሌሎቹ የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ይልቅ በፈተናው እንዲካተቱ ለመመረጣቸው ምክንያት ሆኗል።

ፈተናው በዚህ መልኩ ከተዘጋጀ በኋላ አንድ የ3ኛ ዲግሪ ያለው የዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ መምህር፣ አንድ ሁለተኛዲግሪ ያለው መምህርና የመጀመሪያ ዲግሪ ያላው የመሰናዶ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ገምግመው አስተያየት ሰጥተውበታል። በባለሙያዎቹ የግምገማ አስተያየት መሰረት በአንቀጽ ውስጥ ቃልን ከቃል፣ አረፍተነገርን ከአረፍተነገር፣ አንቀጽን ከአንቀጽ ያያያዙ መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላትንና ሀረጋትን ለይተው እንዲያወጡ የሚጠይቀው የፈተናው ክፍል እጅግ ቀላል ሆኖ በመገኘቱ እንዲቀነስ ተደርጓል። በምትኩ **"የደን መጨፍጨፍን"** በሚል ርዕስ አንቀጽ እንዲገነቡ የሚያደርግ ጥያቄ ተጨምሯል። የባለሙያዎቹን አስተያየት መሰረት አድርጎ የተሻሻለው ፈተናም ለዋናው ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት ከመዋሉ በፊት በቅድመጥናት (pilot study) ደረጃ ከዋናው ጥናት ተሳታፊዎች ጋር ተመሳሳይ ሁኔታ ላላቸው ተማሪዎች ቀርቦ የተግባሪነቱ ተፈትሿል። በዚህ ወቅት ተማሪዎቹ ፈተናውን ሰርተው ለመጨረስ ረጅም ጊዜ ስለወሰደባቸው አብዛኛዎቹ ያልሰሯቸው ጥያቄዎች ታይተው ተቀንሰዋል። ከተቀነሱት ውስጥም አላስፈላጊ ድግግሞሽን አስወግደው አረፍተነገሮችን አስተካለው እንዲጽፉ ከሚጠይቁት ስድስት ጥያቄዎች ሁለቱ ይገኙበታል። ከዚህም ሌላ የተዘበራረቁ አረፍተነገሮችን ቅደምተከተል በማስተካከል አንቀጽ እንድገነቡ ከሚጠይቁት ሁለት ተግባራት አንዱ እንዲወጣ ተደርጓል። ከቅድመጥናት ፍተሻው በተገኙ መረጃዎች መነሻም አስፈላጊውን ማሻሻያ በማድረግ ለዋናው ጥናት ውሏል(አባሪ ሰ ይመለከቷል)። እንዲሁም ፈተናው በዋናው ጥናት ወቅት የእያንዳንዱ የጥናቱ ተሳታፊ መልስ በሶስት ኮፒ ተባዝቶ፣ በሶስት አራሚዎች ታርሞ የአራሚዘለል አስተማማኝነቱ (inter-rater reliability) በክሮንባኽ አልፋ (Cronbach Alpha) ቀመር ተፈትሾ በቅድመትምህርት α=

.981፣ በድህረትምህርት α= .994 የአስተማማኝነት ውጤት ተገኝቷል፡፡ ይህም የተገኘው ውጤት ከፍተኛ አስተማማኝነት እንዳለው ያመላክታል፡፡

### 3.4.2 የጽሑፍ መጠይቅ

የዚህ ጥናት ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡ የጽሁፍ መጠይቁም ተማሪዎች በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች መጻፍን መማራቸው ለመጻፍ ስራ ባላቸው ተነሳሽነት ላይ የሚያስከትለው ለውጥ እንዳለ ለመፈተሽ ያገለገለ ነው፡፡ መጠይቁ Payne (2012) ለተመሳሳይ ተግባራት የተጠቀሙበትን በአጥኚዋ ወደአማርኛ ቋንቋ ተተርጉሞ የተዘጋጀ ነው (አባሪ መ ይመለከቷል)፡፡ ይህ መጠይቅ 37 ጥያቄዎች ያሉት ሲሆን ከበጣም አልስማማም (0) እስከበጣም እስማማለሁ (4) የሚሉ አምስት አማራጮችን ይዞ በሊከርት ስኬል የተዘጋጀ ነው፡፡ በዋናነትም የመጻፍን አስደሳችነት (enjoyment) ጥያቄ ተራ ቁጥር 1፣ 9፣ 17፣ 22፣ 25፣ 26፣ 28፣ 29፣ 31፣ 33፣ 34ና 37፤ የመጻፍ ግለብቃት እምነት (self efficacy) ጥያቄ ተራ ቁጥር 3፣ 4፣ 6፣ 11፣ 12፣ 15፣ 24ና 36፤ የመጻፍ አገልግሎት (instrumentality) ጥያቄ ተራ ቁጥር 5፣ 14፣ 19፣ 20ና 30፤ በመጻፍ የሚገኝ እውቅና (recognition) ጥያቄ ተራ ቁጥር 2፣ 10፣ 21ና 32 እና ለመጻፍ የሚደረግ ጥረት (effort) ጥያቄ ተራ ቁጥር 7፣ 8ና 27 የሚሉ አምስት የመጻፍ ተነሳሽነት ዘርፎችን አካቶ የቀረበ ነው፡፡ መጠይቁ በክሮንባኽ አልፋ (Cronbach Alpha) ቀመር በተደረገለት የአስተማማኝነት ፍተሻም α= 0.95 የተገኘ በመሆኑ ከፍተኛ አስተማማኝነት እንዳለው ተጠቁሟል፡፡ ከዚህም ሌላ ከላይ በተዘረዘሩት የመጻፍ ተነሳሽነት ዘርፎች ስር ለሚገኙ ጥያቄዎች በተደረገለት የፋክተር ትንተና (Factor Analysis) ለመጻፍ አስደሳችነት ከ0.486 እስከ0.820፣ ለመጻፍ ግለብቃት እምነት ከ0.431 እስከ0.760፣ ለመጻፍ አገልግሎት ከ0.653 እስከ0.816፣ በመጻፍ የሚገኝ እውቅና ከከ0.421 እስከ0.839፣ ለመጻፍ የሚደረግ ጥረት ከ0.458 እስከ0.708 ዝምድና እንዳላቸው ማመላከቱ በመገለጹ ጥያቄዎቹ እያንዳንዱን ንኡስ ዘርፍም ሆነ አጠቃላይ የመጻፍ ተነሳሽነትን ለመለካት የሚያስችል የጋራ ባህርይ እንዳላቸው ተመላክቷል፡፡

ይህ መጠይቅ በአጥኚዋ ወደአማርኛ ከተተረጎመ በኋላም በቅድመጥናት (pilot study) ደረጃ ከዋናው ጥናት ተሳታፊዎች ጋር ተመሳሳይ ሁኔታ ላላቸው 30 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች

ቀርቦ አስተማማኝነቱ በክሮንባኽ አልፋ (Cronbach Alpha) ቀመር ተፈትሾ $\alpha$=0.909 አስተማማኝነት መጠን ተገኝቷል (አባሪ ቀ ይመለከቷል)፡፡ ስሌቱንም ተከትሎ አንድም ጥያቄ ሳይቀነስ በአንዳንድ ጥያቄዎች ላይ ብቻ መጠነኛ የቃላትና ሀረጋት ማሻሻያ ተደርጎበት (አባሪ ሠ ይመለከቷል) ለዋናው ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያነት ውሏል፡፡ በዋናው ጥናት ወቅትም በሁለቱ ቡድኖች ከተሳተፉ 92 ተማሪዎች በዚሁ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ አስተማማኝነት በድጋሜ በክሮንባኽ አልፋ ቀመር ሲፈተሽ በቅድመትምህርት ደረጃ $\alpha$= 0.930፣ በድህረትምህርት ደረጃ $\alpha$= 0.912 መገኘቱ አስተማማኝነቱ ከፍተኛ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል (አባሪ በእና ቸይመለከቷል)፡፡

## 3.5 የአጠናን ሂደት

የጥናቱ አሰራር ቅድመጥናት (pilot) እና ዋና ጥናት (main study) የሚሉ ሁለት የሂደት ደረጃዎችን የተከተለ ነው፡፡ እያንዳንዱ ደረጃም የራሱ ዓላማዎች፣ ተሳታፊዎችና የአሰራር ዘዴዎች አሉት፡፡

ቅድመጥናቱ የማስተማሪያ ተግባራት፣ የጽሁፍ መጠይቅ ጥያቄዎች፣ የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተናው ጥያቄዎች ተገቢነት በባለሙያዎች የተገመገሙበትና በሙከራ የተፈተሹበት ነው፡፡ ዓላማው መሳሪያዎቹ ለዋናው ጥናት ከመቅረባቸው በፊት ከይዘትና ቅርጽ አኳያ ያላቸውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ነው፡፡ የሙከራ ቡድኑ የመማሪያ ተግባራትና የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ከልዩ ልዩ ምንጮች በመነሳት በአጥኚዋ ከተዘጋጁ በኋላ ከዋናው ጥናት ቀደም ብሎ በልዩ ልዩ ባለሙያዎች ግምገማ ተደርጎባቸዋል፡፡ በፍተሻው የተሳተፉት የጥናቱ አማካሪ፣ በዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህርና በደረጃው የሚያስተምሩ መምህራን ናቸው፡፡ ከዚያም በዋናው ጥናት ከሚሳተፉ ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ የክፍል ደረጃ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች በማቅረብ ተገቢነታቸውን፣ ትክክለኛነታቸውንና አስተማማኝነታቸውን የመፈተሽ ስራ ተሰርቷል፡፡ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተገኙ አስተያየቶችን መነሻ በማድረግ የመማሪያ ተግባራቱም ሆኑ መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎቹ በአጥኚዋ እንደገና ተሻሽለው ለዋናው ጥናት ዝግጁ ተደርገዋል፡፡

ዋናው ጥናት ሲካሄድም የመማሪያ ማንዋሎቹና መረጃ መሰብሰቢያዎቹ በዚህ መልኩ ከተዘጋጁ በኋላ በ1/08/2010 ዓ.ም የአጣዬ ከተማ የከፍተኛ መሰናዶ ትምህርትና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ኃላፊዎች በተገኙበት ተማሪዎቹ በጥናቱ ለመሳተፍ ያላቸው ፈቃደኝነት ተጠይቆ ፈቃደኝነታቸውን ከገለጹ በኋላ ካሉት 17 የዘጠነኛ ክፍል መማሪያዎች በእጣ ሁለቱ የመማሪያ ክፍሎች ተለይተዋል፡፡ ከዚህ በኋላም የሁለቱም መማሪያ ክፍሎች ተማሪዎች ትምህርቱን ከመጀመራቸው በፊት በ9/08/2010 ዓ.ም ቅድመትምህርት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ ከዚያም በ10/08/2010 ዓ.ም ቅድመትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቁን ሞሉ፡፡

በቅድመትምህርት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተናው የሁለቱ መማሪያ ክፍል ተማሪዎች በመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤቶቻቸው ትንተና ተቀራራቢ መሆናቸው ከታወቀ በኋላ የትኛው የቁጥጥር ወይም የሙከራ ቡድን እንደሚሆን በእጣ ተለይተዋል፡፡ በእጣውም መሰረት 9ኛB ክፍል በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች መጻፍን የሚማረው የሙከራ ቡድን፣ 9ኛC ደግሞ ያለሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹ በተለመደው መንገድ መጻፍን የሚማረው የቁጥጥር ቡድን መሆናቸው ታወቀ፡፡

ቅድመትምህርት የመጻፍ ችሎታቸው ተመጣጣኝ መሆኑ በዚህ መልኩ ከታወቀ በኋላ ከ16/08/2010 ዓ.ም ጀምሮ እስከ12/10/2010 ዓ.ም ድረስ ሁለቱም ቡድኖች በተመደቡላቸው የመጻፍ ክሂል መማሪያዎች በስምንት ሳምንታት ውስጥ በሳምንት ሁለት ክፍለጊዜያት በጠቅላላው ለ17 ክፍለጊዜያት ትምህርቱን ተማሩ፡፡ የስምንት ሳምንታቱ ትምህርት ከተጠናቀቀ በኋላም በ14/10/2010 ዓ.ም ሁለቱም ቡድኖች በተመሳሳይ ሁኔታ ድህረትምህርት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና ተፈተኑ፡፡ ከዚያም ፈተናውን በተፈተኑበት በቀጣዩ ቀን ድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቁን ሞሉ፡፡ በመረጃ አሰባሰብ ሂደቶቹም እንደኩረጃ፣ የመፈተኛ አካባቢ ድምጽ ረብሻና የጊዜ እጥረት ያሉት በመረጃ ትክክለኛነት ላይ ተጽዕኖ የሚያደርሱ ሁነቶችን ለመቆጣጠር አስፈላጊው ጥንቃቄ ተደርጓል፡፡

በአጭሩ ከቅድመጥናቱ የተገኙ ልዩ ልዩ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ አስፈላጊ ማሻሻያዎች በተደረገባቸው መሳሪያዎች ዋናው ጥናት ተካሂዷል፡፡ ዋናው ጥናትም በታቀደው የጥናት ንድፍ መሰረት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም በጥናቱ የተገኙት ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት መረጃዎች ተተንትነው አስፈላጊው ማጠቃለያና መደምደሚያ ላይ ተደርሷል፡፡

## 3.6 የጥናቱ ስነምግባራዊ ሁኔታ

ጥናቱ በተሳታፊዎች ላይ የሚያሳድረው ተለይቶ የታወቀ አሉታዊ ተጽዕኖ ባይኖርም በዚህ ጥናት የተሳተፉ ተማሪዎች በፈቃደኝነት ለሚያደርጉት ተሳትፎ የስምምነት ውል ሞልተዋል፡፡ በስምምነቱም የጥናቱን አላማ በግልጽ ማሳወቅን፣ በጥናቱ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት መግለጽን፣ የግላዊ መረጃ ሚስጥር አጠባበቅን፣ የተሳታፊነት መብቶችን፣ ጥናቱ የሚፈጀውን ጊዜ የመሳሰሉት ተካተው የጥናቱ ተሳታፊዎች በፈቃደኝነት አውቀው እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ ከዚህም ሌላ የሁሉንም ተማሪዎች ወላጆች አግኝቶ ማነጋገር ባይቻልም የትምህርት ቤቱ ወላጅ-ተማሪ-መምህራን ህብረት(ወተመህ) ስለጥናቱ ግልጽ ማብራሪያ ቀርቦላቸው ፈቃዳቸው ተጠይቋል፡፡

## 3.7 የመረጃ አተናተን ዘዴ

የጥናቱን ተሳታፊዎች በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን ለማደራጀት የዋለው ቅድመትምህርት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና ለየቡድኖቹ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት ተሰልቷል፡፡ በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል የጎላ ልዩነት መኖር አለመኖሩም በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (independent samples t-test) ፍተሻ ተካሂዶበታል፡፡ ከፍተሻውም ቀደም ብሎ በዋናው ጥናት ወቅት በቅድምትምህርት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተናው ተማሪዎቹ ያገኙት ውጤት ወጥ ስርጭት ያለው መሆን አለመሆኑን በልዩ ልዩ ቀመሮች የስጭት ወጥነት (Tests of Normality) ፍተሻ ተደርጓል፡፡ በፍተሻው መሰረትም በኮልሞጎሮቭ-ስሚኖቭ (Kolmogorov-Smirnov) ስሌት ተሰልቶ ለቁጥጥር ቡድኑ 0.115 የተዛምዶ መጠን በ46 የነፃነት ደረጃ (df) የጉልህነት መጠኑ (0.161) ከ0.05 ስለሚበልጥ ጉልህ ሆኖ አልታየም፡፡ በተመሳሳይ ለሙከራ ቡድኑም የተገኘው 0.089 የተዛምዶ መጠን በ46 የነፃነት ደረጃ (df) የጉልህነት መጠኑ (0.200) ከ0.05 ስለሚበልጥ ጉልህ አለመሆኑን አሳይቷል፡፡ ተዛምዶው ጉልህ አለመሆኑም

የየቡድኖቹ ቅድመትምህርት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና ውጤት ወጥ ስርጭት እንዳለው አመልክቷል። በተጨማሪም በተያያዥ አምድ ግራፍ በተደረገው ፍተሻም የውጤቶቹ ስርጭት ወጥነት እንዳለው ታውቋል (አባሪ ኘ ይመለከቷል)። ይህም በፓራሜትራዊ ቴስት የሆነውን የባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ለመጠቀም አንዱ እሙን እንደተሟላ አሳይቷል።

ሙከራው እንደተጠናቀቀ ሁለቱ ቡድኖች የተፈተኑት ድህረትምህርት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተናው ውጤትም ለየቡድኖቹ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት ተሰልቷል። ቡድኖቹ በአማካይ ውጤቶቻቸው ልዩነት መታየት አለመታየቱም በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (independent samples t-test) ፍተሻ ተደርጎበታል። ከዚህ ፍተሻ ቀደም ብሎ በዋናው ጥናት ወቅት በድህረትምህርት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተናው ተማሪዎቹ ያገኙት ውጤት ወጥ ስርጭት ያለው መሆን አለመሆኑን በልዩ ልዩ ቀመሮች የስጭት ወጥነት ፍተሻ ተደርጓል። በፍተሻው መሰረትም በኮልሞጎሮቭ-ስሚኖቭ ስሌት ተሰልቶ ለቁጥጥር ቡድኑ 0.098 የተዛምዶ መጠን በ46 የነፃነት ደረጃ (df) የጉልህነት መጠኑ (0.200) ከ0.05 ስለሚበልጥ ጉልህ ሆኖ አልታየም። በተመሳሳይ ለሙከራ ቡድኑም የተገኘው 0.115 የተዛምዶ መጠን በ46 የነፃነት ደረጃ (df) የጉልህነት መጠኑ (0.154) ከ0.05 ስለሚበልጥ ጉልህ አለመሆኑን አሳይቷል ። ተዛምዶው ጉልህ አለመሆኑም የየቡድኖቹ ድህረትምህርት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና ውጤት ወጥ ስርጭት እንዳለው ያመላክታል። በተጨማሪም በተያያዥ አምድ ግራፍ በተደረገው ፍተሻም የውጤቶቹ ስርጭት ወጥነት እንዳለው ታውቋል (አባሪ አ ይመለከቷል)። ይህም በፓራሜትራዊ ቴስት የሆነውን የባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ለመጠቀም አንዱ እሙን እንደተሟላ አሳይቷል።

በሁለቱ ቡድኖች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በቅድመትምህርት ደረጃ ያላቸው የመጻፍ ተነሳሽነት ተመጣጣኝ መሆኑን ለመለካት ከቀረበው መጠይቅ የተገኘው መረጃም ለቡድኖቹ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት ስሌት ተደርጓል። በአማካይ ውጤቶቻቸው ልዩነት መታየት አለመታየቱም በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (independent samples t-test) ተፈትሿል። ሙከራው እንደተጠናቀቀ ሁለቱ ቡድኖች በመጻፍ ተነሳሽነታቸው መለያየት መኖር አለመኖሩን ለመለካት በድጋሚ ከሞሉት መጠይቅ የተገኘው ውጤትም ለየቡድኖቹ አማካይ ውጤትና መደበኛ

ልይይት ተሰልቷል። ቡድኖቹ በአማካይ ውጤቶቻቸው ልዩነት መታየት አለመታየቱም በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (independent samples t-test) ፍተሻ ተካሂዶበታል።

በዋናው ጥናት ወቅት በቅድምትምህርትና በድህረትምህርት ደረጃ የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቁ ተማሪዎቹ ያገኙት ውጤት ወጥ ስርጭት ያለው መሆን አለመሆኑን በልዩ ልዩ ቀመሮች የስጭት ወጥነት (Tests of Normality) ፍተሻ ተደርጓል። በፍተሻው መሰረትም በኮልሞጎሮቭ-ስሚኖቭ ስሌት ተሰልቶ ለቁጥጥር ቡድኑ በቅድመትምህርት 0.098 የተዛምዶ መጠን በ46 የነፃነት ደረጃ (df) የጉልህነት መጠኑ (0.200) ከ0.05 ስለሚበልጥ ብሎም በድህረትምህርት 0.107 የተዛምዶ መጠን በ46 የነፃነት ደረጃ (df) የጉልህነት መጠኑ (0.200) ከ0.05 ስለሚበልጥ ጉልህ ሆኖ አልታየም። በተመሳሳይ ለሙከራ ቡድኑም በቅድመትምህርት 0.115 የተዛምዶ መጠን በ46 የነፃነት ደረጃ (df) የጉልህነት መጠኑ (0.161) ከ0.05 ስለሚበልጥ፣ በድህረትምህርት 0.121 የተዛምዶ መጠን በ46 የነፃነት ደረጃ (df) የጉልህነት መጠኑ (0.090) ከ0.05 ስለሚበልጥ ጉልህ አለመሆኑን አሳይቷል። ተዛምዶው ጉልህ አለመሆኑም የየቡድኖቹ ቅድመትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቅ ውጤት ወጥ ስርጭት እንዳለው አመላክቷል። በተጨማሪም በተያያዥ አምድ ግራፍ በተደረገው ፍተሻም የውጤቶቹ ስርጭት ወጥነት እንዳለው ታውቋል (አባሪ ተ እና ነ ይመለከቷል)። ይህም በፓራሜትራዊ ቴስት የሆነውን የባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ለመጠቀም አንዱ እሙን እንደተሟላ አሳይቷል።

# ምዕራፍ አራት፤ የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

## 4.1 የጥናቱ ውጤት ትንተና

ከቅድመትምህርትና ከድህረትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተናዎችንና የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቅን በመጠቀም በጥናቱ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ መረጃዎቹም እንደየባህርያቸው ተደራጅተው የጥናቱን ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ እንደሚከተለው በቅደምተከተል ተተንትነዋል፤ በማስከተለም ተብራርተዋል፡፡ በሁሉም ትንታኔዎች ለስታትስቲክሳዊ ስሌቶቹ ፍተሻ የጉልህነት ደረጃ (Level of significance) 0.05 ተመርጧል፡፡

የጥናቱ የመጀመሪያ ጥያቄ **"በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የመጻፍ ክሂልን መማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ያሻሽላል?"** የሚል ነው፡፡ ይህን ጥያቄ ለመመለስ በቅድሚያ የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ ተሳታፊዎች ከሙከራው በፊት ያላቸውን የመጻፍ ችሎታ ደረጃ መለየት አስፈላጊ በመሆኑ በተሰጣቸው ቅድመትምህርት የመጻፍ ፈተና ያመጡት ውጤት እንደሚከተለው በሠንጠረዥ 4.1 ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

***ሠንጠረዥ 4.1 የቡድኖቹ ቅድመትምህርት የመጻፍ ችሎታ አማካይ ንፅፅር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት***

| ቡድን | ናሙና | አማካይ (M) | መደበኛ ልይይት (SD) | የቲ-ዋጋ (t) | የነጻነት ደረጃ(df) | ጉልህነት(በባለሁለት ጫፍ) sig.(2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቁጥጥር | 46 | 21.52 | 4.889 | -517 | 90 | .607 |
| ሙከራ | 46 | 20.98 | 5.192 | | | |

ከሠንጠረዥ 4.1 እንደሚታየው የሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች ልዩነት 0.54 ብቻ በመሆኑ ተቀራራቢ ይመስላሉ፡፡ ከዚህም ሌላ የመደበኛ ልይይት ውጤቶቹ ብዙም የተራራቁ

ባለመሆናቸው የሁለቱም ቡድኖች የመጻፍ ውጤት ከየአማካዮቻቸው ያላቸው ርቀት ተቀራራቢ መሆኑን ያመላከታል፡፡ ይሁንእንጂ የአማካይ ውጤቶቻቸውን በማየት ብቻ በመካከላቸው ስላለው የመጻፍ ችሎታ ልዩነት በእርግጠኝነት መናገር ያስቸግራል፡፡

ልዩነቱን በስታትስቲክስ ከመፈተሹ በፊትም ሁለቱ ቡድኖች በቅድመትምህርት የመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤቶቻቸው የልይይቱ መጠን እኩል መሆን አለመሆኑን በሌቪን የልይይቶች ተመጣጣኝነት መፈተሻ ቴስት (Levene's Test for Equality of Variances) ሲፈተሽ (F =0 .144, Sig<0.05) ተፈትሾ የተገኘው የጉልህነት ደረጃ (0.705) ከ0.05 የበለጠ ሆኖ ታይቷል፡፡ ይህም በቁጥጥር ቡድኑና በሙከራ ቡድኑ ቅድመትምህርት የመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤቶች መካከል እኩል የሆነ የልይይት መጠን እንዳለ ስለሚጠቁም ከስሌቱ ፓራሜትራዊ የሆነው የቲ-ቴስት ዋጋ ተወስዷል፡፡

ይህን ተከትሎም ልዩነታቸውን በስታትስቲክስ ስሌት ማረጋገጥ ተገቢ ስለሆነ በሁለቱ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ መረጃው በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ተሰልቶ፣ ውጤቱ (t(90)=-0.517፣ P=0.607) ሆኗል፤ ይህም በቅድመትምህርት የመጻፍ ችሎታ አኳያ በሁለቱ ቡድኖች አማካዮች መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡

በዚህ መልኩ በቅድመትምህርት የመጻፍ ችሎታቸው የጎላ ልዩነት አለመኖሩ ከታወቀ በኋላ የሙከራ ቡድኑ በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹ፣ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ ያለሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹ በተለመደው መንገድ መጻፍን ሲማሩ ቆይተው ድህረትምህርት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና ተፈትነዋል፡፡ ቡድኖች በድህረትምህርት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተናው ያስመዘገቡት ውጤትም በሠንጠረዥ 4.2 ተነጻጽሮ ቀርቧል፡፡

*ሠንጠረዥ 4.2 የቡድኖቹ ድህረትምህርት የመጻፍ ችሎታ አማካይ ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት*

| ቡድን | ናሙና | አማካይ (M) | መደበኛ ልይይት (SD) | የቲ-ዋጋ (t) | የነጻነት ደረጃ(df) | ጉልህነት(በባለሁለት ጫፍ) sig.(2-tailed) | ኤታ ካሬ ( Eta squared) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቁጥጥር** | 46 | 23.60 | 5.379 | 4.974 | 90 | .000 | 0.22 |
| **ሙከራ** | 46 | 30.03 | 6.932 | | | | |

በሠንጠረዥ 4.2 እንደቀረበው በድህረትምህርት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተናው የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት በ6.43 በልጦ ተገኝቷል፡፡ የመደበኛ ልይይቶች ውጤቶቻቸው ግን ተቀራራቢነት ይታይባቸዋል፡፡ ይህም በሁለቱም ቡድኖች የተመዘገቡት የፈተና ውጤቶች ከየአማካያቸው የተመሳሳይ ርቀት ስርጭት እንዳላቸው ያሳያል፡፡ ሆኖም የአማካይ ውጤቶቻቸውን በማየት ብቻ በመካከላቸው ስላለው የመጻፍ ችሎታ ልዩነት በትክክል መናገር ያስቸግራል፡፡

ልዩነቱን በስታትስቲክስ ለመፈተሽ በቅድሚያ ሁለቱ ቡድኖች የድህረትምህርት የመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤቶቻቸው የልይይቱ መጠን እኩል መሆን አለመሆኑን በሌቪን የልይይቶች ተመጣጣኝነት መፈተሻ ቴስት (Levene’s Test for Equality of Variances) ሲፈተሽ (F =1 .969, Sig<0.05) የተገኘው የጉልህነት ደረጃ (0.164) ከ0.05 የበለጠ ሆኖ ታይቷል፡፡ ይህም በቁጥጥር ቡድኑና በሙከራ ቡድኑ ድህረትምህርት የመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤቶች መካከል እኩል የሆነ የልይይት መጠን እንዳለ ስለሚጠቁም ከስሌቱ ፓራሜትራዊ የሆነው የቲ-ቴስት ዋጋ ተወስዷል፡፡

በማስከተልም ልዩነታቸውን በስታትስቲክስ ስሌት ማረጋገጥ ተገቢ ስለሆነ በሁለቱ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ መረጃው በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ተሰልቶ፣ ውጤቱ (t(90)= 4.974፣ P=0.000) ሆኗል፤ ይህም በቡድኖቹ ድህረትምህርት

የመጻፍ ችሎታ መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት እንዳለ አመላክቷል፡፡ የተጽዕኖ ደረጃውም (effect size) ከፍተኛ ሆኖ (eta squared = 0.22) ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች መጻፍን የተማረው ቡድን ብልሃቱን ሳይጠቀም መጻፍን ከተማረው ቡድን የበለጠ የመጻፍ ችሎታ እንዳለው ያሳያል፡፡

የጥናቱ ሁለተኛ ጥያቄ **“በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የተደገፈ የመጻፍ ክሂል ትምህርት የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ያጎለብታል?”** የሚል ነው፡፡ የጥያቄውን ምላሽ ለማወቅ በቅድሚያ የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ ተሳታፊዎች ከሙከራው በፊት ያላቸውን የመጻፍ ተነሳሽነት ደረጃ ለመለየት የሚያስችል የጽሑፍ መጠይቅ በመጠቀም የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው በሠንጠረዥ 4.3 ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

*ሠንጠረዥ 4.3 የቡድኖቹ ቅድመትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት አማካይ ን ጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት*

| ቡድን | ናሙና | አማካይ (M) | መደበኛ ልይይት (SD) | የቲ-ዋጋ (t) | የነጻነት ደረጃ(df) | ጉልህነት(በባለሁለት ጫፍ) sig.(2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቁጥጥር** | 46 | 68.50 | 21.77 | -.188 | 90 | .851 |
| **ሙከራ** | 46 | 67.61 | 23.58 | | | |

የሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች ልዩነት 0.89 ብቻ በመሆኑ ተቀራራቢነት እንዳላቸው ሠንጠረዥ 4.3 ያሳያል፡፡ ከዚህም ሌላ የመደበኛ ልይይት ውጤቶቹ ብዙም የተራራቁ ባለመሆናቸው የሁለቱም ቡድኖች የመጻፍ ተነሳሽነት ከየአማካዮቻቸው ያላቸው ርቀት ተቀራራቢ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ይሁንእንጂ የአማካይ ውጤቶቻቸውን በማየት ብቻ በመካከላቸው ስላለው የመጻፍ ተነሳሽነት ልዩነት በእርግጠኝነት መናገር ያስቸግራል፡፡

ልዩነቱን በስታትስቲክስ ከመፈተሹ በፊትም ሁለቱ ቡድኖች በቅድመትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት አማካይ ውጤቶቻቸው የልይይቱ መጠን እኩል መሆን አለመሆኑን በሌቪን የልይይቶች ተመጣጣኝነት መፈተሻ ቴስት (Levene's Test for Equality of Variances) ሲፈተሽ (F =0 .437, Sig<0.05) ተፈትሾ የተገኘው የጉልህነት ደረጃ (0.510) ከ0.05 የበለጠ ሆኖ ታይቷል፡፡ ይህም በቁጥጥር ቡድኑና በሙከራ ቡድኑ ቅድመትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት አማካይ ውጤቶች መካከል እኩል የሆነ የልይይት መጠን እንዳለ ስለሚጠቁም ከስሌቱ ፓራሜትራዊ የሆነው የቲ-ቴስት ዋጋ ተወስዷል፡፡

የቡድኖቹ የአማካይ ውጤቶች የልይይት መጠን ተቀራራቢ መሆኑ ከታወቀ በኋላ ልዩነታቸውን በስታትስቲክስ ስሌት ማረጋገጥ ተገቢ ስለሆነ በሁለቱ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ መረጃው በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ተሰልቶ፣ ውጤቱ (t(90)=--0.188 ፣ P = 0.851) ሆኗል፤ ይህም በቅድመትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት አንጻር በሁለቱ ቡድኖች አማካዮች መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡

ሁለቱ ቡድኖች በቅድመትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነታቸው የጎላ ልዩነት አለመኖሩ ከታወቀ በኋላ የሙከራ ቡድኑ በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹ ፣ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ ያለሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹ በተለመደው መንገድ መጻፍን ሲማሩ ቆይተው በድጋሜ ድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቁን ሞልተዋል፡፡ ቡድኖች በድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቁ ያስመዘገቡት ውጤትም በሠንጠረዥ 4.4 ተነጻጽሮ ቀርቧል፡፡

***ሠንጠረዥ 4.4 የቡድኖቹ ድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት አማካይ ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት***

| *ቡድን* | *ናሙና* | *አማካይ* (M) | *መደበኛ ልይይት* (SD) | *የቲ-ዋጋ* (t) | *የነጻነት ደረጃ*(df) | *ጉልህነት(በባለሁለት ጫፍ)* sig.(2-tailed) | *ኤታ ካሬ* Eta squared |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቁጥጥር** | 46 | 72.35 | 20.30 | 2..742 | 90 | .007 | 0.077 |
| *ሙከራ* | 46 | 84.61 | 22.52 | | | | |

በድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቁ ውጤት መሰረት የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት በ12.26 ብልጫ እንዳለው በሠንጠረዥ 4.4 የቀረበው መረጃ ያሳያል፡፡ የመደበኛ ልይይቶች ውጤቶቻቸው ግን ተቀራራቢነት ይታይባቸዋል፡፡ ይህም በሁለቱም ቡድኖች የተመዘገቡት የፈተና ውጤቶች ከየአማካያቸው የተመሳሳይ ርቀት ስርጭት እንዳላቸው ያሳያል፡፡ ሆኖም የአማካይ ውጤቶቻቸውን በማየት ብቻ በመካከላቸው ስላለው የመጻፍ ችሎታ ልዩነት በትክክል መናገር ያስቸግራል፡፡

ልዩነቱን በስታትስቲክስ ከመፈተሹ በፊትም ሁለቱ ቡድኖች በድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት አማካይ ውጤቶቻቸው የልይይቱ መጠን እኩል መሆን አለመሆኑን በሌቪን የልይይቶች ተመጣጣኝነት መፈተሻ ቴስት (Levene’s Test for Equality of Variances) ሲፈተሽ (F =0 .393, Sig<0.05) ተፈትሾ የተገኘው የጉልህነት ደረጃ (0.532) ከ0.05 የበለጠ ሆኖ ታይቷል፡፡ ይህም በቁጥጥር ቡድኑና በሙከራ ቡድኑ ድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት አማካይ ውጤቶች መካከል እኩል የሆነ የልይይት መጠን እንዳለ ስለሚጠቁም ከስሌቱ ፓራሜትራዊ የሆነው የቲ-ቴስት ዋጋ ተወስዷል፡፡

በማስከተልም ልዩነታቸውን በስታትስቲክስ ስሌት ማረጋገጥ ተገቢ ስለሆነ በሁለቱ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ መረጃው በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ተሰልቶ፣ ውጤቱ (t(90)= 2.742 ፣ P=0.007) ሆኗል፤ ይህም በቡድኖቹ ድህረትምህርት የመጻፍ ችሎታ መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት እንዳለ አመላክቷል፡፡ የተጽዕኖ ደረጃውም (effect size) መካከለኛ ሆኖ (eta squared = 0.077) ተገኝቷል፡፡ ይህም የሙከራ ቡድኑ ከፍተኛ ድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት ማግኘቱም የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹን መማር በመጻፍ ተነሳሽነቱ ላይ ጉልህ ተጽዕኖ ማሳደሩን ያመላክታል፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረቡት የጥናቱ ትንታኔዎች በመነሳት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን መሰረት ያደረገ የመጻፍ ክሂል ትምህርትም ተማሪዎች ሀሳብን ከማፍለቅ፣ ከማደራጀትና ከመገምገም ጋር የሚገጥሟቸውን መሰናክሎች ለማቃለል ስለሚያግዛቸው መጻፍን እንደአስቸጋሪ ተግባር

እንዳይቆጥሩት ብሎም ደጋግመው የመጻፍ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ስለሚያደርግ የመጻፍ ችሎታቸው እንዲሻሻል በር ይከፍታል ለማለት ይቻላል፡፡

## 4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት አንዱ አላማ በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የተደገፈ የመጻፍ ክሂል ትምህርት የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማዳበር ያለውን ሚና መፈተሽ ነበር፡፡ ለዚህ አላማ ምላሽ የሰጠው አንደኛው ግኝት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች መጻፍን የተማረው ቡድን ብልሃቱን ሳይጠቀም መጻፍን ከተማረው ቡድን የበለጠ የመጻፍ ችሎታ እንዳለው ያሳያል፡፡ ይህ ልዩነት የተፈጠረው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች በታገዘ ትምህርት የመጻፍ ክሂል እውቀታቸውን መቼና እንዴት አቀናጅተው መጠቀም እንደሚችሉ ተግባራዊ ግንዛቤ በማግኘታቸው ሊሆን ይችላል ቢባልም ተጠየቃዊ ይሆናል፡፡ ከዚህ ውጤት ተነስቶም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ታግዞ መጻፍን መማር በተማሪዎች የመጻፍ ውጤት ላይ ጉልህ የሆነ መሻሻል ያሳያል ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ተማሪዎቹ ተጨባጭ የመረጃዎች የተደራጀ አወቃቀር እንዲፈጥሩ ብሎም ከተነጣጠሉ ሀሳቦች ይልቅ ቁልፍ በሆኑና ጽንሰሃሳባዊ ተዛምዶዎች ባሏቸው ሀሳቦች ላይ አተኩረው እንዲጽፉ (Delrose, 2011) እገዛ በማድረጋቸው ሳይሆን አይቀርም፡፡ ምናልባትም ሌላው ምክንያት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች መረዳትን፣ ማዋቀርንና ትርጉምአዘል መማርን የሚያሳልጡ በመሆናቸው (Janssen, Beissner & Yacci, 1993) የተማሪዎቹን ድካም በመቀነስ ውስብስብ የሆነውን የመጻፍ ተግባር በማሳለጥ በቀላሉ ስራቸውን የማከናወን እድል መፈጠሩ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል፡፡ ተማሪዎቹ ሲጽፉ ሀሳባቸውን እንዲያደራጁና የአስተሳሰብ የፈጠራ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ስለሚረዷቸው (Tracey, 2006) የተሻለ የመጻፍ ትግበራ እንዲያከናውኑ በማገዝ የመጻፍ ችሎታቸውን ለማጎልበት አስተዋጽኦ አድርገውም ሊሆን ይችላል፡፡

ይህ ውጤትም የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን ተጠቅሞ መጻፍን መማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እንደሚያሻሽል ካመላከቱት Ching & Chee (2010)፣ Delarose (2011)፣ Cronin, Barkley, & Sinatra (1992)፣ Meera & Aiswary (2014)፣ Meyer (1995)፣ Miller

(2011) ፣ Sharrock (2008) እና Unzueta (2009) ጥናቶች ውጤት ጋር ተደጋጋፊነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል። ሆኖም ከእነዚህ ጥናቶች የMeyer (1995) እና የSharrock (2008) የመጻፍ ክሂል ጀማሪ በሆኑት በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች በሚገኙ፣ የChing & Chee (2010) ጥናት ደግሞ በሳል የመጻፍ ችሎታ ላይ በደረሱ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በሚገኙ የጥናት ተሳታፊዎች ላይ ተሰርተው የተገኙ ውጤቶች መሆናቸው ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል።

የዚህ ጥናት ውጤት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የተደገፈ ትምህርት የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ አለማሻሻሉን ካሳዩት Blair, Ormsbee, & Brandies (2002) እና Marashi, & Massoodi-Hematabadi (2011) ጥናቶች ውጤት ጋር ደግሞ ተቃርኖ አሳይቷል። ምናልባትም የBlair, Ormsbee, & Brandies (2002) ጥናት ዝግመት ባለባቸው ተማሪዎች ላይ ተለይቶ የተሰራ መሆኑ፣ የMarashi, & Massoodi-Hematabadi (2011) ጥናት ደግሞ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹን ራሳቸው ተማሪዎች እያዋቀሩ ሳይሆን መምህራን አዋቅረው እየሰጡ መማራቸው ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር ተደጋጋፊነት እንዳያሳዩ አድርጓቸው ሊሆን ይችላል።

የጥናቱ ሌላው አላማ በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የታገዘ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ተማሪዎች ለመጻፍ ስራ ያላቸውን ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለውን ሚና መፈተሽ ነበር። ለዚህ አላማ ምላሽ የሰጠው ሁለተኛው ግኝትም በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች መጻፍን የተማረው ቡድን ብልሃቱን ሳይጠቀም መጻፍን ከተማረው ቡድን የበለጠ የመጻፍ ተነሳሽነት እንዳሳየ አመላክቷል። ከዚህ ውጤት ተነስቶም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ታግዞ መጻፍን መማር በተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ውጤት ላይ ጉልህ የሆነ መሻሻል ያሳያል ማለት ይቻላል። ይህ ልዩነት የተፈጠረው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹ ትምህርት የመጻፍ ክሂል እውቀታቸውን መቼና እንዴት አቀናጅተው መጠቀም እንደሚችሉ ባገኙት ተግባራዊ ግንዛቤ በመታገዝ በመጻፍ ሂደቱ ንቁ ተሳታፊ የሚያደርጓቸውን ተግባራት በመከወናቸው ነው ቢባል ምክንያታዊ ይሆናል።

ውጤቱም Hashemian & Heidari (2013) የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ተማሪዎች በመጻፍ ተግባራቸው ላይ በጽናት እንዲቆዩ፣ ለመጻፍ ተግባር እንዲገፋፉ፣ የመጻፍ አቅማቸው ከፍ እንዳለ እንዲሰማቸውና አላማቸውን ለማሳካት ቁርጠኝነት እንዲኖራቸው በማድረግ የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን እንደሚያሻሽሉ ከገለጹበት ሀሳብ ጋር የሚደጋገፍ ይመስላል፡፡ በተጨማሪም መጻፍን በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ተጠቅሞ መማር ተማሪዎች በመጻፍ ችሎታቸው እያሳዩ ያሉትን ለውጥና እድገት ጭምር እየገመገሙ እንዲያልፉ ስለሚያግዙ ትርጉም ያለውና አስደሳች እንደሚያደርገው Marten, Seagraves, Thacker, & Young (2005) የገለጹትን ሀሳብ የሚያጠናክር ሆኗል፡፡ ከዚህም ሌላ Lancaster (2013) የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች በማስተማር ትግበራው መጠቀም ተማሪዎች ለመጻፍ ስራ ፍቅር እንዲያድርባቸው የሚያደርግ የመማሪያ ክፍል አውድ መፍጠሪያ አንዱ መንገድ ሆኖ ስለሚያገለግል ለመጻፍ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው አስተዋጽኦ እንዳለው ካስገነዘበበት ሀሳብ ጋር የተስማማ ነው፡፡ እንዲሁም ውጤቱ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን ተጠቅሞ መጻፍን መማር የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት እንደሚያሻሽል ካመላከቱት የEissa (2012) ፣ Mede (2010) እና Zaini et al. (2010) ጥናቶች ውጤት ጋር ተደጋጋፊነት አሳይቷል፡፡

# ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሀሳቦች

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ታግዞ መጻፍን መማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል የሚኖረውን ሚና መፈተሽ እንደሆነ ቀደም ባሉት ምዕራፎች ተገልጿል። ለዚህም ጥናቱ በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችና በአሁኑ ወቅት በስራ ላይ እየዋለ ባለው የመጻፍ ትምህርት አቀራረቦች ሁለቱ ቡድኖች ከተማሩ በኋላ ለሚከተሉት የምርምሩ መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ የሰጠ ነበር።

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፡-

1. በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የመጻፍ ክሂልን መማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ያሻሽላል?
2. በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የተደገፈ የመጻፍ ክሂል ትምህርት የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ያጎለብታል?

ለጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የጥናቱ ተሳታፊዎች ተመርጠው በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን ተመድበው የተዘጋጀላቸውን ትምህርት ተምረዋል። ከዚህም ሌላ ልዩ ልዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችም ተዘጋጅተው በቅድመትምህርትና በድህረትምህርት መረጃዎች ተሰብስበው ትንታኔና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።

ጥናቱ በአይነቱ መጠናዊ፣ በንድፍ ደግሞ ፍትነት መሰል የጥናት ንድፍን በመከተል ተከናውኗል። የጥናቱ ተሳታፊዎች ደግሞ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን በሚገኘው በአጣዬ ከተማ የከፍተኛ መሰናዶ ትምህርትና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት በ2010 ዓ.ም በዘጠነኛ ክፍል ተመዝግበው በ17 የመማሪያ ክፍሎች ሲማሩ ከነበሩት ወንድ 503፣ ሴት 512 በድምሩ 1015 ተማሪዎች ውስጥ በተራ እጣ ንሞና ዘዴ የተለዩት 9ኛ B እና C ተማሪዎች ነበሩ። ቅድመትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና እንዲፈተኑ ከተደረገ በኋላ በመጻፍ ችሎታቸው ያላቸው ተመጣጣኝነት ከታወቀ በኋላም ለሁለቱ መማሪያ ክፍሎች እጣ በመምታት 9ኛ B የሙከራ ቡድን፣ 9ኛ C ደግሞ የቁጥጥር ቡድን መሆናቸው ተለይቷል። በመሆኑም በ9ኛ B ውስጥ የተገኙት ወንድ 20፣ ሴት 26 በድምሩ 46 ተማሪዎች በሙከራ ቡድኑ የተሳተፉ ሲሆን፣ በ9ኛ C ውስጥ የተገኙት ወንድ 22፣ ሴት 24 በድምሩ 46 ተማሪዎች በቁጥጥር ቡድኑ ተሳትፈዋል።

ሁለቱ ቡድኖች የተዘጋጀላቸውን የመጻፍ ትምህርት በትምህርትቤቱ በማስተማር ላይ በምትገኘው በአጥኚዋ በ8 ሳምንታት ውስጥ ለ17 ክፍለጊዜያት መጻፍን ተምረዋል፡፡ በዚህ ሂደትም የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በተዘጋጁላቸው የመማሪያ ተግባራት ዋናና ደጋፊ ሀሳቦችን፤ የምክንያትና ውጤት፣ የማወዳደርና ማነጻጸር፣ የቅደምተከተል ተዛምዶዎች የሚታዩባቸውን ሀሳቦች እየለዩ በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች በመታገዝ ሀሳባቸውን በማስፋፈት ጽሁፋቸውን አሟልተው እንዲጽፉ ተደርጓል፡፡ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹንም ለምን፣ መቼና እንዴት እንደሚጠቀሙባቸው በግልጽ ተምረዋል፤ በብልሃቶቹ ትግበራ ወቅት የሚገጥሟቸውን ችግሮች እንዴት መፍታት እንደቻሉ የሚያንጸባርቁበት እድል በሚሰጥ የማስተማር ትግበራ ውስጥ አልፈዋል፡፡ በተለመደው አቀራረብ የመጻፍ ክሂልን ለተማረው የቁጥጥር ቡድን ደግሞ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ትምህርት ሚኒስተር በ2004 ዓ.ም አሻሽሎ ባዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በሚገኙ የመጻፍ ክሂል መልመጃዎች ማለትም በአረፍተነገሮች ውስጥ የተጓደሉ ቃላትንና ሀረጋትን ማሟላትናየተደራጀ ሀሳብ የያዘ አንቀጽ መጻፍ፣ ከምንባብ የወጡ አረፍተነገሮችን በራሳቸው አባባል ቀይረው መጻፍ በተሰጣቸው ርዕስ አሰረጂ ድርሰት መጻፍ፣ አካባቢያቸውን የሚያስረዳ ገላጭ ጽሁፍ መጻፍ፣ ከተሰጡ ርዕሶች አንዱን መርጠው አንቀጽ መጻፍ፣ የምንባብን ሀሳብ አሳጥሮ መጻፍ፣ ስርዓተነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው አስገብተው መጻፍ፣ የመንስኤና ውጤት ትስስርን የሚያሳዩ አረፍተነገሮችን መጻፍ ተለማምደዋል፡፡ በመሆኑም የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን እውቀትንም ሆነ የሀሳብ ማደራጃ ብልሃቶችን የሚያስተዋውቁ የማስተማር ትግበራ አልቀረበላቸውም፡፡

የቅድመትምህርትና የድህረትምህርት የመጻፍ ችሎታ በፈተና፣ የመጻፍ ተነሳሽነት በጽሁፍ በመጠይቅ ተሰብስቧል፡፡ ለቅድመትምህርትና ለድህረትምህርት የቀረበው ፈተና አንድ ሲሆን በአረፍተነገሮች ውስጥ የሚታዩ አላስፈላጊ ድግግሞሾችን በማስወገድ በራስ አባባል እንደገና መጻፍ፣ የተዘበራረቁ አረፍተነገሮችን ቅደምተከተል በማስተካከል ገላጭ አንቀጽን መጻፍ፣ በአንድ ርዕስ መንደርደሪያ አረፍተነገርን በመመስረት የሀሳብ ዝምድናቸውን የጠበቁ፣ ከዋናው ሀሳብ ያላፈነገጡ፣ ሰዋስዋዊ ስህተቶች የሌሉባቸውና ተገቢ የስርዓተነጥቦች አጠቃቀም በሚታይባቸው አረፍተነገሮች የምክንያትና ውጤት ትስስርን የሚያሳይ አንቀጽ መገንባትን፣ በሌላ አንድ ርዕስ ደግሞ ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት እንድጽፉ የሚጠይቅ ነበር፡፡ ፈተናው በዚህ መልኩ ከመቅረቡ በፊት በአጥኚዋ ተዘጋጅቶ በባለሙያዎች አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡ ከዚህም

ሌላ ቅድመጥናት (pilot study) ፍተሻ በማካሄድ በተገኙ መረጃዎች መነሻም አስፈላጊውን ማሻሻያ በማድረግ ለዋናው ጥናት ውሏል። ፈተናው በዋናው ጥናት ወቅትም የእያንዳንዱ የጥናቱ ተሳታፊ መልስ በሶስት ኮፒ በማባዛት  በሶስት አራሚዎች ታርሞ የአራሚዘለል አስተማማኝነቱ (inter-rater reliability) በክሮንባኽ አልፋ (Cronbach Alpha) ቀመር ተፈትሾ በቅድመትምህርት α= .981፣ በድህረትምህርት α= .994 የአስተማማኝነት ውጤት ተገኝቷል።

የመጻፍ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቅ ሌላው የዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ነበር። መጠይቁ Payne (2012) ለተመሳሳይ ተግባራት የተጠቀሙበትን በአጥኚዋ ወደአማርኛ ቋንቋ ተተርጉሞ የተዘጋጀ ነበር። ይህ መጠይቅ 37 ጥያቄዎች ያሉት ሲሆን በቅድመጥናት (pilot study) ደረጃ ከዋናው ጥናት ተሳታፊዎች ጋር ተመሳሳይ ሁኔታ ላላቸው 30 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ቀርቦ አስተማማኝነቱ በክሮንባኽ አልፋ (Cronbach Alpha -α) ቀመር ተፈትሾ α=0.909 አስተማማኝነት መጠን ተገኝቷል። ስሌቱንም ተከትሎ አንድም ጥያቄ ሳይቀነስ በአንዳንድ ጥያቄዎች ላይ ብቻ መጠነኛ የቃላትና ሀረጋት ማሻሻያ ተደርጎበት ለዋናው ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያነት ውሏል። በዋናው ጥናት ወቅትም በሁለቱ ቡድኖች ከተሳተፉ 92 ተማሪዎች በዚሁ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ አስተማማኝነት በድጋሜ በክሮንባኽ አልፋ ቀመር ሲፈተሽ በቅድመትምህርት ደረጃ α= 0.930፣ በድህረትምህርት ደረጃ α= 0.912 መገኘቱ አስተማማኝነቱ ከፍተኛ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

ከላይ በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች የቅድመትምህርትና የድህረትምህርት መረጃዎች ከተሳታፊዎች ከተሰበሰቡ በኋላ የመረጃዎቹን የስርጭት ወጥነታቸው በስርጭት ወጥነት መፈተሻ ቀመር ተሰልቷል። ከዚያም በጥናቱ እንደተነሱት የምርምር ጥያቄዎች እየታዩ በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክሶች ተተንትነው የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል።

መረጃዎቹ ከተተነተኑ በኋላም በጥናቱ የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል። በመጀመሪያ በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችና በተዘውታሪው የመጻፍ ትምህርት አቀራረቦች የተማሩት ተማሪዎች በድህረትምህርት የመጻፍ ችሎታ ውጤታቸው ጉልህ ልዩነት ማሳየት አለማሳየታቸው በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲፈተሽ ጉልህ ($p$ = .000) ልዩነት ታይቶባቸዋል። የተጽዕኖ ደረጃውም

(effect size) ከፍተኛ (eta squared = 0.22) ሆኖ ተገኝቷል። በዚህም መሰረት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የመጻፍ ክሂልን መማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እንደሚያሻሽል ለማወቅ ተችሏል።

ከዚህም ሌላ በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችና በተዘውታሪው የመጻፍ ትምህርት አቀራረቦች የተማሩት ተማሪዎች በድህረትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት ውጤታቸው ጉልህ ልዩነት ማሳየት አለማሳየታቸው በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲፈተሽ ጉልህ ($p$ = .007) ልዩነት ታይቶባቸዋል። የተጽዕኖ ደረጃውም (effect size) መካከለኛ (eta squared = 0.077) መሆኑ ታውቋል። በመሆኑም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች የመጻፍ ክሂልን መማር የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት እንደሚያጎለብት ለማወቅ ተችሏል።

## 5.2 መደምደሚያ

በጥናቱ መነሻ ችግር ላይ እንደተገለጸው በርካታ ቁጥር ያላቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ተማሪዎች ሀሳባቸውን የማመንጨት፣ የማደራጀት ብሎም በአግባቡ የተደረጀ ጽሁፍ የመጻፍ ችግር ይታይባቸዋል። እንድሁም ብዙዎቹ ተማሪዎች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመከለስ፣ በአርትዖት የመጻፍ ሂደት ደረጃዎች ሁሉ በርካታ ችግሮች ይገጥሟቸዋል። ከመጻፍ ችሎታቸው ማነስ ጋር ተያይዘው በሚገጥሟቸው እንቅፋቶች የተነሳም የመጻፍ ተነሳሽነት ያንሳቸዋል። እነዚህን ችግር ለማቅለል ከሚያስችሉ መንገዶች መካከል አንዱ ትምህርቱን በብልሀት የታገዘ አድርጎ ማቅረብ ነው። ከእነዚህ አቀራረቦች መካከል ደግሞ የመጻፍ ትምህርትን በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች አማካይነት ማቅረብ ተጠቃሽ ነው። ምክንያቱም የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን ተጠቅሞ መጻፍን መማር ውስብስብና አስቸጋሪ የሆነውን የመጻፍ ተግባር በማቅለል የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት በማጎልበት ረገድ ጉልህና አወንታዊ ለውጥ ማምጣት ችሏል።

በመሆኑም የጥናቱን ውጤት ትንተናና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል።

1. በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታና በሃሳብ ማደራጃ ቢጋሮች መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት አለ፡፡ይህም ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል እውቀታቸውን መቼና እንዴት አቀናጅተው መጠቀም እንደሚችሉ ተግባራዊ ልምምድ በሚያደርጉበት ሁኔታ በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች መማራቸው የመጻፍ ችሎታቸውን በጉልህ ደረጃ ያሻሽላል፡፡
2. ከዚህ በተጨማሪ በሃሳብ ማደራጃ ቢጋሮችና በመጻፍ ተነሳሽነት መካከል አዎንታዊ ግንኙነት አለ፡፡ የመጻፍ ክሂል እውቀታቸውን መቼና እንዴት አቀናጅተው በመጻፍ ሂደታቸው ውስጥ መጠቀም እንደሚችሉ ተግባራዊ ግንዛቤ አግኝተው ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ በሚያግዙ ሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች አማካኝነት መማራቸው የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን ያጎለብታል፡፡

## 5.3 የመፍትሄ ሀሳቦች

የመጻፍ ስራ ሀሳቦችን የማፍለቅ፣ የመምረጥ፣ የማደራጀትና እንደየዝምድናቸው የማስተሳሰር ስራን ስለሚጠይቅ ለመማር ውስብስብና አስቸካሪ ነው፡፡ በተለይም ተማሪዎች በህይወት ዘመናቸው ሁሉ የሚጽፉባቸውን ርዕሰጉዳዮች ሁሉ በክፍል ውስጥ ትምህርት አቅርቦ በማስተማር መጨረስ አይቻልም፡፡ ይሁን እንጂ የተለያዩ ርዕሰጉዳዮችን አስመልክቶ በመጻፍ ሂደት ሀሳብን የማፈላለግ፣ የማፍለቅ፣ የመምረጥና የማደራጀት ተግባራትን እንዴት መከወን እንደሚችሉ ብልሃቶችን ማስተማርና ማለማመድ ይቻላል፡፡ መለማመድና መማር ከሚገባቸው ብልሃቶች ውስጥም በዚህ ጥናት የተፈተሹት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ መሻሻልን እንደሚያመጡ ግኝቶቹ አመላክተዋል፡፡
የዚህን ጥናት ግኝቶች ተግባራዊ ለማድረግ ብሎም የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት ለማሻሻል የሚከተሉት ስነትምህርታዊ መፍትሄዎችና ተጨማሪ የምርምር አቅጣጫዎች ተጠቁመዋል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመጻፍ ክሂል የማስተማር ዘዴዎቻቸው ውስጥ ተማሪዎቹ እንደሚጽፉባቸው ርዕሰ ጉዳዮች ባህርያት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን ተጠቅመው ሀሳቦቻቸውን በቃላትና በምስል አቀናጅተው የሚያፈልቁበትን እድል ቢፈጥሩ የመጻፍ ችሎታቸው እንድሻሻል

እገዛ ማድረግ ይችላሉ። በተለይም በመጻፍ ክሂል በመማር ሂደት ውስጥ የተለያየ የአደረጃጀት ባህርይ ላላቸው ሀሳቦች የሚስማሙ ስዕላዊ የሀሳብ ማዋቀሪያዎችን ከቁልፍ ሀሳቦች ጋር አቀናጅተው ቢያስተምሩና ቢያለማምዱ ተማሪዎቹ ከመጻፍ ስራ ጋር ተያይዞ የሚገጥማቸውን እንቅፋት በመቀነስ የመጻፍ ተነሳሽነታቸው ሊዳብር ይችላል።

የአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተትምህርት ባለሙያዎችና የመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች የመጻፍ ክሂል ማለማመጃ ርዕሰ ጉዳዮችን ሲመርጡና ተግባራትን ሲያዘጋጁ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮችን እንደአንድ የመጻፍ ተግባራት ማቅረቢያ መንገድ ቢጠቀሙበት የተማሪዎችን የመጻፍ ችግር ሊቀንስ፣ የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን ሊያሻሽል ይችላል።

ከላይ የተጠቀሱት ስነትምህርታዊ መፍትሄዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጥናቱ ግኝቶች ከዚህ የሰፋ አንድምታ ይኖራቸው ዘንድ በሚከተሉት ጉዳዮች ዙሪያ ተጨማሪ ጥናቶች መደረግ ይኖርባቸዋል። በዚህ ጥናት ለትምህርት የቀረቡት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች አራቱ ብቻ በመሆናቸው በጥናቱ ውጤት ላይ የራሱ ውስንነት ስለሚኖረው በሌሎች የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሮች ላይ ጭምር ተመሳሳይ ጥናት ቢደረግ ስለብልሃቶቹ ሚና ያለውን ግንዛቤ ማስፋት ያስችላል። ከዚህም ሌላ የዚህ ጥናት ውጤት በአንድ የክፍል ደረጃ በውስን የመማሪያ ክፍሎች ብቻ ተተግብሮ የተገኘ ከመሆኑ አኳያ ውስንነት ስለሚኖረው ሌሎች ተመራማሪዎች በሌሎች የክፍል ደረጃዎችና በርከት ባሉ የጥናት ተሳታፊዎች ረዘም ላለ ጊዜ ተመሳሳይ የአጠናን ዘዴን ተከትለው ተጨማሪ ጥናት ቢያደርጉ ብልሃቶቹ በመጻፍ ክሂል ትምህርት ውስጥ እየገጠሙ ያሉ በብቃትና ለደረጃው በሚመጥን መልኩ መጻፍ ያለመቻልን፣ የመጻፍ ተነሳሽነት ማጣትን የሚመለከቱ ችግሮችን ከማቃለል አኳያ ያላቸውን ሚና በጥልቀት ማወቅ ያስችላል።

# ዋቢዎች


ማረው አለሙ። (1996 ዓ.ም)። *የበሳል ድርሰት ማስተማሪያ።* አዲስ አበባ። ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ድርጅት ።

ባዬ ይማም። (2000 ዓ.ም)።*ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋሰው።* አዲስ አበባ ። አልፋ አሳታሚዎች ።

ትምህርት ሚኒስቴር። (2004)። *አማርኛ የተማሪው መጽሐፍ 9ኛ ክፍል* ፤ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

እንድሪስ ዓባይ።(2009 ዓ.ም)። "በቴክስት ውቅር ብልሃቶች በአማርኛ ማንበብን መማር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ተፅዕኖ- በስድስተኛ ክፍል ተተኳሪነት።" ያልታተመ የፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ጥናት ትምህርት ቤት፣አዲስ አበባ።

Anggrainy, S.,Diem, C. D., Vianty, M. & Sugandi, B. (2016).The effect of graphic organizers, guided writing strategies, and reading levels on the writing achievement of the fourth semester students of pgmi program at iain raden intan lampung. *Proceedings of the 2nd SULE — IC FKIP, Unsri, Palembang October 7th — 9th.*

Baxendell, B. (2003). Consistent, coherent, creative: The 3Cs of graphic organizers. *Council for Exceptional Children*, 36(3), 46-53. *10.1177/004005990303500307*

Bishop, A.(2013).*The effects of a graphic organizer training package on the persuasive writing of middle school students with autism.*(Unpublished Master's thesis). Ohio State University

Blair, R. Ormsbee, C., & Brandes, J. (2002).*Using writing strategies and visual thinking software to enhance written performance of students with mild disabilities.*ERIC EBS co hast. Retrieved from http://www.eric.ed.gov.

Boscolo, P., Favero L.D. and Borghetto, M.(2007). Writing on an interesting topic: Does writing foster interest? In P. Boscolo, and S.Hidi (Eds.). *Writing and motivation* (73-92). Oxford: Elsevier Ltd.

Brown, M. (2011). *Effects of graphic organizers on students' achievement in writing process.* Retrieved from ERIC database(ED 527).

Calkin, L. (1994). *The art of teaching writing (new Ed.).*Portsmouth, NH, Heinemann.

Capretz, K., Ricker, B. & Sasak, A. (2003).*Improving organizational skill through use of graphic organizers.* Retrieved from ERIC database (ED473 056).

Delrose, L. (2011). *Investigating the use of graphic organizers for writing* (Unpublished doctoral dissertation).Louisiana State University.

Chen, B., Hirumi, A. & Zhang, N. J. (2007). Investigating the use of advance organizers as an instructional strategy for web-based distance education. *Quarterly Review of Distance Education,* 8 (3), 223-231 Retrieved October 28, 2017 from https://www. learntechlib. org/ p/106648/.

Cheng, Y. S. (2002). Factors associated with foreign language writing anxiety. *Foreignlanguage annals*, 35(6), 647-656.

Ching, L. & Chee, T. (2010). Scaffolding writing using feedback in students' graphic organizers: Novice writers' relevance of idea and cognitive load. *Educational Media International*, 47(2),135-152.

Chohan, S. (2011).Any letter for me?Relationship between an elementary school letter writing program and students' attitudes, literacy achievement and friendship culture.*Early Childhood Education* 39(1), 39-50.

Cronin, H.; Sinatra, R. & Barkley, W. (1992).Combining writing with text organization in content instruction*. NASSP Bulletin 25.*doi:10.1177/019263659 207654207

Curriculum Development Institute. (2001). *The use of graphic organizers to enhance thinking skills in the learning of economics*. Hong Kong: Education Dept. https://books. google. com/.

Delrose, L. (2011). *Investigating the use of graphic organizers for writing* (Unpublished doctoral dissertation).Louisiana State University.

Eissa, M. A. (2012). The effects of advance graphic organizers strategy intervention on academic achievement, self efficacy, and motivation to

learn social studies in learning disabled second year prep students. *International Journal of Psycho-Educational Sciences*,1(1), 13-26.

Ellis, E. (2004). *Q&A: What's the big deal with graphic organizers*?. Retrieved from http://www.graphicorganizers.com/Sara/ArticlesAbout/Q&A%20Graphic %20Organizers.pd

Emerson, K. (2010). *Graphic Organizers and WritingPerformance: Improving Undergraduate Competence Using Action Research in a Workplace Internship*. Work Based Learning e-Journal, 2, 1. Retrieved on October, 20 2012 from http://wblearningejournal.com

Flower, L., and Hayes, J. R. (1981) A cognitive process theory of writing.*College English* 44, 765-777.

Griffin, C. & Tulbert, B. (1995). The effect of graphic organizers on students' comprehension and recall of expository text: A review of the research and implications for practice. *Reading and Writing Quarterly*, 11, 73-89.doi: 10.1080/1057356950110106

Hall, T. & Strangman, N. (2008).*Graphic organizers*. Wakefield MA: National Center on Assessing the General Curriculum.

Harrington, M., Holik, M., & Hurt, P. (1998). *Improving writing through the use of varied strategies* Retrieved from ERIC database (ED420874).

Hashemian, M., & Heidari, A. (2013). The relationship between L2 learners' motivation/attitude and success in L2 writing. *Procedia-Social and Behavioral Sciences*, *70*, 476-489.

Herdi, A. and Yasin, H.S. (2014). Improving students' writing skill by using graphic organizer at the second year students English education department faculty of education and teachers training lancang kuning universitypekanbaru. *Journal English Language Teaching (ELT)* 2, (2), 43-58.

Higgins, P. D. (2012) *The effects of using a critical thinking graphic organizer to improve connecticut academic performance test interdisciplinary writing*

*assessment scores*. (Unpublished doctoral dissertation),Western Connecticut State University.

Hoey, M.(1983). *On the surface of discourse*. London: Allen and Unwin.

Hyland, K. (2009). *Teaching and researching writing* (2nd Ed.). London: Pearson Education.

Kansızoğlu, H.B. (2017). The Effect of Graphic Organizers on Language Teaching and Learning Areas: A Meta-Analysis Study. *Education and Science,* 42 (191), 139-164.

Lancaster, K. (2013). *An examination of using graphic organizers to teach writing: A case study.* ELE 5900.Eastern Illinois University.

Lee, C. C. &Tan, S. C.(2010). Scaffolding writing using feedback in students' graphic organizers novice writers' relevance of ideas and cognitive loads. *Educational Media International*, 47 (2), 135-152. doi:10.1080/ 09523987. 2010. 492678

Lin, S. Strickland; M. Ray, M. & Denner, G. (2004).Computer-based concept mapping as a prewriting strategy to middle school students*. Meridian 7.* Retrieved *March* 13 .*2006 from http//www ncsu. edu./ Meridian /sum/2004cbc*

Lorbre, M. (2004).*Instructional computer technology and student learning: An investigation into using inspiration software to improve eighth grade students' ability to write* (Unpublished doctoral dissertation), Fielding Graduate Institute.

Marashi, H. & Massoodi-Hematabadi, S. (2011). Using teacher- and student-developed graphic organizers as a writing tool. *Journal of language and translation,* 2(1),79-88.

Marten, L. Seagraves, R. Thacker, S. & Young L. (2005). The writing process: Three first grade teachers and their students reflect on what was learned. *Reading Psychology*,26,235-249.

Meyer, D. J. (1995). *The Effects of Graphic Organizers on the Creative Writing of Third Grade Students* (Unpublished MA thesis),Kean College of New Jersey

Mayer, R. E. (1979). Twenty years of research on advance organizers: assimilation theory is still the best predictor of results. *Instructional Science,* 8, 133-167

Mayer, R. E. (1997). Multimedia learning: Are we asking the right questions?. *Educational Psychologist*, 32(1),1-19. doi:10.1207/s15326985ep3201_1 .

Mede, E. ( 2010). The effects of instruction of graphic organizers in terms of students' attitudes towards reading in English. *Procedia Social and Behavioral Sciences* 2, 322—325.

Meera, P. & Aiswarya, K. (2014).A study on the effectiveness of graphic organizers in the writing skill of English among secondary school students.*w.w.w. scholar world. net*. 2 (4),.

Miller, S. (2011). *Using graphic organizers to increase writing performance* ((Unpublished Master's Thesis), State University of New York at Fredonia Fredonia, New York.

Mohammadia, M.; Moenikiab, M. & Zahed-Babelanc, A.(2010). The role of advance organizer on English language learning as a second language. *Procedia Social and Behavioral Sciences* 2, 4667—4671. www.science direct.com

Nik, Y.,Hanzah, A.& Rafidee,H.(2010).Acomparative study on factors affecting the writing performace among Bchelor students. *International Journal of Educational Research & Technology*, 1(1),54-59.

Ojima, M. (2006). Concept mapping as pre-task planning: A case study of three Japanese ESL writers. *System,* 34, 566—585.

Paivio, A. (1986). *Mental representations: A dual coding approach*. Oxford: Oxford University Press, Inc.

Pajares, F.(1996). Self-efficacy beliefs in academic settings. *Review of Educational Research,* 66, 543-578.

Pajares, F. (2003). Self-efficacy beliefs, motivation, and achievement in writing: A review of the literature. *Reading & Writing Quarterly,* 19, 139- 158. Doi: 10.1080/10573560390143085

Parker, S. (2012) *The write way: graphic organizers and responses to literature writing* (Unpublished MA thesis) .California State University, Sacramento

Payne, A. R.(2012). *Development of the academic writing motivation questionnaire*. (Unpublished MA thesis), University of Georgia

Pratama.R.(2014/2015 )improving student writing skill using mind mapping technique (aclssroom action research on the seventh grade of smp n 2 gondangrejo, karanganyar in the school Unpublished MA thesis in Education.California State University, Sacramento.

Richard , J.C.(2003). *Second language writing*. Cambrige: Cambrige University press.

Sharrock, T. (2008).*The effect of graphic organizer on students' writing*: Action Research. Kennesaw State University.

Strangman, N., Vue, G., Hall, T., & Meyer A. (2004). *Graphic Organizers and Implications for Universal Design for Learning: Curriculum Enhancement Report*. Wakefield, MA: National Center on Accessing the General Curriculum. (Links updated 2014). Retrieved [insert date] from http://aem.cast.org/about/publications/2003/ncac-graphic-organizers-udl.html

Sturm, J. M. & Rankin-Erickson, J. L. (2002). Effects of hand-drawn and computer-generated concept mapping on the expository writing of middle school students with learning disabilities. *Learning Disabilities Research & Practice,* 17(2), 124—139.

Tracey, D.M.(2006). *Lenses on reading: an introduction to theories and models*. NewYork: Guilford press.

Unzeta, C. (2009). *The use of computer graphic organizer for persuasive composition writing* (Unpublished Dissertation).Florida International University

Usó-Juan, E, Martínez-Flor, A. and Palmer-Silveira, J. C. (2006). Towards acquiring communicative competence through writing. In Esther U and Alicia M.(Eds.). *Current trends in the development and teaching of the four language skills* (383-400).Berlin: Walter de Gruyter GmbH & Co.

Winter, E. O.(1977). A clause relational approach to English texts: A study of some predictive lexical items in written discourse. *Instructional Science,* 6(1), 1-92.

Young. L. (2005). The writing process: Three first grade teachers and their students reflect on What was learned. *Reading Psychology*. 26: 235-249.

Zaini, S.H., Mokhtar, S.Z. & Nawawi, M. (2010). The Effect of Graphic Organizer on Students' learning in school. *Malaysian Journal of Educational Technology*, 10(1), 17-23

□□□□□

□□□ □. □□□□ □□□ □□□□ □□□□□□

# ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ

# ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

# የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)እና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

## ክፍለትምህርት አንድ

## በቅደምተከተላዊ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር መነሻ መጻፍ

### I. ታላሚውን የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ማስተዋወቅ

1. ቅደምተከተላዊ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ምንድን ነው?

ቅደምተከተላዊ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ድርጊቶች፣ መረጃዎች ወይም ሁነቶች በሚከሰቱባቸው ቅደምተከተሎች አንጻር ሀሳቦችን ለማዋቀር የሚያስችል የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር አይነት ነው፡፡ ከዚህም ሌላ አንድን ነገር ወይም ድርጊት ለመስራት ወይም ለማከናወን መከተል የሚገባንን ደረጃዎች የሚገልጽን ጽሁፍ ማዋቀር ያስችለናል፡፡ ድርጊቶች፣ ሁነቶችና ሀሳቦች በጊዜ፣ በቦታ ወይም በድርጊት ቅደምተከተል የሚብራሩበት ነው፡፡ በዚህ አወቃቀር በአመዛኙ የጽሁፉ ዋና ዋና ሀሳቦች ከቀረቡት ቅደምተከተላዊ ደረጃዎች ወይም ታሪኮች ጋር ይያያዛሉ፡፡ እንደምግብ አዘገጃጀት፣ ግለታሪኮች፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎች፣ የነገሮች አሰራር፣ የተግባር ማሻሻያዎች፣ወዘተ ያሉት የሚከተሏቸውን የክዋኔ ሂደቶች በጽሁፍ ለማቅረብ አዘውትሮ በስራ ላይ ይውላል፡፡

2. ለቅደምተከተላዊ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋርን ተጠቅመን ሀሳባችንን በጽሁፍ ለማስፋፋት የሚያግዙን ቃላት ወይም ሀረጋት እነማን ናቸው?

ውቅር ጠቋሚ ቃላት ወይም ሀረጋት የሚባሉት አንድን አንቀጽ ወይም ጽሁፍ በምንጽፍበት ጊዜ ሀሳቡ እንዴት እንደሚዋቀር ለማሳየት የሚያግዙን የሀሳብ ማሸጋገሪያ ወይም ማገጣጠሚያዎች ናቸው፡፡ የቅደምተከተላዊ የሀሳብ ማደራጃ ቃላት ወይም ሀረጋትም በአንድ

አንቀጽ ወይም በጠቅላላ በጽሁፉ ውስጥ ነገሮች፣ ድርጊቶች፣ ሁነቶች፣ ወዘተ የተፈጸሙበትን ሂደት፣ጊዜ፣ወዘተ በቅደምተከተል ለመግለጽ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ የትኛው ነገር ወይም ድርጊት ወይም ሁነት ከየትኛው ቀድሞ ወይም ተከትሎ እንደተከናወነ፣ እንደመጣ፣ እንደተገኘ፣ ወዘተ. ማመላከት ሁነኛ ዓላማቸው ነው፡፡

ጸሃፊዎች አዘውትረው ከሚጠቀሙባቸው **ቅደምተከተላዊ የሀሳብ ዝምድናን ጠቋሚ ቃላት ወይም ሀረጋት** መካከል ቀጥሎ የተዘረዘሩት ይገኙበታል፡፡

አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት…፣ አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ቀጥሎ፣ ከዚያ፣ በፊት፣ በኋላ፣ በመጨረሻ፣ የሚቀጥል፣ የሚከተለው፣ ብዙም ሳይቆይ፣ አሁን፣ በቅርብ ጊዜ፣ ቀደም ብሎ፣ የኋላ ኋላ፣ የፊተኛው፣ የኋለኛው፣ ቀጣዩ፣ ከዚያ በኋላ፣ ከመጀመሪያው፣ በቅድሚያ፣ በማስከተል፣ ከአጭር ጊዜ በኋላ፣ ደረጃዎች፣ በተከታታይ፣ ከ…በፊት፣ ከ…በኋላ፣ ወዘተ.

## II. የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በምሪት ማለማመድ

**"በፈተና ውጤታማ ለመሆን መደረግ ያለባቸው ተግባራት"** በሚል ርዕስ ድርሰት እንድጽፍ ታዝዣለሁ እንበል፡፡ በመጀመሪያ ርዕሱን በሦስት የሂደት ደረጃዎች ከፋፍየ በቅደምተከተል ሀሳቦችን ማቅረብ እንደምችል ወሰንኩ፡፡ ስለርዕሱ የማውቀውን ራሴን በመጠየቅ በአዕምሮዬ የማስታውሰውን ሀሳብ ሁሉ በሦስቱ ደረጃዎች ውስጥ እጽፋለሁ፡፡ በዚህ ወቅት ወደአዕምሮዬ የመጣን ሀሳብ ሁሉ ሳልመርጥ አሰፍራለሁ፡፡ ለመነሻ ይሆኑኝ ዘንድ መጀመሪያ የተወሰኑ የማውቃቸውን ሀሳቦች ከታች በሚታየው የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ላይ ጻፍኩ፡፡ ድርሰቱን ለመጻፍ የሀሳብ ማዋቀሪያ ቢጋሩ ላይ ሌሎች ተመሳሳይ ሀሳቦችን መጨመር እችላለሁ፡፡ በተቻለኝ መጠን ሀሳቦች እንደየተዛምዷቸው በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ላይ ለማስፈር ሞክሬያለሁ፡፡ በመቀጠል በሦስቱ ደረጃዎቸ ስር ያሉ ሀሳቦችን ባላቸው ቅደምተከተል መሰረት እያዋቀርኩ ረቂቁን ለመጻፍ ሙከራ አደረግኩ፡፡




አሁንም በአዕምሮ ጨመቃ ወቅት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ዙሪያ ያሰፈርኳቸውን ሀሳቦች በማመዛዘን የትኛው ቀድሞ፣ የትኛው ደግሞ ተከትሎ የሚመጣ እንደሆነ እየለየሁ ረቂቄን በመጻፍ ላይ ነኝ፡፡ በዚህ ሂደት የሀሳቦቼን ቅደምተከተል ለማሳየት ቅደምተከተላዊ የሀሳብ ዝምድና ጠቋሚ ቃላትንና ሀረጋትን እየመረጥኩ እየተጠቀምኩ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ረቂቄን አዘጋጅቼ ጨረስኩ፡፡ ረቂቄን መላልሼ በማንበብ ካረምኩ በኋላ የሚከተለውን ጽሁፍ መጻፍ ቻልኩ፡፡

**በፈተና ውጤታማ ለመሆን መደረግ ያለባቸው ተግባራት**

በፈተና ላይ ውጤታማ ለመሆን መደረግ ያለባቸው ተግባራት **በጊዜ ቅደምተከተል** በሶስት ይከፈላሉ፡፡ **የመጀመሪያው ደረጃ** በቅድመፈተና መደረግ ያለባቸውን ተግባራት ይመለከታል፡፡ በቅድመፈተና ሂደት **በቅድሚያ** የፈተናው ጊዜ ከመድረሱ በፊት እያንዳንዱን የትምህርት ክፍል ወይም ምዕራፍ በጥልቀትና በእርጋታ ማጥናት ነው፡፡ **ሌላው ተግባር** በአጥጋቢ ውጤት ለማለፍ የሚደረገውን ጥናት አስተማማኝና ፈተናውን መሰረት ያደረገ መሆኑን በደንብ ማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ ወቅት የፈተናው ጊዜ በጣም ሲቀርብ የሚነበቡ አጫጭር ማስታወሻዎችን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህ ማስታወሻዎች በጣም ያልተንዛዙ ነገርግን የትምህርቱን ፍሬሃሳብ ለይተው የያዙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ **በፈተናው ዋዜማ** በጊዜ በመተኛት አዕምሮ በትክክል እንዲሰራ እረፍት ማድረግም የማይዘነጋ ተግባር ነው፡፡

**ሁለተኛው ደረጃ** በፈተና ወቅት መደረግ ያለባቸውን ጥንቃቄዎች የሚመለከት ሲሆን ፈተናውን በተሳካ ሁኔታ ለመጨረስ እጅግ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ **በፈተና ጊዜ መጀመሪያ** መደረግ ያለበት ፈታኙ በሚያዘው መሰረት ተገቢ በሆነ ቦታ ላይ መቀመጥ ነው፡፡ **ከዚያ** የፈተናው ወረቀት ሲሰጥ ረጋ ብሎ መመሪያዎችንና ጥያቄዎችን በደንብ መመልከት ይገባል፡፡ **ቀጥሎ** መፃፍ የሚገባቸውን እንደስም፣ ክፍል፣ ቁጥር ያሉ ነገሮችን በትክክልና በተገቢው ቦታ ማስፈር ይገባል፡፡ **ከዚያ በኂላ** የተሰጠውን ሰዓት በመመልከት ረጋ ብሎ ደጋሞ እያነበቡ መስራት ያስፈልጋል፡፡

**ሶስተኛው ደረጃ** ከፈተና በኂላ መደረግ የሚገባቸውን ተግባራት የሚመለከት ነው፡፡ ከፈተናው ከወጡ በኂላ **በመጀመሪያ** ነገሮችን ወዲያው ለመርሳት መሞከር ብልህነት ነው፡፡ አለበለዚያ ቀጣይ ፈተና ካለ ለዚያ የሚደረግ ዝግጅትን ይሻማል፡፡ **ከዚያም** ባለፈው ፈተና ስህተት ተሰርቶ ከሆነ ሌላ ተመሳሳይ ስህተት ላለመስራት ለራስ ቃል መግባትና ትምህርት መውሰድ እንጂ ራስን ማስጨነቅ አይገባም፡፡

## III. የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በድጋፍ መተግበር

**“ሰብል ማምረት” በሚለው ርዕስ አንድ ድርሰት ጻፉ፡፡** ርዕሱን ካነበባችሁ በኋላ በአዕምሯችሁ የምታስታውሱትን ሀሳብ ጻፉ፡፡ በዚህ ወቅት ወደአዕምሯችሁ የመጣ ሀሳብ ሁሉ አስፍሩ፡፡ ለመነሻ ይሆናችሁ ዘንድ በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ውስጥ የተወሰኑ ሀሳቦች ቀርበውላችኋል፡፡ **ድርሰቱን ለመጻፍ የሀሳብ ማዋቀሪያ ቢጋሩ ላይ የቀሩ ሀሳቦችን አሟሉ፡፡** ከቻላችሁ ሀሳቦች እንደየተዛምዷቸው በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ላይ ጻፉ፡፡ **በመቀጠል ሀሳቦቹ ባላቸው ቅደምተከተል መሰረት አስፋፍታችሁ ድርሰታችሁን ጻፉ፡፡**




ድርሰቱን አስፋፍታችሁ ለመጻፍ አሁን በአዕምሮ ጨመቃ ወቅት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ዙሪያ ያሰፈራችኋው ሀሳቦች የትኛው ቀድሞ፣ የትኛው ደግሞ ተከትሎ የሚመጣ እንደሆነ እየለያችሁ ረቂቃችሁን ጻፉ፡፡ ይህም ብቻ ብቻቸውን ተበታትነው የነበሩት ሀሳቦች በተወሰኑ ክፍሎች

ተከፋፍለው በመሰባሰብ በአንቀጾች ተዋቅረው የመጀመሪያውን የጽሁፋችሁን ረቂቅ ለማዘጋጀት ይረዳችኋል።

በመቀጠል በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ዙሪያ ያስፈራችኋውን ሀሳቦችን እንደገና በመቃኘት በረቂቁ ውስጥ ያልተካተቱ ካሉ መርምሩ፤ የሀሳባቹ ቅደምተከተላዊ አደረጃጀት አለመፋለሱንም አረጋግጡ። ከዚያም ረቂቃችሁን እያነበባችሁ በመከለስና በማረም የተሻለ አደረጃጀት ያለው ጽሁፍ ጻፉ። በክለሳችሁ ወቅት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋራችሁ እየታገዛችሁ ከርዕሳችሁ ያፈነገጡ ሀሳቦች አለመካተታቸውን አረጋግጡ፡

## IV. **የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ነጻ ትግበራ**

**"በህይወቴ የማልረሳው ገጠመኝ"** በሚል ርዕስ ድርሰት ለመጻፍ የሚያስችላችሁን የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር አዘጋጁ። በህይወታችሁ የማትረሱትን አስደሳች ወይ አሳዛኝ ገጠመኝ በማስታወስ የገጠመኙን አንኳር መገለጫዎች በቅደምተከተል አስፍሩ። በእያንዳንዱ አንኳር የገጠመኛችሁ መገለጫ ስርም ሊነሱ የሚገባቸውን ንኡሳን ሀሳቦች በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ውስጥ አስፍሩ። እነዚህን መነሻ በማድረግ እያስፋፋችሁ ድርሰታችሁን ጻፉ።



## V. ግምገማና ጽብረቃ

**ከላይ የቀረበውን ልምምድ መሠረት በማድረግ በሚከተሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ያላችሁን ግንዛቤ ግለፁ፡፡**

1.በዚህ ክፍለትምህርት የተማርከው/ሽው የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ምንድን ነበር? ቢጋሩን እየተጠቀሙ የአንድን ጽሑፍ ሀሳቦች ማቅረብ ምን ምን ጠቀሜታዎች አሉት?

2.ከላይ ባደረግከው/ሽው ልምምድ ሀሳቦችን ቅደምተከተላዊ አደረጃጀት ለማሳየት ምን ምን ስልቶችን ተገበርክ/ሽ? የእያንዳንዳቸው ፋይዳስ ምንድን ነው?

3.ከላይ በቀረበው ልምምድ በተማርከው/ሽው የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር በመጠቀም ጽሁፍ ስታዋቅር/ሪ ምን ምን ችግሮች አጋጠሙህ/ሽ? ችግሮችስ እንዴት ለመፍታት ሞከርክ/ሽ?

4.ቅደምተከተላዊ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋርን ለወደፊት በምትጽፍበት/በምትጽፊበት ጊዜ መቼ፣ ለምንና እንዴት እንደምትጠቀምበት/ሚበት በዝርዝር አስረዳ/ጂ፡፡

# ክፍለትምህርት ሁለት

# በዋናና ዝርዝር ሀሳቦች ማዳራጃ ቢጋር መነሻ መጻፍ

## I. ታላሚውን የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ማስተዋወቅ

### 1. ዋናና ዝርዝር የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ምንድን ነው?

የዋናና ዝርዝር ሀሳቦች ማደራጃ ቢጋር አንድን ቁልፍ ርዕሰ ጉዳይ በአብይነትና በንኡስነት አማክለው የሚፈልቁ መረጃዎችን ትስስር ማሳየት የሚያስችል ነው፡፡ በተለይም ተዋረዳዊ የአደረጃጀት ዝምድናዎች ያላቸውን ሀሳቦች ንድፍ በጽሁፍ ለማቅረብ ይበልጥ ምቹ ነው፡፡ ተዋረዳዊ ዝምድና ያላቸው መረጃዎች አብይ ወይም ንኡስ አላባዎች ያላቸው ሲሆኑ ይህ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር በአብዛኛው የአብዥ ዛፍ ቅርጽ ይኖረዋል፡፡ በአንጻሩ ከዋናው ሃሳብ ጋር ዝምድና ያላቸውን መረጃዎች በተዋረድ ማቅረብ ሲያስቸግር ደግሞ የሸረሪት ድር ቅርጽ ያለውን የሀሳብ ማደራጃ መጠቀም ይቻላል፡፡

### 2. ዋናና ዝርዝር የሀሳብ ማደራጃ ቢጋርን ተጠቅመን ሀሳባችንን በጽሁፍ ለማስፋፋት የሚያግዙን ቃላት ወይም ሀረጋት እነማን ናቸው?

ዋናና ዝርዝር የሀሳብ ማደራጃ ቃላት ወይም ሀረጋት በአንድ አንቀጽ ወይም በድርሰት ውስጥ ነገሮች፣ ድርጊቶች፣ ሁነቶች፣ ወዘተ ባላቸው የሀሳብ ደረጃ ለይቶ ለመግለጽ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ የትኛው ነገር ወይም ድርጊት ወይም ሁነት ከየትኛው የሰፋ ወይም ዘርዘር ያለ እንደሆነ ማመላከት ሁነኛ ዓላማቸው ነው፡፡

ጸሃፊዎች አዘውትረው ከሚጠቀሙባቸው **ዋናና ዝርዝር የሀሳብ ማደራጃ ጠቋሚ ቃላት ወይም ሀረጋት** መካከል ቀጥሎ የተዘረዘሩት ይገኙበታል፡፡

**ዋና ሀሳብ አመልካች፡-** ዋናው ነገር…፣ በጠቅላላው…፣ አብዩ ጉዳይ…፣ መሰረታዊው ነገር…፣ ዋናው ጉዳይ…፣ ቁም ነገሩ…፣ ወዘተ.

**ዝርዝር ሀሳብ አመልካች፡-** ለመዘርዘር ያህል…፣ ሲዘረዘሩም…፣ ለምሳሌ…፣ የዚህ አስረጅም…፣ ለመጥቀስ ያህል…፣ አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወዘተ.

## II. የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በምሪት ማለማመድ

**“የአፈር ለምነትን መጠበቅና መንከባከብ”** በሚል ርዕስ ድርሰት እንድጽፍ ታዝዣለሁ እንበል፡፡ በመጀመሪያ ርዕሱን **“ደን መትከል፣ እርከን/ክርት መስራትና የመሬት አጠቃቀምን ማወቅ”** በሚሉ ሦስት ዋና ዋና ሀሳቦች መከፋፈል እንደምችል ወሰንኩ፡፡ በመቀጠል ስለርዕሱ የማውቀውን ራሴን በመጠየቅ በአዕምሮዬ የማስታውሰውን ሀሳብ ሁሉ በሦስቱ ዋና ዋና ሀሳቦች ስር እጽፋለሁ፡፡ በዚህ ወቅት ወደአዕምሮዬ የመጣን ሀሳብ ሁሉ ሳልመርጥ አሰፍራለሁ፡፡ ለመነሻ ይሆኑኝ ዘንድ መጀመሪያ የተወሰኑ የማውቃቸውን ሀሳቦች ከታች በሚታየው የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ላይ ጻፍኩ፡፡ ድርሰቱን ለመጻፍ የሀሳብ ማዋቀሪያ ቢጋሩ ላይ ሌሎች ተመሳሳይ ሀሳቦችን መጨመር እችላለሁ፡፡ በተቻለኝ መጠን ሀሳቦችን እንደየተዛምዷቸው በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ላይ ለማስፈር ሞክሬያለሁ፡፡ በመቀጠል በሦስቱ ዋና ዋና ሀሳቦች ስር ያሉ ዝርዝሮችን ባላቸው ዝምድናና ደረጃ መሰረት እያዋቀርኩ ረቂቄን ለመጻፍ ሙከራ አደረግኩ፡፡




አሁንም በአዕምሮ ጨመቃ ወቅት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ዙሪያ ያሰፈርኳቸውን ሀሳቦች በማመዛዘን ባላቸው ስፋት የትኛው ቀድሞ፣ የትኛው ደግሞ ተከትሎ የሚመጣ እንደሆነ እየለየሁ ረቂቄን በመጻፍ ላይ ነኝ፡፡ በዚህ ሂደት ዋናና ንኡስነት (ስፋትና ጥበት) ለማሳየት የሀሳብ ዝምድና ደረጃ ጠቋሚ ቃላትንና ሀረጋትን እየመረጥኩ እየተገለገልኩ ነው፡፡ በዚህ

ሁኔታ ረቂቁን አዘጋጅቼ ጨረስኩ፡፡ ረቂቁን መላልሼ በማንበብ ካረምኩ በኋላ የሚከተለውን ጽሁፍ መጻፍ ቻልኩ፡፡

**የአፈር ለምነትን መጠበቅና መንከባከብ**

አፈር በጎርፍና በነፋስ እንዳይወሰድና ለምነቱን እንዳያጣ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም መንከባከብ ይቻላል፡፡ አንዱና የመጀመሪያው አማራጭ ተራራማ ቦታዎችን በደን መሸፈን ነው፡፡ በዚህም ዛፎች አፈር በጎርፍ እንዳይሸረሸርና በነፋስ እንዳይጠረግ መከላከል ይችላሉ፡፡ ዛፎች በሥራቸው አማካይነት አፈሩን ቆንጥጠው መሬቱ በጎርፍ እንዳይሸረሸር ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዛፎች የአፈርን ለምነትና ውፍረት በመጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ከዛፎች የሚረግፉት ቅጠላቅጠሎችም ሆኑ ያረጁ ዛፎች ስራስሮች ወደብስባሽ ስለሚለወጡ የአፈር ለምነትን ይጨምራሉ፡፡ ስለዚህ ተራራማ ቦታዎችን በደን በመሸፈን የአፈር መከላትን በመከላከል ለምነትን መጨመር ይቻላል፡፡

በዳገታማ ቦታዎች ላይ እርከንና ክትር መሥራት ሌላው ዋና የአፈርን መሸርሸርን መከላከያ ስልት ነው፡፡ ዳገታማ መሬቶችን አግድም በማረስ፣ በድንጋይና በአፈር እርከን በመሥራት አፈሩ ቁልቁል በጎርፍ ታጥቦ እንዳይሄድ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህም ከከፍተኛ ቦታ የሚንደረደረው ጎርፍ እርከኑ ላይ እንዲያርፍና ደለል እንዲሠራ ያደርጋል፡፡ እርከኑ ላይ ያረፈው አፈርም ውኃ መቋጠር ስለሚችል ለምነትና ርዕበት ይኖረዋል፡፡ ለረዥም ጊዜ በጎርፍ ምክንያት ገደላማ በሆኑ ቦታዎች ላይ ደግሞ ክትር በመስራት የጎርፍ ፍጥነትን መግታትና አፈሩ ታጥቦ ወደሌላ ቦታ እንዳይሄድ መከላከል ይቻላል፡፡

የአፈር ለምነትን ለመጠበቅ የመሬት አጠቃቀም ስርዓትን መከተልም ሁነኛ የአፈር ለምነት መጠበቂያና መንከባከቢያ ስልት ነው፡፡ መሬትን ለእርሻ፣ ለደን ልማት፣ ለግጦሽ በማለት ከፋፍሎ በሥርዓት መጠቀም የመሬት ለምነትን ይጨምራል፡፡ ይህ ሲሆን አፈር ያለአግባብ አይባክንም፡፡ ሰብልን አፈራርቆ መዝራትም የአፈር ለምነትን መጠበቂያ ስርዓት ነው፡፡ ይህም ሲባል የጥራጥሬ እህሎች ከሌሎች ሰብሎች ጋር በየዓመቱ እያፈራረቁ መዝራት አፈሩ በተለያዩ ንጥረነገሮች እንዲበለጽግ በማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይሰጣል፡፡

## III. የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በድጋፍ መተግበር

**"የጋራ ሀላፊነትን መወጣት"** በሚል ርዕስ ድርሰት ጻፉ፡፡ ርዕሱን ካነበባችሁ በኋላ በአዕምሯችሁ የምታስታውሱትን ጻፉ፡፡ በዚህ ወቅት ወደአዕምሯችሁ የመጣ ሃሳብ ሁሉ  አስፍሩ፡፡ ለመነሻ

ይሆናችሁ ዘንድ በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ውስጥ ዋና ዋና ሀሳቦች ስለሰፈሩላችሁ እናንተ በእያንዳንዳቸው ስር ሊነሱ ይገባል የምትሏቸውን ዝርዝር ሀሳቦች በማስታወስ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩን አሟሉ፡፡ በመቀጠል እያንዳንዱን ዋና ሀሳብ በስሩ ካሰፈራችኋቸው ንኡስ ሀሳቦች መነሻ በማድረግ ድርሰታችሁን ጻፉ፡፡




ድርሰቱን አስፋፍታችሁ ለመጻፍ አሁን በአዕምሮ ጨመቃ ወቅት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ዙሪያ ያሰፈራችኋው እያንዳንዳቸውን ዋና ሀሳቦች የየአንቀጻችሁ መነሻ አድርጋችሁ ተጠቀሙ፡፡ የትኞቹ ዝርዝር ሀሳቦችም በዋና ሀሳቡ ስር መግባት እንዳለባቸው እያረጋገጣችሁ ሀሳቦቹን በማስፋፈት ረቂቃችሁን ጻፉ፡፡ ይህም ብቻ ብቻቸውን ተበታትነው የነበሩት ሀሳቦች በተወሰኑ ክፍሎች ተከፋፍለው በመሰባሰብ በአንቀጾች ተዋቅረው የመጀመሪያውን የጽሁፋችሁን ረቂቅ ለማዘጋጀት ይረዳችኋል፡፡

በመቀጠል በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ዙሪያ ያሰፈራችኋውን ሀሳቦችን እንደገና በመቃኘት በረቂቁ ውስጥ ያልተካተቱ ካሉ መርምሩ፤ እያንዳንዱ ዋና ሀሳብ በስሩ የያዛቸው ዝርዝር ሀሳቦች አብረውት የሚሄዱ መሆናቸውን አረጋግጡ፡፡ ከዚያም ረቂቃችሁን እያነበባችሁ በመከለስና

በማረም የተሻለ አደረጃጀት ያለው ጽሁፍ ጻፉ፡፡ በክለሳችሁ ወቅት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋራችሁ እየታገዛችሁ ከርዕሳችሁ ያፈነገጡ ሀሳቦች አለመካተታቸውን አረጋግጡ፡

## IV. የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ነጻ ትግበራ

**"የቤተሰብ ምጣኔ"** በሚል ርዕስ ድርሰት ለመጻፍ የሚያስችላችሁን የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር አዘጋጁ፡፡ በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ታግዛችሁ ርዕሱ በዋና ዋና ሀሳብ ከፋፍሉ፡፡ በእያንዳንዱ ዋና ሀሳብ ስርም ሊነሱ የሚገባቸውን ንኡሳን ሀሳቦች አስፍሩ፡፡ በመቀጠል እያንዳንዱን ዋና ሀሳብ በስሩ ካሰፈራችኋቸው ንኡስ ሀሳቦች መነሻ በማድረግ ድርሰታችሁን ጻፉ፡፡




## V. ግምገማና ጽብረቃ

**ከላይ የቀረበውን ልምምድ መሠረት በማድረግ በሚከተሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ያላችሁን ግንዛቤ ግለፁ፡፡**

1.በዚህ ክፍለትምህርት የተማርከው/ሽው የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ምንድን ነበር? ቢጋሩን እየተጠቀሙ የአንድን ጽሑፍ ሀሳቦች ማቅረብ ምን ምን ጠቀሜታዎች አሉት?

2.ከላይ ባደረግከው/ሽው ልምምድ ሀሳቦችን በደረጃ ዋናና ንዑስ ብለህ/ሽ ለመከፋፈል ምን ምን ስልቶችን ተገበርክ/ሽ? የእያንዳንዳቸው ፋይዳስ ምንድን ነው?

3.ከላይ በቀረበው ልምምድ በተማርከው/ሽው የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር በመጠቀም ጽሁፍ ስታዋቅር/ሪ ምን ምን ችግሮች አጋጠሙህ/ሽ? ችግሮችስ እንዴት ለመፍታት ሞከርክ/ሽ?

4.ቅደምተከተላዊ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋርን ለወደፊት በምትጽፍበት/በምትጽፊበት ጊዜ መቼ፣ ለምንና እንዴት እንደምትጠቀምበት/ሚበት በዝርዝር አስረዳ/ጂ፡፡

# ክፍለትምህርት ሦስት

# በምክንያትና ውጤት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር መነሻ መጻፍ

## I. ከታላሚውን የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ማስተዋወቅ

### 1. የምክንያትና ውጤት የሀሳብ ውቅር ምንድን ነው?

*ምክንያት አንድ ነገር ለምን እንደተከሰተ የሚነግረን ሀሳብ ነው፡፡ ውጤት ደግሞ በአንድ ነገር ምክንያት ምን እንደተከሰተ የሚጠቁመን ሀሳብ ነው፡፡ ምክንያትና ውጤት የሀሳብ ውቅርም ሁነቶች ወይም ነገሮች የተከሰቱበትን ሰበብና ያስከተሉትን ውጤት በትስስር በማቅረብ ሀሳብ የሚደራጅበት የሀሳብ አወቃቀር ዓይነት ነው፡፡ ይህ አወቃቀር ሀሳቦችን ባላቸው ምክንያታዊ ተዛምዶ የሚያስተሳስር ነው፡፡ የምክንያትና ውጤት ትስስር መስመሮቹ መጠን በጨመረ ቁጥር የተዛምዶው ውስብስብነት ከፍ ይላል፡፡ በሌላ አባባል አንድ ምክንያት በርካታ ውጤቶችን ወይም በርካታ ምክንያቶች አንድ ውጤትን የሚያስገኙበት ሁኔታ ሲፈጠር ተዛምዶው የተወሳሰበ ይሆናል፡፡ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ መልክዓምድራዊ፣ ስነህይወታዊ፣ ወዘተ ለውጦች የተከሰቱባቸውን ሁኔታዎች የሚገልፁ ጽሁፎች በአመዛኙ የምክንያትና ውጤት ትስስርን መሰረት አድርገው ይዋቀራሉ፡፡*

### 2. የምክንያትና ውጤት የሀሳብ ውቅርን ጠቋሚ ቃላት ወይም ሀረጋት እነማን ናቸው?

***የምክንያትና ውጤት** የሀሳብ ዝምድና ጠቋሚ ቃላት ወይም ሀረጋትም በአንድ አንቀፅ ወይም በጠቅላላ ፅሁፉ ውስጥ ነገሮች፣ ድርጊቶች፣ ሁነቶች፣ ወዘተ የተከሰቱበትን ሰበብና ያስገኙትን ውጤት የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ የትኛው ነገር ወይም ድርጊት ወይም ሁነት የትኛውን ውጤት እንዳመጣ ወይም የትኛው ውጤት በምን ሰበበ ነገር ወይም ድርጊት ወይም ሁነት እንደተከሰተ ማመላከት ሁነኛ ዓላማቸው ነው፡፡*

*ፀሃፊዎች አዘውትረው ከሚጠቀሙባቸው **ምክንያትና ውጤት የሀሳብ ዝምድናን ጠቋሚ ቃላት ወይም ሀረጋት** መካከል ቀጥሎ የተዘረዘሩት ይገኙበታል፡፡*

*ምክንያቱም፣ በ…ምክንያት፣ ስለ- ፣ በ…ሰበብ፣ ለምን፣ በ….የተነሳ፣ በ…መሰረት፣ ከ…የተነሳ፣ የ…እንደሆነ፣ እንደዚያ ከሆነ፣ (ለዚህ) መነሻው፣ ይህን ያመጣው…፣ ይህ ሊሆን (ሊከሰት፣*

ሊመጣ) የሚችለው፣ ውጤቱ፣ ለ...ዓላማ፣ የተከሰተው፣ የተገኘው፣ ያስከተለው፣ የዳረገው፣ መንስኤው፣ ወደ...ያመራል፣ ያስገኛል፣ ወዘተ...

## II. የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በምሪት ማለማመድ

**"ጠንካራ የስራ ባህልና ቱርፋቶቹ"** በሚል ርዕስ በምክንያትና ውጤት ትስስር የተገነባ ድርሰት እንድጽፍ ታዘዝኩ እንበል፡፡ በመጀመሪያ ስለርዕሱ በማሰላሰል **"ምጣኔ ሀብትን ማጎልበት፣ የግለሰብ ኑሮ ማሻሻልና ማህበራዊ እድግ "** የሚሉ ሦስት ውጤቶች እንደሚኖሩት ወሰንኩ፡፡ በመቀጠል ከእነዚህ ውጤቶች ጋር ተያያዥ የሆኑ የማውቃቸውን ሀሳቦች ራሴን በመጠየቅ እጽፋለሁ፡፡ በዚህ ወቅት ወደአዕምሮዬ የመጣን ሀሳብ ሁሉ ሳልመርጥ አሰፍራለሁ፡፡ ለመነሻ ይሆኑኝ ዘንድ መጀመሪያ የተወሰኑ የማውቃቸውን ሀሳቦች ከታች በሚታየው የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ላይ ጻፍኩ፡፡ ድርሰቱን ለመጻፍ የሀሳብ ማዋቀሪያ ቢጋሩ ላይ ሌሎች ተመሳሳይ ሀሳቦችን መጨመር እችላለሁ፡፡ በተቻለኝ መጠን ሀሳቦችን እንደየተዛምዷቸው በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ላይ ለማስፈር ሞክሬያለሁ፡፡ በመቀጠል ሦስቱን ውጤቶች ለየብቻ በአንቀጽ በመካፋፈል በስራቸው ሊነሱ የሚገባቸውን ዝርዝሮች እየጨመርኩ ረቂቁን ለመጻፍ ሙከራ አደረግኩ፡፡




አሁንም በአዕምሮ ጨመቃ ወቅት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ዙሪያ ያሰፈርኳቸውን ሀሳቦች በማመዛዘን የምክንያትና ውጤት ግንኙነት እየመዘንኩ ረቂቁን በመጻፍ ላይ ነኝ፡፡ በዚህ ሂደት የትኛው ሀሳብ ምክንያት የትኛው ደግሞ ውጤት(ውጤቶች) እንደሆኑ ለማሳየት የምክንያት

ውጤት ትስስር ጠቋሚ ቃላትንና ሀረጋትን እየመረጥኩ እየተገለገልኩ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ረቂቁን አዘጋጅቼ ጨረስኩ፡፡ ረቂቁን መላልሸ በማንበብ ካረምኩ በኋላ የሚከተለውን ጽሁፍ መጻፍ ቻልኩ፡፡

**ጠንካራ የስራ ባህልና ትሩፋቶቹ**

ጠንካራ የሥራ ባህል የግለሰብን የገቢ መጠን በማሳደግ ኑሮን ለማሻሻል ይጠቅማል፡፡ በተሰማሩበት የሙያ መስክ ጉልበትንና ዕውቀትን በአግባቡ በሥራ ላይ ማዋል፣ ምርታማነትን በማሳደግ ገቢን ለመጨመር ይረዳል፡፡ ገቢ ባደገ መጠንም የአኗኗር ዘይቤ ይለወጣል፡፡ የጤና፣ የትምህርት፣ የፍጆታ ግብዓቶች በማሟላት ደስተኛ ቤተሰብን ይፈጥራል፡፡ የቤተሰብ ፍላጎት ሲሟላም ቤተሰባዊ ሰላምና ደስታ ይሰፍናል፡፡ ደስተኛ መሆንም በተሰማሩበት ሙያ በራስ የመተማመን ስሜት ያጎለብታል፡፡ ለአዲስ የፈጠራ ሥራ በመነሳሳት በየሙያው የተሻለ ሥራ ለመሥራት ያስችላል፡፡

ጠንካራ የሥራ ባህል ማኅበራዊ ዕድገት ያመጣል፡፡ የማኅበረሰቡ አባላት በመረዳዳትና በመተጋገዝ የታቀደን ሥራ በጋራ መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡ አንዳቸው ያላወቁትን ከሌሎች በመማር የሚያጋጥማቸውን ተግዳሮት በመፍታት ውጤታማ ይሆናሉ፡፡ ጉልበትንና ግብዓቶችን በጋራ ከተጠቀሙ ብዙ ጊዜ የሚወስድን ሥራ በወቅቱ ለመጨረስ ይችላሉ፡፡ በመሥራታቸው በራስ የመተማመን ስሜትን በማዳበር አካባቢያቸውን ለመለወጥና ለማሳደግ ይነሳሳሉ፡፡

ጠንካራ የሥራ ባህል ህይወትን በአግባቡ ለመምራትና የቤተሰብን ፍላጎት ለማሟላት ያስችላል፡፡ የግለሰብ ለውጥና ዕድገት የቤተሰብን ብሎም የማኅበረሰብ ዕድገት ያመጣል፡፡ በዚህም የሀገር ምጣኔሀብት ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ ስለሚሄድ መሻሻል ይታያል፡፡ የሀገር ምጣኔሀብት ዕድገት ደግሞ የዜጎችን ኑሮ ይለውጣል፤ መሠረተልማቶችን ያስፋፋል፤ ዜጎችን የትምህርት፣ የጤናና የመሳሰሉት ማኅበራዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡

## III. የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በድጋፍ መተግበር

**“የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ፋይዳዎች” በሚለው ርዕስ አንድ ድርሰት ጻፉ፡፡** ርዕሱን ካነበባችሁ በኋላ በአዕምሯችሁ የምታስታውሱትን ጻፉ፡፡ በዚህ ወቅት ወደአዕምሯችሁ የመጣ ሃሳብ ሁሉ

አስፍሩ፡፡ ለመነሻ ይሆናችሁ ዘንድ በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ውስጥ በአካል ብቃት እንቅስቃሴ ከሚገኙ ውጤቶች ጥቂቶቹ ስለሰፈሩላችሁ እናንተ በተጨማሪ ሊነሱ ይገባል የምትሏቸውን ውጤቶች በማስታወስ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩን አሟሉ፡፡ በመቀጠል እያንዳንዱን ውጤት ከምክንያቱ ጋር ያለውን ትስስር መነሻ በማድረግ ድርሰታችሁን ጻፉ፡፡




ድርሰቱን አስፋፍታችሁ ለመጻፍ አሁን በአዕምሮ ጨመቃ ወቅት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ዙሪያ ያሰፈራችኋው እያንዳንዳቸውን ውጤቶች የየአንቀጻችሁ መነሻ አድርጋችሁ አስፋፉ፡፡ የትኞቹ ዝርዝር ሀሳቦችም በየምክንያት ውጤት ትስስሩ ውስጥ መገለጽ እንዳለባቸው እያረጋገጣችሁ ሀሳቦቹን በማስፋፈት ረቂቃችሁን ጻፉ፡፡ ይህም ብቻ ብቻቸውን ተበታትነው የነበሩት ሀሳቦች በተወሰኑ ክፍሎች ተከፋፍለው በመሰባሰብ በአንቀጾች ተዋቅረው የመጀመሪያውን የጽሁፋችሁን ረቂቅ ለማዘጋጀት ይረዳችኋል፡፡

በመቀጠል በሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ዙሪያ ያሰፈራችኋውን ሀሳቦችን እንደገና በመቃኘት በረቂቁ ውስጥ ያልተካተቱ ካሉ መርምሩ፤ እያንዳንዱ ምክንያትና ውጤት ትስስርም ተጠየቁ ያልተፋለሰ መሆኑን አረጋግጡ፡፡ ከዚያም ረቂቃችሁን እያነበባችሁ በመከለስና በማረም የተሻለ አደረጃጀት ያለው ጽሁፍ ጻፉ፡፡ በክለሳችሁ ወቅት በሀሳብ ማደራጃ ቢጋራችሁ እየታገዛችሁ ከርዕሳችሁ ያፈነገጡ ሀሳቦች አለመካተታቸውን አረጋግጡ፡፡

## IV.የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ነጻ ትግበራ

**"ጊዜን በከንቱ ማሳለፍ"** በሚል ርዕስ ድርሰት ለመጻፍ የሚያስችላችሁን የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር አዘጋጁ:: ርዕሱን በምክንያትና ውጤት ከፋፍሉ:: ምክንያቶቹንና ውጤቶቹን የሚያሰፉ ንኡሳን ሀሳቦች አስፍሩ:: በመቀጠል ሀሳባችሁን አስፋፍታችሁ ድርሰታችሁን ጻፉ::




## VI. ተጨማሪ ልምምድ

**"የውሀ ብክለትና መንስኤዎቹ"** በሚል ርዕስ ድርሰት ለመጻፍ ተገቢ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ካዘጋጃችሁ በኋላ ተገቢ ምክንያቶቹን አስፍሩ:: በመቀጠልም ሀሳቦቹን አስፋፍታችሁ ድርሰታችሁን ጻፉ::

## VII. ግምገማና ዕብረቃ

**ከላይ የቀረበውን ልምምድ መሠረት በማደረግ በሚከተሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ያላችሁን ግንዛቤ በፅሁፍ ግለፁ::**

1.በዚህ ክፍለትምህርት የተማርከው/ሽው የቴክስት ውቅር ብልሃት ምንድን ነበር? አንድን ርዕስ በምክንያትና በውጤት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ተከትሎ መጻፍ ምን ምን ጠቀሜታዎች አሉት?

2.ከላይ ባደረግከው/ሽው ልምምድ በጽሁፍህ/ሽ ውስጥ የምክንያትና ውጤት የሀሳብ ትስስር ለማሳየት ምን ምን ስልቶችን ተገበርክ/ሽ? የእያንዳንዳቸው ፋይዳስ ምንድን ነው?

3.ከላይ በቀረበው ልምምድ የምክንያትና ውጤት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋርን ተጠቅመህ/ሽ ስትጽፍ/ፊ ምን ምን ችግሮች አጋጠሙህ/ሽ? ችግሮችስ እንዴት ለመፍታት ሞከርክ/ሽ?

4.የምክንያትና ውጤት የሀሳብ ማደራጃ ቢጋርን መሰረት ያደረገ የመጻፍ ብልሃትን ለወደፊት መቼ፣ ለምንና እንዴት ባለ ሁኔታ ተግባራዊ አደርገዋለሁ ብለህ/ሽ ታስባለህ/ ታስቢያለሽ? መልስህን/ሽን በዝርዝር አብራራ/ሪ፡፡

# ክፍለትምህርት አራት

# በማወዳደርና ማነጻጸር የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር መነሻ መጻፍ

## I.ታላሚውን የቴክስት ውቅር ብልሃት ማስተዋወቅ

1. *አወዳዳሪና አነጻጻሪ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር ምንድን ነው?*

***አወዳዳሪና አነጻጻሪ የሀሳብ ማደራጃ ቢጋር*** *ሀሳቦች ወይም ነገሮች ባሏቸው መሰረታዊ ገጽታዎች ወይም ጥራት ወይም ባህርያት አኳያ እያመዛዘኑ ለማወዳደርና ለማነጻጸር ወይም አንድነትና ልዩነታቸውን ለማተት በስራ ላይ የሚውል ስልት ነው፡፡ የማወዳደር ወይም የማነፃፀር የሀሳብ ውቅር ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮች ወይም ሁነቶች ወይም ድርጊቶች ያሏቸውን ተመሳስሎዎች ወይም ልዩነቶች በማሳየት የሚዋቀር ነው፡፡ በመሆኑም ሀሳቦች ባላቸው አንድነት ወይም ልዩነት እየተወዳደሩ ካልሆነም እየተነፃፀሩ የሚዛመዱበት ስልት ነው፡፡ የሚወዳደሩት ወይም የሚነፃፀሩት ጉዳዮች ቁጥራቸውና ዝርዝር ገፅታዎቻቸው በበዙ ቁጥር የተዛምዶ ደረጃው ውስብስብነት ይጨምራል፡፡ ዋና ዋና ሃሳቦቹም ንፅፅርን፣ ውድድርን ወይም አማራጭ እይታዎችን ማቅረብ በሚያስችል ሁኔታ ይደራጃሉ፡፡*

2. *የማወዳደርና ማነፃፀር የሀሳብ ውቅርን ጠቋሚ ቃላት ወይም ሀረጋት እነማን ናቸው?*

*ውቅር ጠቋሚ ቃላት ወይም ሀረጋት የሚባሉት አንድን አንቀፅ ወይም ፅሁፍ በምናነብበት ጊዜ ሀሳቡ እንዴት እንደተዛመደ ለመለየት የሚያግዙን የሀሳብ ማሸጋገሪያ ወይም ማገጣጠሚያዎች ናቸው፡፡* ***የማወዳደር ወይም የማነፃፀር*** *የሀሳብ ዝምድና ጠቋሚ ቃላት ወይም ሀረጋትም በአንድ አንቀፅ ወይም በጠቅላላ ፅሁፉ ውስጥ አንድ ነገር፣ ድርጊት ወይም ሁነት ከሌላ ነገር፣ ድርጊት ወይም ሁነት ጋር ያለውን ተመሳሳይነት ወይም ልዩነት የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ በማወዳደር የሚቀርብን ሀሳብ የሚጠቁሙት በሚወዳደሩት ጉዳዮች ዙሪያ የሚታዩ ተመሳስሎዎችን ሲያመላክቱ፣ በማነፃፀር የሚቀርብን ሀሳብ የሚጠቁሙት ደግሞ በጉዳዮቹ ዙሪያ የሚታዩ ልዩነቶችን ይጠቁማሉ፡፡*

*ፀሃፊዎች አዘውትረው ከሚጠቀሙባቸው* ***የማወዳደር ወይም የማነፃፀር የሀሳብ ዝምድናን ጠቋሚ ቃላት ወይም ሀረጋት*** *መካከል ቀጥሎ የተዘረዘሩት ይገኙበታል፡፡*

***ማነጻጸርን ከሚጠቁሙት መካከልም*** *ከ.. የሚለየው፣ በአንፃሩ፣ በሌላ በኩል፣ በተቃራኒው፣ ከዚህ በተለየ፣ በምትኩ፣ ከ…ይልቅ፣ ግን፣ ነገርግን፣ ከዚህ በተገላቢጦሹ፣ በተለየ መንገድ፣*

ያነሰ፣ በላቀ፣ በበለጠ፣ ሲሆን፣ ልዩነታቸው፣ የሚለያያቸው፣ እንጂ፣ ወዘተ. የሚሉ ይገኙበታል፡፡

**ማወዳደርን ከሚጠቁሙት ውስጥም** በተመሳሳይ፣ እኩል፣ ይጋራሉ፣ ይመሳሰላሉ፣ ልክ እንደ… ሁሉ፣ በጋራ፣ የጋራ ባህርያቸው፣ እንደዚሁ ሁሉ፣ ….ብቻ ሳይሆን….ጭምር፣ አንድነታቸው፣ በትይዩ፣ ተመሳስሏቸው፣ የሚያዛምዳቸው፣ መሳለመሳ፣ በአቻነት፣ ወዘተ. የሚሉ ይገኙበታል፡፡

## II. የሀሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በምሪት ማለማመድ

